

GENDER & ADOLESCENCE: GLOBAL EVIDENCE

የመነሻ ጥናት
ተከታታይ ሪፖርት

# የታዳጊዎች ደህንነት በኢትዮጵያ፡ በጾታ የተለዩ ችሎታዎች፣ አውዶችና የለውጥ ስትራቴጂዎች ፍተሻ

## በጌጅ መሰረታዊ ግኝቶች ላይ ተመስርቶ የተቀናጀ ሪፖርት

ኒኮላ ጆንስ፣ ሳራ ቤርድ፣ ጆአን ሂክስ፣ ኤልሳቤጥ ፕሬስለር-ማርሻል፣ ጣሰው ወልደሃና እና ወርቅነህ ያደቴ

ሜይ 2020

## ስጋና

ተመራማሪዎቹ መሰረቱን በኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋም ያደረገውን የጌጅ ኢትዮጵያ የመጠናዊ ምርምር ቡድን አባላት በተለይም ለጫኔ እጅጉና ለመሰለ አርዓያ፣ እንዲሁም ለጌጅ ኢትዮጵያ አይነታዊ ምርምር ቡድን አባላት ለሆኑት ለአብርሃም ኢያሱ፣ አሚን አብዱልቃድር፣ አይሻ አህመድ፣ ፋጡማ አቡበከር፣ ፋጡማ ኑሬ፣ ፍጹም ወርቅነህ፣ ዶ/ር ጉዳይ እምሬ፣ ዶ/ር ካሳሁን ጥላሁን፣ ኪያ ገዛኸኝ፣ መቲ ከበደ፣ ናርዶስ ጩታ፣ እና ይታገሱ ገበየሁ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ። ለትርጉምና ድምጽ ክተባ አባላት ለሆኑት አብርሃም አለሙ፣ ብዙአየሁ አየለ፣ እንደሻው የማነ፣ ጌታሁን ሺፈራው፣ ሄለን ደገፋ፣ ህሊና አሰፋ፣ ማዘንጊያ ቢራ፣ መና መኮንን፣ ተፈራ ጎሹ፣ ትግስት ተንስኡ፣ ጸጋ መለሰ፣ ጽኑ አምደስላሴ፣ ወልዴ አስፋው እና የሺ ሙላቱም ምስጋና ይድረሳቸው።

በሪፖርቱ ዝግጅት ወቅት ከመጀመሪያው ጀምሮ የተሳተፉትንና የማይተመን አስተዋጽኦ ያበረከቱትን ሌቲሻ ሉኒንን ማመስገን እንወዳለን። በተጨማሪም፣ ኢማ ጆንስንና ሜጋን ዴቮናልድ ላደረጉልን ያልተገደበ የምርምር እገዛ እንዲሁም አና ታቦር፣ ቤተልሄም ገብሬ፣ ኤሪክ ኑሜስተርና ማልጎርዛታ ጃኑቺ ኮድ በማድረግ ላደረጉልን ድጋፍ ማመስገን እንወዳለን። በአርትኦት ስራ እጅግ የላቀ ድጋፍ ያደረጉልንን ካትሪን ኦኔልና አና አንድሪኦሊ ልናመሰግናቸው እንወዳለን።

ኖቨምበር 2018 በተካሄደው የጌጅ የመነሻ ጥናት ግምገማ ላይ ተሳትፈው ጠቃሚ ሀሳቦችና ምክሮች ለሰጡን የፌደራልና የክልል ባለሞያዎች በተለይም ለአቶ ስለሺ፣ ሊያ ወልደሚካኤልና አዜብ ረዘነ ምስጋና ማቅረብ እንፈልጋለን።

በመጨረሻም፣ በዚህ ጥናት ላይ ተሳታፊ ለመሆን ፈቃደኛ ሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ ስላሉ ወንድና ሴት ታዳጊዎች የኖሩበትን ልምዳቸውንና ምልከታቸውን ያካፈሉንን ሁሉንም ታዳጊዎች፣ አሳዳጊዎች፣ የማህበረሰብ መሪዎችና አገልግሎት ሰጪዎች ልናመሰግናቸው እንወዳለን። በጥናቱ ውስጥ ባይሳተፉም ፎቶግራፍ እንዲነሱ ለፈቀዱልን ታዳጊዎችና ወላጆቻቸው፣ እውነተኛ ገጽታቸውን በምስል በማስቀረት በኩል ደግሞ ለናታሊ በርትራምስና ላገዟቸው ለኢንግሪድ ጌርካማ ትልቅ ክብር አለን።

ይህንን ሪፖርት ወደ አማርኛ ለተረጎሙልን ለዶ/ር ካሳሁን ጥላሁንም ምስጋናችን ከፍ ያለ ነው።.

### የዋቢ ፅሁፍ ማጣቀሻ ጥቆማ

ኒኮላ ጆንስ፣ ሳራ ቤርድ፣ ጆአን ሂክስ፣ ኤልሳቤጥ ፕሬስለር-ማርሻል፣ ጣሰው ወልደሃና እና ወርቅነህ ያደቴ (2011 ዓ.ም.) የታዳጊዎች ደህንነት በኢትዮጵያ፡ ስርዓተ-ፆታዊ ችሎታዎች፣ አውዶችና የለውጥ ስትራቴጂዎች ፍተሻ፡፡ የጌጅ ኢትዮጵያ መነሻ ጥናት ግኝት ላይ የተመሰረተ ውህድ ሪፖርት፡፡ ለንደን፡-ስርዓተ ፆታና ታዳጊነት፡አለማቀፍ ማስረጃ፡፡

Jones, N., Baird, S., Hicks, J., Presler-Marshall, E., Woldehanna, T. and Yadete, W. (2018) 'Adolescent well-being in Ethiopia: exploring gendered capabilities, contexts and change strategies. A synthesis report on GAGE Ethiopia baseline findings.' London: Gender and Adolescence: Global Evidence.

# ማውጫ


መግቢያ 1

1 ትምህርትና መማር 6

2 አካላዊ ምሉዕነትና ከጥቃት ነጻ መሆን 10

3 ጤንነት፣ አመጋገብ፣ እና የስነተዋልዶ ጤና 14

4 ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት 17

5 ድምጽና ውሳኔ ሰጪነት 22

6 የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት 27

የፖሊሲና ትግበራ ምክረ ሀሳቦች 31

ማጣቀሻዎች 33

አባሪ: የጌጅ ኢትዮጵያ የምርምር ቦታዎች 37

## ምስሎች

ምስል 1: የጌጅ ጽንሰ ሀሳብ ንድፍ 2
ምስል 2: ምርምር የሚካሄድባቸውን ቦታዎች የሚያሳይ የኢትዮጵያ ካርታ 4

## ሰንጠረዦች

ሳጥን 1: የጌጅ መግለጫና የመነሻ ሪፖርቱ ቀጾች 3

## ሰንጠረዦች

ሰንጠረዥ ሀ1: የከተማና ገጠር አካባቢዎች 37
ሰንጠረዥ ሀ2: የጌጅ ምርምር አካባቢዎች በኢኮኖሚና ማህበራዊ ተጋላጭነት መስፈርት 38
ሰንጠረዥ ሀ3: የጌጅ ኢትዮጵያ መነሻ አይነታዊ ምርምር 39

# መግቢያ

ኢትዮጵያ በአለም ላይ ከፍተኛ የወጣት ቁጥር ካላቸው አገሮች አንዷ ስትሆን ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ዜጎቿ ከ20 ዓመት በታች ናቸው።ሀገሪቱ ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የሴትና የወንድ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት የማስገባት ምጣኔ በመጨመር፣ የጤናና ስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተደራሽነት በማስፋፋት፣ እንዲሁም ያለዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ብልት መቁረጥ የመሳሰሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመዋጋት ረገድ ጎልቶ የሚታይ ለውጥ አምጥታለች (Jones et al., 2017; CSA and ICF, 2017)፡፡ ምንም እንኳን ያስመዘገበችው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የድህነት መጠኑን እንዲቀንስ ቢያደርገውም የአለም ባንክ በቅርቡ ባወጣው መረጃ መሰረት ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ህዝብ አንድ አራተኛ የሚሆኑት ዜጎቿ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩባት፣ በአለም ላይ በድህነት ውስጥ የሚኖሩ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ካሉባቸው አምስት አገሮች አንዷ ናት (UNDP Ethiopia, 2018; Katayama, 2019)፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛ የወጣት ስራ አጥነትና ዝቅተኛ የመቀጠር ምጣኔ ይገኝባታል (CBMSIN, 2018)፡፡

ይህ ሪፖርት በዓይነቱ ልዩ በሆነው የጌጅ (ስርዓተ ጾታና ታዳጊነት፡ አለማቀፋዊ መረጃ) ድብልቅ የረጅም ጊዜ ጥናትና ትኩረቱን ዕድሜያቸው ከ10 እስከ 19 ዓመት የሆኑ ወንድና ሴት ታዳጊዎችን ዕምቅ ችሎታዎች ለማጎልበት በሚያግዙ ጉዳዮች፣ አፍላ ወጣትነትን አልፈው ወደ ጎልማሳነት የዕድሜ ክልል በሚሸጋገሩበት ጊዜ የሚያልፉበትን ሂደት በመፈተሸ ላይ ባደረገ የተጽዕኖ ምዘና ጥናት በተገኘ መረጃ የተመሰረተ ነው፡፡ በታዳጊነት ዕድሜ፣ በተለይም የአፍላነትን ዕድሜ ተከትሎ የሚከሰቱ አካላዊ፣ አዕምሮኣዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ለውጦች በይዘታቸውና በሚከሰቱበት ፍጥነት በጨቅላ ህጻንነትና ቅድመ ታዳጊነት ዘመን ከሚታዩት ለውጦች ቀጥሎ የሚመጡ ናቸው፡፡ በሰው ልጅ ህይወት ከሚከሰቱት ከነዚህ እጅግ ወሳኝ ለውጦች እንዲሁም በዓለም ላይ የታዳጊዎች ቁጥር ከ1.2 ሚሊዮን ባለይ ከመሆኑና አብዛኞቹ ደግሞ በማደግ ላይ ባለው ደቡባዊው ዓለም የሚኖሩ ከመሆናቸው የተነሳ የታዳጊነት ዕድሜ ድህነትን፣ ኢ-እኩልነትንና መገለልን ለመታገል አመቺ መሆኑን የልማት ማህበረሰቡ አብዝቶ ይገነዘባል፡፡ በወጣቶች ላይ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ለታዳጊዎች፣ ለጉልምስና ዘመናቸውና ለልጆቻቸው የሦስት እጥፍ ድርሻ ለመሰብሰብ የሚያስችል ዕድል አለ፡፡

የጌጅ መነሻ የሆነው ሀሳብ የታዳጊነት የመሸጋገሪያ ዕድሜ የወንድና ሴት ልጆችን ህይወት የሚቀርጽ መሆኑ ሲሆን የሚያሳድረው ተጽዕኖ ደግሞ በሚኖሩበት አካባቢ ባለው ማህበራዊና ባህላዊ ድንጋጌዎች ምክንያት በጾታ የተለየ መሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ማህበራዊ ድንጋጌዎች፣ በተለይም በወሲባዊ ጉዳይ ላይ በጥብቅ የሚተገበሩ ሲሆን ታዳጊዎች ወደ ጎልማሳነት ዕድሜ እየተቃረቡ ሲመጡ የሚያልፉባቸው የወደፊት ህይወት ጎዳናዎች ለወንዶችና ሴቶች የተለያዩ እንዲሆኑ ያስገድዳሉ። ማህበራዊ ለውጥን በፍጥነት ለመከታተል፣ ለመረዳትና የፕሮግራም ማሻሻያዎችን ለማድረግ እነዚህ ልዩነቶች ቁልፍ ጉዳይ ናቸው።

ይህ ሪፖርት በድብልቅ የምርምር ግኝቶች ላይ ያተኮረ የጌጅ አጫጭር ተከታታይ ሪፖርቶች አካል ነው። በጌጅ የጽንሰ ሀሳብ ንድፍ መሰረት (ምስል 1 ይመልከቱ) ከመሰረታዊ ግኝቶቻችን በመነሳት የሚከተሉት የወንድና ሴት ታዳጊዎች አቅሞችን ያካተቱ ስድስት ሪፖርቶች ይቀርባሉ፤ (1) ትምህርትና መማር፤ (2) ጤንነት፣ አመጋገብና ጾታዊና ስነተዋልዶ ጤና፤ (3) አካላዊ ምሉዕነትና ከጥቃት ነጻ መሆን፤ (4) ማህበራዊ-ስነልቦናዊ ደህንነት፤ (5) ድምጽና ውሳኔ ሰጪነት፤ እና (6) የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት። ይህ የተቀናጀ ሪፖርት ቁልፍ ግኝቶችንና የፖሊሲ አንድምታዎችን ከዘርፈ-ብዙ አቅሞች እይታ አንጻር ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል።

## የጽንሰ ሀሳብ ንድፍ


የጌጅ ጥናት የታዳጊዎችን አሁናዊም ሆነ የወደፊቱን እድገትና አቅም በሚገባ ለመረዳትና ለማዳበር ስለሚያስችል በአቅሞች፣ የለውጥ ስትራቴጂዎችና አውዶች መካከል ባለው ትስስር ላይ ትኩረት በማድረግ የሁለንተናዊ (Holistic) ፅንሰሀሳብ ንድፍን ይከተላል (ምስል 1 ይመልከቱ)። የጽንሰ ሀሳብ ማዕቀፉ በውጤት፣ ምክንያትና አውዶች አስፈላጊነት ላይ ከሚያተኩረው ከፓውሰንና ቲሌይ (Pawson & Tilley, 1997) ሶስቱ የግምገማ አካሄድ ይዘቶች የተወሰደ ቢሆንም የወንድና ሴት ታዳጊዎችን አቅሞች ለማሻሻል በሚያስችል መልኩ ቀርጸነዋል።

የመጀመሪያው የጽንሰ ሀሳብ ንድፉችን የመሰረት ድንጋይ የሆኑት የአቅም ውጤቶች ናቸው። ለመጀመሪያ ጊዜ አማርትያ ሴን (Amartya Sen,1984; 2004) በተባለ ጸሐፊ በተቀነቀነውና በቤተሰብና ማህበረሰብ መካከል ስላለው ውስብስብ የስርዓተ ጾታ ንቅናቄ የተሻለ ግንዛቤ ለመያዝ፣ በማርታ ኑስባም (Martha Nussbaum, 2011) እና ኔይላ ከቢር (Naila Kabeer, 2003), በዝርዝር የቀረበው የአቅሞችን የመረዳት አካሄድ (capabilities approach) የግለሰቦችን ስኬታማ የመሆን አቅም ለማስፋት ኢኮኖሚያዊ፣ ሰዋዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ስነልቦናዊና ማህበራዊ እሴቶችን ከመፈተሽ አንጻር የተለመደ የአስተሳሰብ ማዕቀፍ እየሆነ መጥቷል፡ ፡(ምስል 2 ይመልከቱ)።

የዚህ አስተሳሰብ በጣም ጠቃሚው ጉዳይ አካል ጉዳተኛ፣ ወይም በለጋ ዕድሜያቸው እናት የሆኑ፣ የተገለሉና ለመድረስ አስቸጋሪ የሆኑ በተለያየ የህይወት መንገድ ላይ የሚገኙ ወንድና ሴት ታዳጊዎች ላይ ማተኮር መቻሉ ነው።

ሁለተኛው የጽንሰ ሃሳብ ንድፉችን መሰረታዊ ነጥብ አውድ ነው። የጽንሰ ሀሳብ ማጠንጠኛችን ሴቶች እና ወንዶች ልጆች

ምስል 1: የጌጅ ጽንሰ ሀሳብ ንድፍ



የሚገኙበትን ስነ-ምህዳራዊ አቀማመጥ የሚመለከት ሲሆን፣ የአቅም ውጤቶቻቸው በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ፣ በሀገር ብሎም በአለም አቀፍ አውዶች ላይ የተመሰረተ ነው።

ሶስተኛውና የመጨረሻው የጽንሰ ሃሳብ ንድፋችን የወንድና ሴት ታዳጊዎች የሚገኙበት ነባራዊ እውነታ በተለያዩ የለውጥ ስትራቴጂዎች፣ ለምሳሌ ታዳጊዎችን በግለሰብ ደረጃ በማብቃት፣ ወላጆችን በመደገፍ፣ ከአዋቂ ወንዶችና ልጆች ጋር በመሳተፍ፣ የማህበረሰብ መሪዎችን በማንቃት፣ ለታዳጊዎች ምላሽ ሰጪ አገልግሎቶችን በማሻሻል፣ እና አስተዳደራዊ ጉድለቶችን በመቅረፍ ሊሻሻል እንደሚችል ያምናል።

## የምርምር ጥያቄዎች

ከጽንሰ ሀሳብ ንድፋችን በመነሳት የጌጅ ምርምር መሰረታዊ የሆኑ ሦስት ጥያቄዎች ተነስተዋል። የጥያቄዎቹ ዋና ትኩረት (1) የታዳጊዎች ተሞክሮና ተሞክሮዎቻቸው በጾታ እንዲሁም በታዳጊዎቹ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ጂኦግራፊካል አቀማመጥ የሚለያዩበት መንገድ፤ (2) ፕሮግራሞችና የሚሰጡ አገልግሎቶች የታዳጊዎችን ተጋላጭነት የሚደርሱበትን እንዲሁም ሙሉ አቅማቸው የሚጎለብትበት መንገድ፤ እና (3) የፕሮግራም ውጤታማነትን፣ ስፋትና እና ዘላቂነትን ከማረጋገጥ አንፃር የፕሮግራም ዲዛይን እና የአተገባበር ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ላይ ነው። ለመነሻ ሪፖርቱ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ጥያቄዎች ላይ የምናተኩር ሲሆን ሦስተኛውን ጥያቄ በመካከለኛ እና በማጠቃለያ ደረጃዎች በዝርዝር እንመረምራለን።

## የጥናቱ ዘዴ

የምርምር ጥያቄዎቹን ለመመለስ ጌጅ ድብልቅ የጥናት ዘዴ ተጠቅሟል። መሰረታዊ መረጃው በኢትዮጵያ ከተማና ገጠር አካባቢዎች ከሚገኙ ከ6,700 በላይ ከሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች ታዳጊዎችና ከወላጆቻቸው በጌጅ መረጃ መሰብሰቢያ (GAGE Consortium, 2018) የተሰበሰበ ነው። በተጨማሪም 220 ከሚሆኑ ታዳጊዎች፣ ወላጆችና ማህበረሰቦች ጥልቅ የተናጠልና የቡድን ዓይነታዊ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችም ተጠቅመናል። ናሙናችን ሁለት የዕድሜ ክልሎችን ማለትም ዕድሜያቸው ከ10–12 ዓመት እና ከ15–17 ዓመት የሆነ ታዳጊዎችን ያካትታል (ለዝርዝር መረጃ አባሪውን ይመልከቱ)።

የመጠናዊና ዓይነታዊ መረጃው የተሰበሰበዉ ከ2017 መጨረሻ እስከ 2018 መጀመሪያ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። ወደፊት የመጠናዊ የዳሰሳ ጥናቱ ሦስት ተከታታይ ምልከታዎችን የሚያካትት ሲሆን፣ ይኸውም በአነስተኛ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉት ዕድሜያቸው ከ12–14 ዓመት፣ ከ13–15 እና ከ15–17 ዓመት ሲደርስ እንዲሁም በከፍተኛ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉት ደግሞ ዕድሜያቸው ከ17–19 ዓመት፣ ከ18–20 እና ከ20–22 ዓመት ሲደርስ የሚካሄድ ይሆናል፡ ፡ ዋናው የአይነታዊ ምርምር በተመሳሳይ መገናኛዎች የሚካሄድ ሲሆን፣ በተጨማሪም ከ2018 መገባደጃ/ 2019 መጀመሪያ ጀምሮ የአቻ ለአቻ እና አሳታፊ ምርምር እናካሂዳለን።

### ሳጥን 1: የጌጅ መግለጫና የመነሻ ሪፖርቱ ቅጾች

ጌጅ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ድብልቅ የረጅም ጊዜ ጥናትና የተጽዕኖ ግምገማ የሚያጠና ሲሆን ትኩረት የሚያደርገውም ዕድሜያቸው ከ10–19 ዓመት የሆኑ ታዳጊዎች ከህጻንነት አፍላ ወጣትነትን አልፈው ወደ ጎልማሳነት በሚሸጋገሩበት ጊዜ የሚኖራቸውን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ ጉዳዮችን በመፈተሽ ላይ ነው።

በታዳጊነት ዕድሜ፣ በተለይም የአፍላነትን ዕድሜ ተከትሎ የሚከሰቱ አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ለውጦች በይዘታቸውና በሚከሰቱበት ፍጥነት በጨቅላ ህጻንነትና ቅድመ ታዳጊነት ዘመን ከሚታዩት ለውጦች ቀጥሎ የሚመጡ ናቸው። በሰው ልጅ ህይወት ከሚከሰቱት ከነዚህ እጅግ ወሳኝ ለውጦች እንዲሁም በዓለም ላይ የታዳጊዎች ቁጥር ከ1.2 ሚሊዮን በላይ ከመሆኑና አብዛኞቹ ደግሞ በማደግ ላይ ባለው ደቡባዊው ዓለም የሚኖሩ ከመሆናቸው የተነሳ የታዳጊነት ዕድሜ ድህነትን፣ ኢ-እኩልነትንና መገለልን ለመታገል አመቺ መሆኑን የልማት ማህበረሰቡ አብዝቶ ይገነዘባል። በወጣቶች ላይ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ለታዳጊዎች፣ ለጉልምስና ዘመናቸውና ለልጆቻቸው የሦስት እጥፍ ድርሻ ለመሰብሰብ የሚያስችል ዕድል አለ።

የጌጅ መነሻ የሆነው ሀሳብ የታዳጊነት የመሸጋገሪያ ዕድሜ የወንድና ሴት ልጆችን ህይወት የሚቀርጽ መሆኑ ሲሆን የሚያሳድረው ተጽዕኖ ደግሞ በሚኖሩበት አካባቢ ባለው ማህበራዊና ባህላዊ ድንጋጌዎች ምክንያት በጾታ የተለየ መሆኑ ነው። እነዚህ ማህበራዊ ድንጋጌዎች፣ በተለይም በወሲባዊ ጉዳይ ላይ በጥብቅ የሚተገበሩ ሲሆን ታዳጊዎች ወደ ጎልማሳነት ዕድሜ እየተቃረቡ ሲመጡ የሚያልፉባቸው የወደፊት ህይወት ጎዳናዎች ለወንዶችና ሴቶች የተለያዩ እንዲሆኑ ያስገድዳሉ። ማህበራዊ ለውጥን በፍጥነት ለመከታተል፣ ለመረዳትና የፕሮግራም ማሻሻያዎችን ለማድረግ እነዚህ ልዩነቶች ቁልፍ ጉዳይ ናቸው።

ይህ ሪፖርት በድብልቅ የምርምር ግኝቶች ላይ ያተኮረ የጌጅ አጫጭር ተከታታይ ሪፖርቶች አካል ነው። በጌጅ የጽንሰ ሀሳብ ንድፍ መሰረት (ምስል 1 ይመልከቱ) ከመሰረታዊ ግኝቶቻችን በመነሳት የሚከተሉት የወንድና ሴት ታዳጊዎች አቅሞችን ያካተቱ ስድስት ሪፖርቶች ይቀርባሉ፤ (1) ትምህርትና መማር፤ (2) ጤንነት፣ አመጋገብና ጾታዊና ስነተዋልዶ ጤና፤ (3) አካላዊ ምሉዕነትና ከጥቃት ነጻ መሆን፤ (4) ማህበራዊ-ስነልቦናዊ ደህንነት፤ (5) ድምጽና ውሳኔ ሰጪነት፤ እና (6) የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት። ይህ ተጓዳኝ የተቀናበረ ሪፖርት ከአንድ ባለብዙ ገፅታ ችሎታ ሌንስ ቁልፍ ቁልፍ ግኝቶችን እና የፖሊሲ አንድምታዎችን ያጠቃልላል።


## የምርምር አካባቢዎች

የጥናታችን ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ በከተማ፣ ገጠርና አርብቶአደር ማህበረሰብ ክፍሎች የሚኖሩ ታዳጊዎች ሲሆኑ ከሦስት ክልሎች ማለትም ከአፋር፣ አማራና ኦሮሚያ እንዲሁም ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የተወሰዱ ናቸው (አባሪውን ይመልከቱ)።

የከተማ አካባቢዎች የተመረጡት ሁለት ቁልፍና ተመጋጋቢ የሆኑ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ ነው። እነዚህም: (1) ጉዳትን የሚያባብሱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን መረዳትን አስፈላጊነት የሚያጎላ በኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊዎችና ስርዓተ ጾታ ላይ ያሉ ነባር መረጃዎች እና ማስረጃዎች ግምገማ (Stavropoulou and Gupta-Archer, 2017a; 2017b ይመልከቱ); እና (2) ከሁለቱ የጌጅ ትብብር አስፈፃሚ አካላት፣ ፓዝፋይንደርና ኬር ኢትዮጵያ ጋር የሚደረግ የፕሮግራም አቅም1 ናቸው። ከተጋላጭነት መስፈርቶች ጋር ተያይዞ የመጀመሪያውን ጉዳይ በተመለከተ፣ ያለዕድሜ ጋብቻ በከፍተኛ ሁኔታ የሚታይባቸውን (ወግ አጥባቂ የስርዓተ ጾታ ደንብ ላላቸው እንደ ወካይ) ሁለት ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎችን (አባሪ ይመልከቱ) እና ከፍተኛ መጠን ያለው ያለዕድሜ ጋብቻ የሚከናወንባቸውን ወረዳዎች (Jones et al., 2016 ይመልከቱ) እንዲሁም በኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እና/ወይም በምግብ ዋስትና የተጎዱ አካባቢዎችን መርጠናል (አባሪ ይመልከቱ)። በጠቅላላው በደቡብ ጎንደር 75፣ በምስራቅ ሀረርጌ 80 እና በአፋር 20 ቀበሌዎችን (ማህበረሰቦችን) ጨምሮ በእያንዳንዱ የገጠር ክልል በሚገኙ አምስት ወረዳዎች ውስጥ እንሰራለን።

የከተማ አካባቢዎቹ የተመረጡት አከራካሪ ሆኖ ለቆየው የከተማነት ብያኔ አሰጣጥ የሚሰጡትን ጠቀሜታ ታሳቢ በማድረግ በተለያየ የስፋት ደረጃ ያሉ በመሆናቸው ነው (Hannigan and Richards, 2017; Chant et al., 2017)። ስለሆነም፣ ባቱ የወረዳ ከተማ ስትሆን፣ ደብረ ታቦር ደግሞ የዞን ከተማ፣ እንዲሁም

ምስል 2: ምርምር የሚካሄድባቸውን ቦታዎች የሚያሳይ የኢትዮጵያ ካርታ




ምንጭ: ከዋና ፋይል የተሰራ፡ የኢትዮጵያ የቦታ አስተዳደራዊ ካርታ፡ የጌጅን የጥናት ቦታዎችን ለማሳይት ተሸሽሎ የቀረበ

1 እዚህ ላይ ከተፅዕኖ ግምገማ አኳያ የመጨረሻ የዞንና የወረዳ የጥናት ቦታዎችን ስንመርጥ ከመንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት (መያድ) ጋር ተባባሪ ሆነው የሚሰሩ ድርጅቶች የሚገኙበትንና ከታዳጊዎች ጋር በተገናኘ የሚሰሩበትን ፓኬጅ (አብረናት እንተግብር - በቢልና ሚሊንዳ ጌትስ ፋዉንዴሽን) እና የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ አስገብተናል።

ድሬ ዳዋ የከተማ አስተዳደር ናቸው። ከተሞች ለገጠሩ አካባቢ በሚኖራቸው ቅርበት የከተማና ገጠሩን ሁኔታ ለማወዳደር እንዲያመች ደብረ ታቦር (ደቡብ ጎንደር) እና ድሬዳዋ (ለምስራቅ ሀረርጌ ባለው የቦታ ቅርበት) ተመርጠዋል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ታዳጊዎች ከሥራ ወደ ትምህርት የሚያደርጉትን ሽግግር ለመረዳት ፈልገናል። ስለሆነም ባቱ፣ ጉልህ በሆነ የአበባ መስኖ ኢንዱስትሪ እና በተለይም ከደቡብ ኢትዮጵያ ለሚደረገው የወጣቶች ስደት ማእከልነት ያለው ሚና እንዲሁም ድሬዳዋ፣ አዲስ እየተገነባ ባለው የኢንዱስትሪ ፓርክ እና ወደ መካከለኛው ምስራቅ ለሚደረገው ስደት ኮሪደር ከመሆናቸው የተነሳ ሁለቱም

ከተሞች ለወጣቶች አዳዲስ የሥራ ዕድልና የቅጥር ዓይነቶችን ያሟላሉ። በተጨማሪም ወጣቶቹ ከነዚህ አዳዲስ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ወይም እንደማይሆኑ ማሳየት ይችላሉ።ከዘላቂ ልማት ግቦች ጋር በተገናኘ ‹ማንም ወደኋላ እንዳይቀር› ከሚለው አጀንዳ ጋር ተያይዞ የጌጅ ጠንካራ ትኩረት የሆኑት ተጋላጭ ታዳጊዎች እነዳሉ ሆኖ፣ ናሙናችን የአካል ጉዳት ያለባቸው ታዳጊዎችን፣ ያገቡ ወይም የተፋቱ ታዳጊ ሴቶችን፣ ታዳጊ እናቶችን፣ እንዲሁም ከሌላ አካባቢ ተፈናቅለው የመጡ ማህበረሰቦችን ያካትታል። እነዚህን ታዳጊዎች በሁለት መንገዶች አካተተናቸዋል። የመጀመሪያው አስፈላጊ በሆነው ዕድሜ ላይ የሚገኙ ታዳጊዎችን የነሲብ ናሙና በመጠቀም ሲሆን፣ ሁለተኛው እንደዚህ ያሉ ወጣቶች ብዙውን ጊዜ በማህበረሰባቸው ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን መገለልና መድልዎን ለመቋቋም በማሰብ የታለመ የናሙና ዘዴ በመጠቀም ነው (Muz et al, 2018)።

# 1 ትምህርትና መማር

## 1.1 መግቢያ

ኢትዮጵያ ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የትምህርት ተደራሽነትን ከማስፋት አኳያ ተጨባጭ የሆነ ዕድገት አሳይታለች (UNESCO, 2015)፡፡ በፖሊሲ ውሳኔዎች አማካይነት ለትምህርት የተመደበው በጀት ድርሻ በእጥፍ በማሳደግ እ.ኤ.አ. በ 2013 እስከ 27 በመቶ የደረሰ ሲሆን (World Bank, 2018)፣ መንግስት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ቁጥር ሦስት እጥፍ (በ2017 ወደ 35,000 ገደማ) ማድረስ ችሏል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥርም 3 ሚሊዮን ብቻ የነበረው ወደ 21 ሚሊዮን ደርሷል (MoE, 2018)፡፡ ለአለማቀፉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሽፋን የቀረበ ነበር። ሆኖም ሁሉም የኢትዮጵያ ታዳጊዎች ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት መብታቸውን ለመጠቀም አሁንም ከባድ መሰናክሎች ይገጥሟቸዋል፡፡ የ5ኛ ክፍልን የሚያጠናቀቁ ወጣቶች ግማሽ የሚሆኑት ብቻ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (በ11ኛ እና 12ኛ ክፍሎች) የሚማሩት ከ 10% በታች ሲሆኑ የማቋረጥ መጠኑም ከፍተኛ ነው (ibid.)፡፡ በተጨማሪም፣ "የመማር ደረጃዎች ደካማ ናቸው፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህም ያቆሙ ይመስላሉ" (RISE, 2018)፤ በተለይ ለልጃገረዶች በወርአበባ ምክንያት ወይም በቤት ውስጥ ስራ እንዲሰሩ ስለሚገደዱ ከትምህርት ገበታ ውጪ ሊሆኑ ይችላሉ (Pankhurst et al., 2018; Bastian et al., 2013; MoFED and UN Ethiopia, 2012; Woldehanna et al., 2017; Woldehanna and Pankhurst, 2014)፡፡ በከተማ የሚገኙ 4.6% የሚሆኑት ህጻናት እና በገጠር የሚኖሩ 2.3% የሚሆኑት ሕፃናት ብቻ ትምህርት ቤት እንደሚማሩ የሚገመት ሲሆን፣ አካል ጉዳተኛ ታዳጊዎች የመማር መብታቸውን ለመጠቀም ያላቸው ዕድል በጣም የተገደበ ነው (Katsui et al, 2014; Jones et al., 2018)፡፡

## 1.2 የወጣቾ የወደፊት አላማ/ምኞት

የኢትዮጵያ ታዳጊዎች የትምህርት ፍላጎቶች በጥቅሉ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ (Tefera et al., 2013; Camfield, 2011; Feeny and Crivello, 2015; Jones et al., 2014a, 2016c, 2017)፡፡ ምንም እንኳን ዕድሜያቸው እጨመረ ሲሄድ ለትምህርት ያላቸው ፍላጎት የሚቀንስ ቢሆንም ወደፊት በትምህርት ላይ የሚቆዩባቸውን አመታት መገመት ያስችላል (Favara, 2017)፡፡ የትምህርት ፍላጎት እንደየአካባቢው የተለያየ ቢሆንም፣ ለምሳሌ በደቡብ ጎንደር አካባቢ ያሉ ታዳጊዎች ከፍተኛ የትምህርት ፍላጎት ሲኖራቸው በዞን 5 ያሉት ደግሞ ዝቅተኛ ሲሆን መጠናዊውም ሆነ አይነታዊ ምርምሮቻችን ታዳጊዎች ከፍተኛ የትምህርት ፍላጎት አላቸው የሚለውን አስተሳሰብ ይደግፋሉ። በአጠቃላይ በጥናታችን ውስጥ ከተሳተፉት ታዳጊዎች ውስጥ ሁሉም ማለት ይቻላል (94%) ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመከታተል የሚፈልጉ ሲሆን ሦስት አራተኛ ወይም 61 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል ይፈልጋሉ፡፡ በእርግጥም ፣ ጥቂት ውስንነቶች ቢኖሩም፣ የአይነታዊ ምርምራችን ብዙ ታዳጊዎች ትምህርትን ወደ ስኬት የሚወስዳቸው አድርው እንደሚመለከቱ እና ሙያዊ የሥራ መስኮችን እንደሚመርጡ ያሳያል፡፡ እንዲት የአካል ጉዳት ያለባት የደብረ ታቦር ልጃገረድ እንዳለችው፣ ‹‹ዋናው ጉዳያችን ትምህርት ነው››፡፡ ጥናታችን ታዳጊዎች ከፍተኛ ምኞት እንዳላቸው ያረጋገጠ ቢሆንም፣ አሳሳቢ ምክንያቶችንም አግኝቷል፡ ፡ በመጀመሪያ፣ የትምህርት ምኞቶች በጾታ የተለዩ ናቸው፤ ለምሳሌ በደቡብ ጎንደር ያሉ ልጃገረዶች ከወንዶች ይልቅ ከፍ ያለ ምኞት ሲኖራቸው፣ በምሥራቅ ሐረርጌ ያሉ ወንዶች ደግሞ ከሴቶች የበለጠ ከፍ ያለ ምኞት አላቸው፡፡ ሁለተኛ፣ አስተማሪነትን የመሳሰሉ መማርን የሚጠይቁ አንዳንድ ሙያዎች ታዳጊዎችን ብዙ የሚስቡ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የሚገኘው ደመወዝ መሰረታዊ ዕውቀትን ብቻ ከሚጠይቁ ስራዎች፤ ለምሳሌ በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ ከጫት ምርት ወይም ባካባቢው ከሚሰሩ ስራዎች ከሚገኘው ገቢ ያነሰ ነው፡፡

## 1.3 የወላጅ ድጋፍ

ወላጆች ልጆቻቸው ተቀጥረው ስራ እንዲያገኙና በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ ትምህርት ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘባቸው ለወንድና ሴት ልጆች የሚያደርጉት የትምህርት ድጋፍ ካለፈው ትውልድ የተሻለ ሆኗል (Jones et al., 2014a; 2016c; 2017; Smith et al., 2015)፡፡ ከቦታ ቦታ ልዩነት ቢኖርም አብዛኞቹ ሴት አሳዳጊዎች (98%)፣ ልክ እንደ ብዙዎቹ ታዳጊዎች፣ ልጆቻቸው የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው የከፍተኛ ትምህርት እንዲቀጥሉ የሚፈልጉ መሆናቸውን ጥናታችን ያሳያል፡፡ በእርግጥም የአይነታዊ ምርምራችን፣ አሳዳጊዎች ለትምህርት የሚሰጡት ትኩረት በየአመቱ እየተሻሻለ መምጣቱን ያሳያል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በአንድ በኩል ትምህርት ከእርሻ የሚያላቅቃቸው መሆኑን በአንዳንድ ቦታዎች ያሉ ወላጆች እየተገነዘቡ በመምጣታቸው ነው፡፡ በማህበረሰብ ሐ (ደቡብ ጎንደር) የሚገኝ አንድ ሰው እንዳለው፣ ‹‹በአካባቢያችን የእርሻ መሬት እጥረት አለ፡፡ የእርሻ መተዳደሪያም መሻሻል የማይችል ነው፤ ስለሆነም ወላጆች ልጆቻቸው በትምህርት ላይ እንዲያተኩሩ ያበረታቷቸዋል፡፡››

ይሁን እንጂ ምንም እንኳን መሻሻል ቢኖርም ጥናታችን እንደሚያሳየው በተለይም በምሥራቅ ሐረርጌ ያሉ አንዳንድ ልጃገረዶች ለትምህርት የሚደረግላቸው የወላጅ ድጋፍ ለወንዶች ከሚደረገው ድጋፍ ያነሰ ነው፡፡ይህ የሆነበት ዋና ምክንያት አግላይ ሆነው የስርዓተ ጾታ ድንጋጌ ወላጆቻቸው የልጃገረዶችን ሚና አሳንሰው እንዲመለከቱ ስላደረጋቸው ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ወላጆች ብዙውን ጊዜ ለሴት ልጆቻቸው ለትምህርታቸው ብዙም

ቁሳዊ ድጋፍ አያደርጉላቸውም፤ እንዲሁም ትምህርት እንዳይማሩ የሚያደጋቸውን የቤት ውስጥ ሥራዎች ይጭኑባቸዋል።

## 1.4 ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽነት

በክልሎች መካከል ጉልህ ልዩነት ቢኖርም፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁሉም በሚባል ደረጃ ህጻናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብተዋል (UNESCO, 2018; Ministry of Education, 2018)፡፡ ይሁን እንጂ ጥናታችን አራት መሰናክሎችን ለይቶ፣ ማለትም የመጀመሪያ ምዝገባ፣ መደበኛ ክትትል፣ ቀጣይ ምዝገባ እና ትምህርት በመለየት ታዳጊዎች ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘት መቻላቸውን በተመለከተ፣ ደበልጥ የተወሳሰበ ስዕል ይሰጠናል። ጥናቱ እንዳመለከተው 85% ታዳጊዎች ትምህርት ቤት የተመዘገቡ እና አማካይ ተማሪው በክፍል ደረጃው (4.6 ዓመቱን ትምህርት በ11 ዓመቱ የጠናቀቀ) ቢሆንም፣ የአይነታዊ ምርምራችን የሚያሳየው አንዳንድ ወጣቶች በተለይም በዞን 5 ያሉ ሙሉ በሙሉ ከትምህርት ገበታ ውጪ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከሚገባው በላይ ዘግይተው ሲመዘገቡ፣ በዋነኝነት በእንስሳት እርባታ እና በአርብቶ አደር ቤተሰቦች ዘንድ ከቦታ ቦታ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ምክንያት ነው፡፡ አንዲት በማህበረሰብ መ (ደቡብ ጎንደር) የምትገኝ ቁልፍ የመረጃ ሰጪ እንዳብራራችው፣ "ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ወላጆች የተወሰኑ ልጆቻቸውን እርሶ አደሮች እንዲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ እንዲማሩ ለማድረግ መወሰን አለባቸው"። ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ልጆች ማስተናገድ የሚችል ትምህርት ቤት እጥረት ምክንያት የአካል ጉዳተኛ ልጆች በተለይ ወደ ትምህርት ቤት የሚገቡበት ዕድል የላቸውም።

ጥናታችን በተጨማሪም ብዙ ታዳጊዎች - በተለይም በዞን 5 ያሉ - አንዳንድ ጊዜ ለአንድ ወይም ለሁለት ቀናት፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲበዛ ለሳምንታት በመደበኛነት ከት/ቤት እንደሚቀሩ ያሳያል።

ጥናት ከማካሄዳችን በፊት ባሉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ በሁሉም የገጠር አካባቢዎች የሚገኙ በዕድሜ አነስተኛ በሆነው ቡድናችን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በአማካይ 15% (በከተሞች አካባቢ 6%) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት ቀርተዋል። የአይነታዊ ምርምር ውጤታችን የግብርናና የቤት ውስጥ ስራዎች አብዛኛውን ጊዜ ከትምህርት ለመቅረት ምክንያት መሆናቸውን

> ◗◗ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት ለማምጣት ወደ ቤታቸው ስንሄድ አንዳንድ እናቶች በኛም ላይ ድንጋይ የሚወረውሩብን ጊዜ አለ። የሚረዳቸው ሌላ ሰው ስለሌላቸው ልጃገረዶቹ እነሱን መርዳት እንዳለባቸው ይሰማቸዋል።
>
> (አንድ የት/ቤት ርዕሰ መምህር፣ ማህበረሰብ ሸ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ ኢትዮጵያ)

ያሳያል። ከማህበረሰብ ሸ (ምስራቅ ሃረርጌ) አንድ አስተማሪ እንዳብራራው፣ ‹‹ወላጆች የእርሻ ሥራ ለመስራት ወደ እርሻ ቦታ በሚሄዱበት ጊዜ ልጆች ከብቶችና ፍየሎችን ይጠብቃሉ። ከ2 ወይም ከ3 ወራት በኋላ ተመልሰው ይመጣሉ።›› ታዳጊዎች፣ በተለይም ወንዶቹ፣ እድሜያቸው ከፍ እያለ ሲመጣ ከትምህርት የሚቀሩባቸው ምክንያቶች ወቅታዊ የሆነ ከስራ ጋር በተያያዘ የሚያደርጉት ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ሁኔታ ነው። በማኅበረሰብ ሸ (ደቡብ ጎንደር) አንድ የትምህርት ባለሙያ፣ "ልጆች ብዙውን ጊዜ ሥራ ፍለጋ ወደ ሌሎች ቦታዎች ይሰደዳሉ፤ ወንዶቹ አብዛኛውን ጊዜ የሰሊጥ ሰብል በሚታረምበትና በሚሰበሰብበት የመኸር ወቅት በክፍያ ወደሚሰራባቸው መተማና ሁመራ እርሻ አካባቢዎች ይሄዳሉ›› በማለት አስረድቷል።

የመንግስት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በ2ኛ እርከን የመጀመሪያ ትምህርት ቤቶች ያለው የትምህርት ምዝገባ ምጣኔ በ1ኛ እርከን ካለው ምጣኔ በግምት ግማሽ ያህል ሲሆን፣ የመነሻ ምርምራችንም ያሳተፋቸው ታዳጊዎች ከትምህርት ቤት ማቋረጥ በሚጀምሩበት በተገቢው ጊዜ ነው። የአይነታዊ ምርምራችን የሚያመለክተው ለትምህርት ማቋረጥ የሚገፋፉ ምክንያቶች በከፍተኛ ሁኔታ በጾታና በእውድ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎች እንዳብራሩት፣ የቤተሰብ ችግር (የወላጅ ህመም እና ሞት እንዲሁም ፍቺ)፣ በትምህርት ቤት የሚያጋጥም ጥቃት፣ ያለ በቂ ትምህርት ከክፍል ወደ ክፍል የሚደረግ አስገዳጅ ዝውውር፣ ያልተሟላ የትምህርት ግብዓት (የመማሪያ ቁሳቁስ እጥረት እና በቂ የውሃ አቅርቦት ያለመኖር)፣ ለትምህርት ቤት ያለው ርቀት እና ታዳጊዎችን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ወጪዎች ሁሉ ሚና ይጫወታሉ። ወንዶችም ሆኑ ልጃገረዶች ከወላጆቻቸው ጋር በቤት ውስጥ ለመስራት አሊያም በክፍያ ስራ ገቢ ለማግኘት ትምህርት ያቋርጣሉ። እንዲሁም፣ ልጃገረዶች አንዳንድ ጊዜ ተገደው (በደቡብ ጎንደር እና በአፋር) ሌላ ጊዜ ደግሞ በራሳቸው ፍላጎት (በምሥራቅ ሐረርጌ በጣም የተለመደ ነው) ትዳር ለመያዝ ሲሉ ትምህርት ያቋርጣሉ።

ታዳጊዎች እያደጉ ሲመጡ መረጃዎችን ዘርዘር አድርጎ ማየቱ በጣም ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ፣ በደቡብ ጎንደር፣ በ11 ዓመታቸው ልጃገረዶች (96%) ከወንድ ልጆች (89%) ይልቅ ለትምህርት የሚገቡ ሲሆን በምስራቅ ሀረርጌ ደግሞ ወንዶች (85%) ከልጃገረዶች (70%) ይልቅ ወደ ትምህርት እንደሚገቡ ደርሰንበታል፡፡ በዞን 5 እንደሚታየው ደግሞ ወንዶች (29%) ከልጃገረዶች (18%) ይልቅ ብዙ ቀናት ከትምህርት ቤት ይቀራሉ። ተመሳሳይ ተቃርኖ በአይነታዊ ምርምራችንም ውስጥ በግልጽ ይታያል፤ ይህም በጾታ እና በትምህርት መካከል ያለው ግንኙነት በአንዳንድ አካባቢዎች የማይለዋወጥ ሲሆን፣ በሌሎቹ አካባቢዎች ደግሞ ተለዋዋጭ ነው።

የታዳጊዎች ደህንነት በኢትዮጵያ: በጾታ የተለዩ ችሎታዎች፣ እውዶችና የለውጥ ስትራቴጂዎች ፍተሻ

---

2 በታዳጊ ክልሎች ወደ ትምህርት የሚገቡ ተማሪዎች ቁጥር ከሀገር አቀፍ አማካይ ቁጥር ወደኋላ የቀረ ነው፤ ለምሳሌ በሶማሌና አፋር ያለው የቅበላ ምጣኔ የደቡብ ክልልና የጋምቤላ ክልሎችን ግማሽ ያህል ነው (Ministry of Education, 2018).

በደቡብ ጎንደር፣ ለምሳሌ፣ እያደገ የመጣው የወንዶች በክፍያ ስራ ላይ መሰማራት ልጃገረዶች የሚያጋጥሟቸው ባህላዊ ጉዳቶች የበለጠ መስተናገድ ይጀምራሉ። በሌላ በኩል፣ በምስራቅ ሐረርጌ፣ ወንዶች አሁንም በሁሉም መስፈርት ከልጃገረዶች በላይ ከፍተኛ ተጠቃሚ ናቸው። ይሁን እንጂ በዞን 5፣ ጥቂት ታዳጊዎች (ወንዶች ወይም ሴቶች) 2ኛ ክፍልን አልፈዋል።

የአይነታዊ ምርምራችን እንደሚያሳየው ታዳጊዎች፣ ጎልማሶች እና የትምህርት ባለሞያዎች የትምህርት ጥራት ወደኋላ የቀረው በአቅርቦት እጥረትና በመምህራን ስልጠና ላይ በቂ ትኩረት ባለመደረጉ መሆኑን ይስማማሉ። መምህራን፣ በተለይም በገጠር አካባቢ የሚገኙ፣ ብዙውን ጊዜ ተስፋ የቆረጡ እንደሆኑ ተናግረዋል፡ ፡ የመማሪያ ክፍሎች የተጨናነቁ ብቻ ሳይሆኑ መሰረታዊ የትምህርት መሳሪያ የሆኑት ዴስክና መጻሕፍት የሌላቸው ናቸው፤ ይህም የማንኛውንም ግለሰብ ትኩረት የሚገታ ነው። ደግሞም፣ መምህራን ብዙውን ጊዜ ‹ሥልጠና ባላገኙበት መስክ› ይመደባሉ (መምህር፣ ማህበረሰብ ረ፣ ደቡብ ጎንደር)። በማኅበረሰብ ሸ (ምስራቅ ሀረርጌ) ውስጥ አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጪ በበኩላቸው በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ያሉ የመማሪያ ክፍሎች በጣም የተጨናነቁ በመሆናቸው የተማሪዎቹ የትምህርት ውጤት ምንም ይሁን ምን ከክፍል ወደ ክፍል ማሳለፍ እንዳለባቸውና የማያልፉ ተማሪዎች እንዳይኖሩ ለመምህሮቹ ይነገራቸዋል ብለዋል።

## 1.5 ለትምህርት ሽግግር የሚደረግ ድጋፍ

በሀገር አቀፍ ደረጃ፣ ምንም እንኳን ዕድሜያቸው ከፍ ያለ ተማሪዎች ቁጥር ብዙ በመሆኑ አጠቃላይ የምዝገባ ምጣኔ በእጥፍ ያህል ቢጨምርም፣ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተጣራ ምዝገባ መጠን 25% እንዲሁም በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ 10% የሚሆኑት ብቻ ናቸው (MoE, 2018)። የመሠረታዊ ጥናታችን ያሳተፈው በዋነኝነት ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመሸጋገር ብዙ ዓመታት የወሰደባቸው ታዳጊዎችንና እና በከተሞች አካባቢ የሚኖሩ በዕድሜ ከፍ ያሉ ታዳጊዎች ሲሆኑ ግኝታችን የሁለተኛ ደረጃስ ትምህርት እንዳይቀጥሉ የሚገቱ በርካታ እንቅፋቶችን ለይቷል። የገጠር ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ ‹‹ከቤተሰቦቻቸው ርቀው መሄድ ስለሚኖርባቸው የትምህርት ቤት ርቀት ዋነኛው እንቅፋት ነው ። ይህም ማለት የምግብ፣ የጽህፈት መሳሪያዎች፣ የቤት ኪራይ እና ሌሎች ከፍተኛ ወጪዎች ይኖርባቸዋል።›› (መምህር፣ ማህበረሰብ ሰ፣ ደቡብ ጎንደር) ከፈተና የመውደቅ ከፍተኛ ምጣኔ፣ በተለይም በገጠር ትምህርት ቤቶች ለተማሩ ተማሪዎች፣ እና የገንዘብ እጥረት እንዲሁ ለበርካታ ታዳጊዎች ትምህርት እንዳይቀጥሉ አድርጓቸዋል። ለልጃገረዶች የበለጠ መሰናክሎችም አሉ። በታዳጊነት ዕድሜ አጋማሽ ላይ በጣም የተለመደ በሆነው ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ልጃገረዶች በአመዛኙ በትምህርት ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸው እና የቤት ስራቸውን ለመስራት በቂ ጊዜ ባለማግኘታቸው በፈተናዎቻቸው ይወድቃሉ፡ ፡በተጨማሪም ወላጆች ለልጆቻቸው ደህንነት ስለሚሰጉ የሴቶች ልጆቻቸውን እንቅስቃሴ ይበልጥ ይገድባሉ። በማህበረሰብ መ (ደቡብ ጎንደር) ውስጥ የሴቶች ማህበር ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንደገለጹት፣ ‹‹ወላጆች ዕድሜያቸው ከፍ ያሉትን ሴት ልጆቻቸውን ጥቃት ሊደርስባቸው ወይም በድንገት ነፍሰ ጡር ሊሆኑ ስለሚችሉ ወደ ትምህርት ቤት መላክ አይፈልጉም››።

## 1.6 የለውጥ ስትራቴጂዎች

ጥናታችን የታዳጊዎችን የትምህርት ተደራሽነትን ለማሻሻል የሚረዱ በርከት ያሉ የለውጥ ስትራቴጂዎችን ለይቷል። የመጀመሪያ



## መምህራን ሁሉንም ተማሪዎች ከአንድ የክፍል ደረጃ ወደ ሌላ እንዲያሳልፉ እና ያላለፉ ተማሪዎችን ሪፖርት እንዳያደርጉ ታዝዘዋል ፡፡

**(አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጭ፣ ማህበረሰብ ሸ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ ኢትዮጵያ)**

ደረጃ ትምህርትን መሠረተ ልማት ለማጎልበት ከሚደረገው ጥረት ውጪ፣ ስትራቴጂዎቹ ብዙውን ጊዜ የሚያተኩሩት የወላጆችን እና ታዳጊዎችን ስለ ትምህርት አስፈላጊነት ግንዛቤ ለማሳደግ ነው፡፡ ደግሞም፣ በአንዳንድ ማህበረሰቦች የሴቶች ክለቦች እና የሴቶች ማጠናከሪያ ትምህርቶች ልጃገረዶች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ እየረዱ ሲሆን፣ በሌሎቹ ደግሞ መምህራን እና/ወይም የቀበሌ ባለስልጣናት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በሚቀሩ ጊዜ ወደየተማሪዎች መኖሪያ ቤት እየሄዱ እንዲያመጧቸው ተመድበዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በምስራቅ ሀረርጌ ማህበረሰብ ቀ አንድ መምህር እንዳለው፣ ‹‹ከመደበኛ የማስተማር ስራ በተጨማሪ መምህራን ወደ ተማሪዎች መኖሪያ ቤት እየሄዱ ወደ ትምህርት ቤት እንዲያመጧቸው ተመድበዋል … በየቀኑ ከሰዓት በኋላ መምህራን ወደ ተማሪዎች መኖሪያ ቤት እየሄዱ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ ያደርጋሉ፡፡›› በግለሰብ መምህራን፣ በበለፀጉ ቤተሰቦች እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ እንዲሁም የትምህርት ቤት ምገባ ታዳጊዎች ትምህርታቸውን እንዲማሩ በመርዳት ረገድ አስፈላጊ እንደነበሩ በአንዳንድ ምላሽ ሰጭዎች ሪፖርት ተደርጓል፡፡ ምንም እንኳን የቀድሞው ሙሉ በሙሉ ጊዜያዊ ቢሆንም፣ የኋለኛው ደግሞ ተቋርጧል፡፡

# 2 አካላዊ ምሉዕነትና ከጥቃት ነጻ መሆን

## 2.1 መግቢያ

አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ታዳጊዎች በህይወታቸው ቢያንስ አንድ ዕድሜ-ተኮር ወይም ጾታ-ተኮር ጥቃት ይደርስባቸዋል፡ ፡ በፓንክረስትና ጓደኞቹ (Pankhurst et al., 2016) በወጣቶች የህይወት ዘመን የአይነታዊ ጥናት ናሙና ውስጥ 90% የሚሆኑት ጥቃት ደርሶባቸዋል። አካላዊ ጥቃት (በተለይም በትምህርት ቤት ውስጥ የሚፈጸም አካላዊ ቅጣት) በጣም የተስፋፋ ሲሆን ወንዶች (በተለይም ትናንሽ ልጆች) በጣም የተጋለጡ ናቸው (Pankhurst et al., 2016; Save the Children, 2011)። ወሲባዊ እና ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት - እንደ ያለዕድሜ ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት / ብልት መቆረጥ የመሳሰሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ እንዲሁም ትንኮሳ እና አስገድዶ መድፈርን ጨምሮ - በስፋት ያታያል (Jones et al., 2014a; 2014b; 2016a; 2016b; 2016c; 2017; Camfield and Tafere, 2011; Pankhurst et al., 2018)፡ ፡ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ምንም እንኳን ሥር የሰደደ አሰራር ቢሆንም፣ በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ ክልሎች እና ታናናሽ ሴት ልጆች ላይ ጉልህ መቀነስ እያሳየ ነው። የቅርብ ጊዜ የኢትዮጵያ የስነ ሕዝብና የጤና ጥናት መረጃ እንደሚያመለክተው 40% የሚሆኑት ከ 20 እስከ 24 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሴቶች ያገቡት ዕድሜያቸው ከ 18 በታች እያሉ ነው። እንዲሁም 6 በመቶ የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከ15-19 የሆኑ ልጃገረዶች (ከ 20 እስከ 24 ዓመት ከሚሆኑት 14% ወጣት ሴቶች ጋር ሲነጻጸር) ያገቡት ከ15 ዓመት በታች እያሉ ነው (CSA and ICF, 2017)።

## 2.2 ዕድሜ-ተኮር ጥቃት

በተጠኑ ጥናቶች ላይ በስፋት እንደተገለጸው፣ አብዛኞቹ ታዳጊዎች የአካላዊ ቅጣት የሚደርስባቸው በወላጆቻቸውና በአስተማሪዎቻቸው መሆኑን ጥናታችን ያሳያል። በኢትዮጵያ ውስጥ በሕፃናትና ታዳጊዎች ላይ በቤት ውስጥ የሚፈጸም ጥቃት የተለመደ እንደሆነ ማስረጃዎች ያመለክታሉ (Pankhurst et al., 2018; Jones et al., 2017; Save the Children, 2011)። የዚህም ምክንያቱ ባብዛኛው ‹‹ወላጆች ለተሻለ የልጅ አስተዳደግ አካላዊ ቅጣት አስፈላጊ ነው የሚለውን ባህላዊ አስተሳሰቦችንና እምነቶችን ስለሚጋሩ›› ነው (Wonde et al., 2014: 21)።የዳሰሳ ጥያቄዎቻችንን ከመለሱልን ታዳጊዎች መካከል ወደ 70 በመቶው የሚሆኑት ምንም ዓይነት ወሳኝ የጾታ ልዩነት ሳይኖር በቤት ውስጥ ጥቃት እንዳጋጠማቸው ወይም እንዳዩ ተናግረዋል።

በአስተማሪዎች የሚፈጸም አካላዊ ጥቃትን በተመለከተ ቀደም ሲል የተደረጉት ጥናቶች እንደሚያሳዩት አካላዊ ቅጣቶች በመላው ኢትዮጵያ ተስፋፍተው ይገኛሉ። እነዚህ አካላዊ ቅጣቶች የሚፈጸሙት ልጆች ያልተገባ ባህሪ ሲያሳዩ ብቻ ሳይሆን ብዙውን ጊዜ ከቁጥጥራቸው በላይ በሆኑ ጉዳዮች ምክንያታቸው ብዙውን ጊዜ የቤተሰብ ድህነት ወይም በቤት ውስጥ የሚጣልባቸው የሥራ ጫና (ለምሳሌ ዘግይቶ መምጣት ወይም የቤት ስራ አለመስራት በመሳሰሉት) ምክንያት ነው (Jones et al., 2015; 2016a; 2016b; 2017; Save the Children, 2011; Pankhurst et al., 2016, 2018)። በጎጅ ግኝቶች እንደተረጋገጠው 72% ከሚሆኑት የጥናታችን ተሳታፊዎች ወንዶች (78%) ከሴቶች (66%) ይልቅ በትምህርት ቤት ውስጥ ጥቃት እንደደረሰባቸው ገልጸዋል። የአይነታዊ ምርምራችን የሚያመለክተውም በተለይ ወንዶች (እምብዛም የማይታዘዙ ስለሆኑ)፣ ይህ ቅጣት በጣም ከባድ ሊሆን የሚችል መሆኑን ነው። ልጃገረዶች ተገቢ ያልሆነ ምግብን ማዘጋጀትን ወይም ከወንዶች ጋር በአደባባይ መታየትን የመሳሰሉ የስርዓተ ጾታ ደንቦችን በመጣስ እንዲሁም ከነሱ ቁጥጥር ውጪ በሆኑ በቤት ውስጥ እና በእንክብካቤ ስራ ሃላፊነቶች ምክንያት ዘግይተው መግባትን ጨምሮ ቅጣት ይደርስባቸዋል። ወንዶች ልጆች እነዚህን የሥርዓተ-ጾታ ልዩነቶች ለይተው በማወቃቸው፣ መልካም ባህሪ ባለማሳየታቸው ከሴት ልጆች ይልቅ የበለጠ እንደሚቀጡ ተስማምተዋል። አንድ የ 10 ዓመት ልጅ ከማኅበረሰብ ተ (ምስራቅ ሀረርጌ) እንደተናገረው፣ “እርሱ [መምህሩ] ክፍል ውስጥ ስለማይረብሹ [ልጃገረዶቹን] አይደበደባቸውም”።

የአይነታዊ ምርምራችን በዋነኝነት ወንዶች በሌሎች ወንዶች ላይ የሚፈጸመው የእኩያ ጥቃት በጣም የተስፋፋና በአብዛኛው ወንድነታቸውን ለማሳየት ካለው ፍላጎት ጋር የተዛመደ መሆኑን ያሳያል። በኢትዮጵያ ስላለው የወንዳወንድነት እና የአመጸኝነት ልምዶች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያጎላ ነባር ሥነ-ጽሑፍን (Heinonen, 2011; Pankhurst et al., 2018; Pells and Morrow, 2018) መሠረት በማድረግ የእኛ ግኝቶች ወጣት ወንዶች በግጦሽ መሬት እንደሚጣሉ እና ጥንካሬያቸውን እንደሚያረጋግጡ፣ ትልልቆቹ ወንዶች ደግሞ በሴቶችና ለበቀል እንደሚጣሉ ያሳያሉ፡ ፡ አንድ የ12 ዓመት ታዳጊ ከማህበረሰብ መ (ደቡብ ጎንደር) በድብድብ ብቃቱ በእኩዮቹ እንደሚወደድና እንደሚጠላ በኩራት ተናግሯል: ‹‹እነሱ [ሌሎች ልጆች] ይወዱኛል ደግሞም ይፈሩኛል፤ ምክንያቱም ከብቶቻቸውን በሰብላችን ላይ ሲለቁ አደበድባቸዋለሁ፤ አሸንፋቸዋለሁ።››

## 2.3 ወሲባዊና ጾታ-ተኮር ጥቃት

ወሲባዊ እና ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ተስፋፍተው እንደሚገኙ የሚታወቅ ቢሆንም (CSA and ICF, 2017)፣ በታዳጊነት ዕድሜ ልምምዶች ላይ ያለው የእውቀት መሠረት በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ ውስን ነው፤ ያለው መረጃም በዕድሜ ከፍ ያሉ ለወጣቶች ላይ የበለጠ ያተኩራል (Jones et al., 2014a;

> **በአካባቢያችን ልጃገረዶች እንዲያገቡ ይገደዳሉ። ደፈራት፤ ከዚያም አገባት።**
>
> ((እንዲት ወጣት ታዳጊ ልጃገረድ፣ ማህበረሰብ ሐ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ኢትዮጵያ)

2014b; 2016b; 2017; Erulkar and Mekbib, 2007; Erulkar and Ferede, 2009)። የእኛ የጌጅ ግኝቶች እንደሚያመለክቱት በሴት ልጆች ላይ በሚደርሱ በቃላት ጥቃት፣ በአካላዊ ጥቃትና በጾታዊ ጥቃት መካከል ያለው ትስስር ውስብስብ እና ለመለያየት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ልጃገረዶች በወጣትነታቸው ብዙውን ጊዜ በወሲባዊ ትንኮሳ ይጠቃሉ፣ ይደበደባሉ፣ እንዲሁም ሰውነታቸው እያደገ ሲሄድ ለጾታዊ ጥቃት ይጋለጣሉ። በድሬዳዋ የምትገኝ በዕድሜ ከፍ ያለች ታዳጊ ልጃገረድ እንዳጠቃለለችው፣ ‹‹ዕድሜያችን እየጨመረ ሲመጣ ሁላችንም እንጸጸታለን።›› ምንም እንኳን በጥናታችን ውስጥ ያሉ ጥቂት ልጃገረዶች ከወጣት ወንዶች ከሚቃጣባቸው ወሲባዊ ትንኮሳ እና አካላዊ ጥቃት አንዳቸው ሌላውን ለመጠበቅ ፈቃደኞች ቢሆኑም፣ ልጃገረዶች በእድሜ ትላልቅ ከሆኑ ወንዶች ለሚፈጸምባቸው ወሲባዊ ጥቃት የመከላከል አቅማቸው አናሳ ይመስላል። ይኸውም በአብዛኛው ልጃገረዶች በሁሉም የግብረ-ሥጋዊ እንቅስቃሴ ውስጥ “ፈቃደኛ” ተሳታፊ እንደሆኑ አድርገው በሚመለከቱት የስርዓተ ጾታ ህጎች ምክንያት ጥቃት እንደተፈጸመባቸው አድርገው ተወቃሽ ያደርጓቸዋል። በደቡብ ጎንደር ልጃገረዶች ተገደው ቢደፈሩ እና ቤተሰቦቻቸው ይህን ቢያውቁ ሊከሰት የሚችለው እርግዝና በጋብቻ የተፈጠረ እንደሆነ እንዲታሰብ በሚል ተጋብተው እንዲኖሩ የሚደረግ መሆኑን ብዙዎቹ ልጃገረዶች አስረድተዋል። በማህበረሰብ ሐ (ደቡብ ጎንደር) ወጣት ታዳጊ ልጃገረድ እንዳብራራችው፣ ‹‹በአካባቢያችን ልጃገረዶች እንዲያገቡ ይገደዳሉ። ደፈራት፤ ከዚያም አገባት።›› ምንም እንኳን ከሴት ጓደኞቻቸው ያነሰ ተጋላጭነት ቢኖራቸውም፣ በምርምር ጣቢያዎቻችን ውስጥ ያሉ አንዳንድ ወንዶች ልጆችም ለመናገር አስነዋሪ ለሆነ ወሲባዊ ጥቃት እንደተጋለጡ ሪፖርት አድርገዋል።

## 2.4 የሴት ልጅ ብልት መቁረጥ

የኢትዮጵያ ሥነ-ሕዝብ እና የጤና ጥናት (DHS, 2016) እንዳመለከተው የሴት ልጅ ብልት የመቁረጥ መጠን፣ አይነት እና ከሚቆረጥበት ዕድሜ ጋር በተያያዘ በየክልሎች ከፍተኛ ልዩነት አለ (CSA and ICF, 2017)። የእኛ ግኝት የሚያረጋግጠው የሴት ልጅ ብልት መቁረጥ በተለያየ የዕድሜ ደረጃ (ከጨቅላ ህጻንነት ዕድሜያቸው እስከ ቅድመ ታዳጊ ዕድሜ ድረስ ባሉት) ሴቶች ላይ የሚከናወን ጥልቅ ስር የሰደደ የባህል ልምምድ መሆኑን ሲሆን፣ ዓይነቱም በየክልሎች ይለያያል (ለምሳሌ፣ ከመለስተኛ ደረጃ ወይም ‹ሱና› እስከ ከፍተኛ ደረጃ ሁለትና ሶስት ይደርሳል።) (የዓለም ጤና

> **ሴቶች ልጆቻቸው ራሳቸው እንዲገረዙ ቤተሰቦቻቸውን ይለምኗቸዋል።**
>
> (የ10 ዓመት ልጃገረድ፣ ማህበረሰብ በ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ ኢትዮጵያ)

ድርጅት (WHO, 2018) ን ይመልከቱ)። በደቡብ ጎንደር ያካሄድነው የአይነታዊ ምርምር ስራችን የሚያሳየው ድርጊቱ በጨቅላ ህጻንነት ጊዜ የሚተገበርበት እምብዛም ያልተለመደ እየሆነ መምጣቱን ሲሆን ፣ ምክንያቱም ከዚህ ጋር ተያይዞ ስለሚፈጠሩ በጤና ላይ ስለሚያስከትለው ጉዳት ግንዛቤ እየጨመረ በመምጣቱ ነው፡ ፡ በምስራቅ ሐረርጌ፣ ብልት መቆረጥ ብዙውን ጊዜ በቅድመ ታዳጊነት ዕድሜ የሚከናወን እና የበለጠ ተስፋፍቶ ያለው ደረጃ II ወይም ደረጃ III ሲሆን፣ ልጃገረዶች ከጓደኞቻቸው እኩል ለመሆንና ባህላዊ ደንቦችን አክብረው ለመገኘት ሲሉ እራሳቸው መቆረጥ እንደሚሹ አስተውለናል። ከማህበረሰብ በ የ10 አመት ልጃገረድ እንዳለችው፣ ‹‹ሴቶች ልጆች እራሳቸው እንዲገረዙ ቤተሰቦቻቸውን ይለምኗቸዋል››። ድርጊቱ በተስፋፋበትና እንደ ማህበረሰብ ለ የአካባቢው መሪ አባባል ‹‹ማህበረሰቡም ሊተወው ፈቃደኛ ባልሆነበት›› በዞን 5፣ በጤና ላይ ስለሚያስከትለው ጉዳት ግንዛቤ እየጨመረ በመምጣቱ የብልት መቁረጥ ዓይነቱ ቀስ በቀስ ወደ ‹‹ሱና›› መጥቷል።

## 2.5 ያለዕድሜ ጋብቻ

በኢትዮጵያያለዕድሜ ጋብቻ ሁኔታም ይለያያል። ያለዕድሜ ጋብቻ ምጣኔውና ጋብቻ የሚፈጸምበት ዕድሜ በአንድ ዞን ውስጥ በሚገኙ ወረዳዎችና ቀበሌዎች እንኳን ሳይቀር (Jones et al., 2016a; 2016b) በየክልሎች በከፍተኛ ሁኔታ ልዩነትይታያል። ያለዕድሜ ጋብቻ የልጃገረዶችን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመቆጣጠር እና ባህላዊ ባህልን ለመጠበቅ በሚደረጉ ሙከራዎች ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ልምምዱ እንደ ጋብቻው ሁኔታ፣ ጋብቻ የሚፈጸምበት ዕድሜ እና በትዳር ጓደኛ ምርጫ በሁሉም አካባቢዎች በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚለያይ የጌጅ ጥናታችን ያሳያል። በደቡብ ጎንደር፣ ጋብቻ የሚፈጸምበት ዕድሜ ከፍ እያለ የመጣ ሲሆን ያለዕድሜ ጋብቻ የመከሰትም ሁኔታ እየቀነሰ ይገኛል። ይህ ደግሞ ግብርና አስተማማኝ የኑሮ ዋስትና የማይሰጥ መሆኑን ለትምህርት ያለው ቁርጠኝነትና ግንዛቤ እያደገ በመምጣቱ ነው። በተጨማሪም፣ በአከባቢው የሚገኙት አብዛኛዎቹ ጋብቻዎች አሁን ድረስ በወላጆች የተመቻቹና ትናንሽ ልጃገረዶች እንዲያገቡ የሚገደዱ ሲሆን፣ ምንም እንኳን ውስን ቢሆንም፣ ልጃገረዶች ማንን እንደሚያገቡ አስተያየት እንዲሰጡ የሚያስችል ዕድል) አለ። ከማህበረሰብ ሐ መካከል ያለች ታዳጊ እንዳለችው፣ ‹‹ያለእነሱ ፈቃድ እንዴት ማግባት እችላለሁ? ቤተሰቤ ማግባት እንደምፈልግ ጠየቁኝ፣ አዎ አልኳቸው እናም ለሱ አጋቡኝ። እሱ የአካባቢያችን ሰው እንደ ሆነ አውቃለሁ፣ ግን በደንብ አላውቀውም።›› በሌላ በኩል በምስራቅ ሐረርጌ በአንዳንድ አካባቢዎች ያሉ ልጃገረዶች ከወላጆቻቸው ፍላጎት ውጪ በሕፃንነታቸው ለማግባት 'እየመረጡ' ሲሆን ጎልማሶች በጋብቻ ላይ ያለው ዕድሜ እየቀነሰ መሆኑን ይገልጻሉ። አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን ከትምህርት ቤት እንዲያወጡ የሚያደርጋቸው ድርቁ ሊሆን እንደሚችል ያምናሉ። ከማህበረሰብ ተ አንድ አባት “ሴት ልጆች ያለ ስራ ከመቀመጥ ይልቅ ጋብቻን ይመርጣሉ” ብለዋል። ሌሎች ደግሞ ባህላዊ የሽጎዬ ጭፈራ በተለይም የጋብቻ ደላሎች የሚሳተፉበት በተለየ መልክ የልጆችን ጋብቻ የሚያበረታታ ባህላዊ መድረክ ሆኗል ብለው ያምናሉ። ልጃገረዶች ራሳቸው አንዳንድ ጊዜ



የአካል ጉዳተኛ ታዳጊ ልጃገረድ በእብናት፣ አማራ
© ናታሊ በርትራምስ / ጌጅ 2019

የእኩዮችን ተጽዕኖ ተጠያቂ ያደርጋሉ። ከማህበረሰብ በ አንድ የ15 ዓመት ታዳጊ፣ ‹‹እነሱ [ጓደኞቼን ማለቴ ነው] ስላገቡ እኔም አገባሁ፡ ፡›› በማለት ገልጻለች።

በዞን 5 (አፋር) ውስጥ የለውጥ ምልክቶች ውስን ናቸው። ምክንያቱም በዋናነት በእነሱ የአብሱማ ጋብቻ ስርዓት ምክንያት ጋብቻ የሚፈጸመው ከእናቶች ወንድም ልጆች ጋር ስለሆነ ልጃገረዶች ማንንና መቼ እንደሚያገቡ የመምረጥ መብት የላቸውም። ጎልማሶችና አንዳንድ ታዳጊዎች የአብሱማ ጋብቻ ቢቀር፣ አንድ ሰው ከማህበረሰብ እንዳለው፣ ‹‹የትውልዳችን ሀረጋችን ይቋረጣል›› ብለው ስለሚያምኑ ለዚህ አይነቱ ጋብቻ ተቆርቋሪ ቢሆኑም ልጃገረዶች ግን የተውት መሆናቸውን አይተናል፡ ፡ ከማህበረሰብ ለ ውስጥ ያለች አንዲት ልጃገረድ፣ ‹‹በሕይወት እስካለን ድረስ የአጎታችንን ልጅ ማግባት ማቆም አለብን›› ብላለች፡ ፡ በእርግጥ ምላሽ ሰጭዎች እራስን ማጥፋት መሞከር ከችግሩ መውጫ መፍትሄ አለመሆኑን ተናግረዋል። በማኅበረሰ ሀ ውስጥ ያለ አንድ በዕድሜ ከፍ ያለ ታዳጊ እንዳስረዳው፣ ‹‹ተገዳ ያገባችውን ሰው ስላልወደደችው መርዝ የጠጣች አንዲት ልጃገረድ የአብሱማ ጋብቻውን አክብራ ትዳሯን አጥብቃ እንድትይዝ በጎሳ መሪዎች ተነግሯታል።››

## እነሱ [ጓደኞቼን ማለቴ ነው] ስላገቡ እኔም አገባሁ፡፡

((አንዲት የ15 ዓመት ሴት ታዳጊ፣ ማህበረሰብ በ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ ኢትዮጵያ)

## 2.6 የለውጥ ስትራቴጂዎች

በታዳጊዎች ላይ የሚፈጸሙ በእድሜ እና በጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃትን ለማስቆም የሚደረጉ ጥረቶች እንደየጥቃቱ አይነትና እንደ አከባቢው ሁኔታ በጣም ያልተመጣጠኑ ናቸው። በአጠቃላይ፣ ታዳጊዎች በቤት እና በትምህርት ቤት የሚጥማቸውን የአካል ቅጣቶች ለመቀነስ የተደረገው ጥረት በጣም ጥቂት ነው። አንዳንድ የስነ-ዜጋ መምህራን ለተማሪዎች ስለ ልጆች መብቶች ስምምነቶችና ልጆች ከጥቃት ነፃ የመሆን መብት ቢናገሩም፣ እነዚሁ አስተማሪዎች እራሳቸው ጥቃት እያደረሱ መሆናቸውን ታዳጊዎቹ ታዝበዋል። ወሲባዊ እና ጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃትን ለማስቆም የሚደረጉ ጥረቶች አሰልቺ ቢሆኑም ግን የበለጠ ተስፋ ሰጪ ናቸው፡ ፡ ለምሳሌ፣ በባቱ (የምስራቅ ሸዋ) ሴት አቃቤ ህግ እንደገለጸችው ፅህፈት ቤቷ 'አስገድዶ መድፈር ጉዳዮችን የሚመለከት' ብቻ ሳይሆን ከሴቶችና ከልጆች ጉዳዮች ጋር በመተባበርም ልጃገረዶችና ሴቶች ጥቃቶችን ሪፖርት እንዲያደርጉ በማበረታታት የጥቃት ሰለባ እንዳይሆኑ ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል። ምንም እንኳን የህግ አቀራረቦች አንዳንድ ጊዜ ተፈጻሚ ቢሆኑም፣ ያለዕድሜ ጋብቻን (እና በትንሹም ቢሆን፣ የሴት ልጅ ግርዛትን) ለመቀነስ የተደረጉ ጥረቶች፣ በተለይ በአማራ ክልል ላቅ ያለ ሲሆን፣ ለወላጆችና ለሴቶች ልጆች ግንዛቤን ለማሳደግ በአብዛኛው ለወላጆች እና ለሴቶች ልጆች ግንዛቤ በመፍጠር ላይ ያተኮረ ነው። ጥናታችን ያለዕድሜ ጋብቻ በሚፈጸምባቸው ቦታዎች ላይ ማተኮር አስፈላጊ መሆኑን እና የማህበራዊ ድንጋጌዎችን ያልተመጣጠነና ውስብስብ ተፈጥሮአዊ ባህሪ የመለወጥ ሂደቶችን የሚመሩ ስልቶችን ማጎልበት ወሳኝ መሆኑን ያሳያል።

# 3 ጤንነት፣ አመጋገብ፣ እና የስነተዋልዶ ጤና

## 3.1 አመጋገብ

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በህብረተሰቡ ደረጃ መሰረታዊ የመከላከያ የጤና አገልግሎት በሚሰጡ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የምትታወቅ ብትሆንም፣ ታዳጊዎች ስለነዚህ የጤና አገልግሎቶች ያላቸው ተደራሽነት እና ልምዶች እምብዛም የምናውቀው ነገር የለም። በታዳጊዎች የአካላዊ ጤንነት ላይ የሚገኘው መረጃ በዋነኝነት የሚያተኩረው በተመጣጠነ ምግብ እና ዕድሜያቸው ከ 15 ዓመት በላይ ለሆኑት የወሲባዊ እና የስነተዋልዶ ጤና ባህርያት ነው። ይህ ጠባብ ትኩረት በዋነኝነት ያለዕድሜ ጋብቻ ከሚጋለጡ ታዳጊ ልጃገረዶች የስነተዋልዶ ጤና ፍላጎቶች ከሚሰነዘሩ ስጋቶች የመነጨ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ከአንድ አራተኛ በላይ የሚሆኑት ዕድሜያቸው 19 ዓመት ሲሆናቸው ቀድሞውኑ እርጉዝ ወይም እናቶች ሆነዋል (CSA and ICF, 2017)።

## 3.2 አጠቃላይ ጤንነት

የወጣት ታዳጊዎች አጠቃላይ የጤና ፍላጎቶች እንዲሁም የሁሉም ታዳጊዎች ሰፊ የጤና ተጋላጭነት በጥናታዊ ጽሑፎች ውስጥ አልተመላከቱም (Patton et al., 2012)። መሠረታዊ ጥናታችን እንደሚያሳየው 90% የሚሆኑት ታዳጊዎች ጤንነታቸው 'ጥሩ' እንደሆነ ሪፖርት ቢያደርጉም ከድህነት ጋር የተያያዘ በሽታ ግን አሁንም የተለመደ ነው። በታዳጊዎች ሪፖርት ከተደረጉት የጤና እክሎች መካከል አንዳንዶቹ የሚመጡት በንጽህና ጉድለት ነው። ለምሳሌ ከማህበረሰብ ረ (ደቡብ ጎንደር) አንድ የ 12 ዓመት ወጣት እንዲህ ብሏል፣ ‹‹በቅርቡ ሆዴን አሞኝ ነበር… የጤና ባለሙያው ህመሙ በተበከለ ውሃ ምክንያት የመጣ እንደሆነና ውሃውን ከአፈላሁ በኋላ ብቻ እንድጠቀም ነገሩኝ።››

አዋቂዎች ታዳጊዎች ስለሚገጥሟቸው የረጅም ጊዜ የጤና ችግሮች ይናገራሉ። በወንዶች ልጆች ሱስ የሚያስይዙ በተለይም አልኮልን እና ጫት መጠቀም እየጨመረ የመጣው ችግር (Jones et al., 2017) በተመለከተ፣ በድሬዳዋ አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጭ እንዳስታወቀት፣ “በአሁኑ ጊዜ የሱሰኝነት ባህሪ እየጨመረና በታዳጊዎቻችች ዘንድ የተለመደ እየሆነ መጥቷል። በእውነቱ ችግሩ በጣም አሳሳቢና ለሀገርም ትልቅ ስጋት ሆኗል። ወንዶች ልጆች ከልጃገረዶች ይልቅ ለችግሩ እጅግ በጣም የተጋለጡ ናቸው፡፡ ይኸውም ለልጃገረዶች አልኮል መጠጣት ወይም ጫት መቃም በማህበረሰቡ ተቀባይነት ስለሌለው እምብዛም አይጠቀሙም።

በጥናታችን መሠረት የተለያዩ ታዳጊ ቡድኖች እጅግ በጣም የተለያዩ የጤና ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። ለምሳሌ በከተሞች አካባቢ ትራፊክ እና ከሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳቶች በጣም የተለመዱ ናቸው። በምስራቅ ሐረርጌ የአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ የወባ በሽታ እያስከተለ መሆኑን ጎልማሶች/አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡ ባጠቃላይ፣ የጤና እክል ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር በአዋቂዎች ዘንድ ስጋት አለ። ይኸውም በአንድ በኩል የሴት ልጆች የታመሙትን የመንከባከቡ ኃላፊነት ከፍተኛ ስለሆነ ነው።

አንዳንድ ታዳጊዎች ለተለያዩ ሕመሞች እና ጉዳቶች የጤና እንክብካቤ መፈለጋቸውን የሚገልጹ ቢሆንም፣ ዘላቂ የአካል ጉዳቶች ወቅታዊ የጤና እንክብካቤ ውስን በመሆናቸው ምክንያት እንደሚከሰቱ አይነታዊ ምርምራችን ያመላክታል። ለምሳሌ፣ በርካታ ታዳጊ መልስ ሰጪዎች ሊከላከሉትና ሊታከም በሚችል የትራኮማ ኢንፌክሽን ምክንያት አይነስውር ሆነዋል።

## 3.3 አመጋገብ

የታዳጊዎች የአመጋገብ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን የሚያሳይ ማስረጃ አለ (Pankhurst et al., 2018) – ምንም እንኳን ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች ልጆች በጣም አነስተኛ ቢሆንም (Brown, 2012)። የመጠናዊ ምርምራችን እንደሚያሳየው በጊጅ ናሙና ውስጥ ያለው አማካይ ታዳጊ በመጠኑ የምግብ ዋስትና በሌለው ቤተሰብ ውስጥ እንደሚኖር እና በአይነታዊ መረጃችን መሠረትም ከመጠኑ ይልቅ የምግብ ጥራቱ ዝቅተኛ መሆኑን ነው። ሆኖም ግን በገጠር አካባቢዎች በተለይም በምስራቅ ሐረርጌ በቅርቡ ከተከሰተው ድርቅ አኳያ፣ ታዳጊዎች የተመጣጠነ ምግብ ያለማግኘት፣ ለአንዳንዶቹም ያለ ምግብ መዋል ያልተለመደ ነገር አይደለም። በገጠር አካባቢዎች የታዳጊዎች የረጅም ጊዜ ደካማ የአመጋገብ ስርዓት በሰውነታቸው ክብደትና ቁመት ልኬት ከዕድሜያቸው አንጻር በግልጽ የሚታይ ሲሆን በከተማ ከሚኖሩ እኩዮቻቸው በጣም የከፋ ነው።

ልጃገረዶች በተለይ ለከባድ የአመጋገብ ስርዓት ተጋላጭ መሆናቸውን ጥቂት ማስረጃዎችን አግኝተናል። ከእድሜያቸው አንጻር የቁመት ልኬታቸው ከወንዶች ያነሰ ነው። አንዳንድ ቁልፍ

> **ባሁኑ ወቅት፣ የታዳጊ ወጣቶች የሱሰኝነት ባህሪ እየጨመረና የተለመደ እየሆነ መጥቷል፡፡ ችግሩ በጣም አሳሳቢና ለሀገርም ትልቅ ስጋት ሆኗል።**
>
> (አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጪ፣ ድሬዳዋ፣ ኢትዮጵያ)

> **በዚህ አካባቢ ያሉ ወላጆች፣ በተለይ ገንቢ ምግብ ከመስጠት አንጻር፣ ለወንዶች ልጆቻቸው ቅድሚያ ይሰጣሉ።**
>
> (አንድ የጤና መኮንን፣ ደብረ ታቦር፣ ደቡብ ጎንደር፣ ኢትዮጵያ)



የድሬዳዋ ልጃገረድ © ናታሊ በርትራምስ / ጌጅ 2019

መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት የጾታ መድሎ በሚያደርጉ ማህበራዊ ድንጋጌዎችና ልማዶች ምክንያት ወላጆች ለወንዶች ልጆች የተሻሉ ምግቦችን በመስጠት ቅድሚያ ይሰጧቸዋል። በደብረ ታቦር (በደቡብ ጎንደር) አንድ የጤና መኮንን እንዳብራሩት፣ “በዚህ አካባቢ ያሉ ወላጆች፣ በተለይ ገንቢ ምግብ ከመስጠት አንጻር፣ ለወንዶች ልጆቻቸው ቅድሚያ ይሰጣሉ››።

## 3.4 አፍላ ወጣትነትና የወርአበባ

በትምህርት ቤት የሚሰጥ የጤና ትምህርት ተደራሽነት የተደባለቀ ይመስላል። የትምህርት ሚኒስቴር (MoE, 2018) ሪፖርት እንዳደረገው 80 በመቶው የሀገሪቱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የጤና ትምህርትን በሥርዓተ ትምህርታቸው ያካተቱ ቢሆንም፣ ጆንስና ጓደኞቹ (Jones et al., 2017) እንዳረጋገጡት፣ ልጃገረዶች ብዙውን ጊዜ ስለ አፍላ ወጣትነት በቂ ትምህርት ስለማያገኙ ለወር አበባ ዝግጁ አልነበሩም (በተጨማሪ Sommer et al., 2015; Blake et al., 2018 ይመልከቱ)። በተመሳሳይ መንገድ፣ የመሠረታዊ ጥናታችን የሚያሳየው ወጣት ታዳጊዎች፣ በተለይም በገጠር ያሉ፣ ስለ አፍላ ወጣትነት ወቅታዊ መረጃ የማግኘት ውስንነት ያለባቸው ሲሆን፣ የመረጃ ምንጭ ያላቸው 52% የሚሆኑት ብቻ መሆናቸውን ነው። የሚያገኙትም መረጃ ጠቅለል ያለ እንጂ ተግባራዊ የሚሆን እንዳልሆነ የአይነታዊ የምርምር ሥራችን ያሳያል። ጥቂት በዕድሜ አነስ ያሉ ታዳጊዎች፣ በተለይ በከተሞች አካባቢ የሚገኙ፣ ብቻ አፍላ ወጣትነት ማለት‹‹ለወንዶች ጺም ማብቀል፣ የድምጽ መጎርነን፣ እና ለሴቶችደግሞ የወርአበባ ማየትና ብብት አካባቢ ጸጉር ማብቀል›› (የ11 ዓመቷ ወጣት ከደብረ ታቦር፣ ደቡብ ጎንደር) እንደሆነ መናገር ችለዋል።

በተለይ ስለወር አበባ ያላቸው ግንዛቤ ውስን ነው። ከወር አበባ ጋር የተያያዙ ነገሮች ለሴቶች ከፍተኛ የጭንቀት ምንጭ ናቸው፤ ምክንያቱም አንዳንድ ልጃገረዶች (በተለይም በገጠር አካባቢዎች) የወርአበባ የከባድ ህመም ምልክት እንደሆነ ያምናሉ። ለሴት ልጅ ወሲባዊ ባህሪ መጥፎ ስም የሚሰጠው አድሎአዊ የማህበራዊ ድንጋጌ፣ የወርአበባ የወሲብ ተግባር ምልክት ነው ከሚለው የተሳሳተ እምነት ጋር ተዳምሮ እናቶችና ሴቶች ልጆች እንዲሁም እህቶችም እንኳ በወር አበባ ጉዳይ ላይ መወያየት እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። በትምህርት ቤት የውሃ፣ የጽዳት መገልገያዎችና የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ አቅርቦት አለመኖር፣ እንዲሁም በወንዶች የሚደርስባቸው ሹፈት ተዳምሮ የተወሰኑ ልጃገረዶች በየወሩ ለብዙ ቀናት ከትምህርት ቤት እንዲቀሩ ያስገድዳቸዋል።

## 3.5 ወሲባዊና የስነተዋልዶ ጤና

ምንም እንኳን የእርግዝና መከላከያ አጠቃቀም በብሔራዊ ደረጃ እና በእድሜ ደረጃዎች ሁሉ በ2000 ከነበረው ከ6% በ2016 ወደ 35% በፍጥነት ቢጨምርም (CSA and ICF, 2017)፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚጠቀሙ ታዳጊ ልጃገረዶች በዕድሜ ከሚበልጧቸው ሴቶች ያነሱ ናቸው (UNFPA, 2017)። በሁሉም የምርምር ጣቢያዎች ውስጥ ያሉ ልጃገረዶች በዋነኛነት በመርፌ የሚሰጡ የወሊድ መከላከያ የሚጠቀሙ ከመሆናቸው በስተቀር፣ የታዳጊዎች የወሊድ መከላከያ አወሳሰድ መረጃ፣ አቅርቦቶች እና

> **አማቴ በወሊድ ወቅት ስለሚከሰቱ የጤና ችግሮች ግንዛቤ ስለነበራት ለአንድ ዓመት ያህል የወሊድ መቆጣጠሪያ እንድጠቀም ነገረችኝ። ለባለቤቴ ስነግረው አልፈልግም አለ።**
>
> **(አንዲት ያገባች የ15 ዓመት ልጃገረድ፣ ባቱ፣ ምስራቅ ሸዋ፣ ኢትዮጵያ)**

አገልግሎቶች በጣም የተለያየ መሆኑን የጌጅ የአይነታዊ ምርምር ግኝታችን አረጋግጧል። በደቡብ ጎንደር 45 በመቶ የሚሆኑት ወጣት ሴቶች፣ በምሥራቅ ሐረርጌ ውስጥ ካሉት 12% እና በዞን 5 ካሉት 5% ከሚሆኑት ጋር ሲነጻጸሩ የእርግዝና መከላከያ ዘዴን በትክክል መለየት ይችላሉ።

የአይነታዊ ምርምራችን የሚያሳየው፣ በደቡብ ጎንደር፣ ባለትዳሮችም ሆኑ ያላገቡ ልጃገረዶች የወሊድ መቆጣጠሪያ የተሻለ ተጠቃሚ መሆናቸውንና ባሎች የእናቶችን እና የህፃናትን ደህንነት ለማሻሻል አብዛኛውን ጊዜ የዘገየ እርግዝናን የሚደግፉ መሆናቸውን ነው። እንዲሁም፣ ያላገቡ ሴት ልጆች ወላጆች ብዙውን ጊዜ ሴት ልጃቸው ብትደፈር እንኳ እርግዝናን ለመከላከል ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው። በሌላ በኩል በኦሮምያ በሕፃናቱ ግፊት የሚፈጸሙ ያለዕድሜ ጋብቻዎች በጣም እየተለመዱ እና በወጣትነት ዕድሜያቸው እየተከናወኑ ባሉበት በአሁኑ ወቅት ጥቂት ያገቡ ልጃገረዶች መውለድ እንደሚችሉ ለማረጋገጥ እስከሚወልዱ ድረስ ቢያንስ አንድ ጊዜ የወሊድ መከላከያ ይጠቀማሉ። ምንም እንኳን ዘመድ የሆኑ ሴቶች የእርግዝና መከላከያ እንዲጠቀሙ ቢያበረታቷቸውም፣ ባሎች ብዙውን ጊዜ ይህንን ይከለክላሉ። አንዲት የ15 ዐመት ያገባች ሴት ከባቱ (ምስራቅ ሸዋ) እንዲህ ስትል ገልጻለች፣ ‹‹አማቴ በወሊድ ወቅት ስለሚከሰቱ የጤና ችግሮች ግንዛቤ ስለነበራት ለአንድ ዓመት ያህል የወሊድ መቆጣጠሪያ እንድጠቀም ነገረችኝ። ለባለ ቤቴ ስነግረው አልፈልግም አለ።›› በአፋር፣ የአንዳንድ አርብቶ አደር ማህበረሰቦች ከከተማ ርቀው የሚኖሩ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ፣ ለከተማ ቀርብ መሆን የወሊድ መቆጣጠሪያ ለመጠቀም የበለጠ ጠቀሚነት አለው። በማህበረሰ ሀ ውስጥ ያሉ ታዳጊዎች እንደገለጹት በታዳጊነት ዕድሜ አጋማሽ ውስጥ ያሉ ያላገቡ ልጃገረዶች ወደ አብሱማ ጋብቻ ከመግባታቸው በፊት እርግዝናን ለመከላከል የወሊድ መቆጣጠሪያ ይጠቀማሉ። በዞን 5 ውስጥ ያሉ ወንዶች ልጆች ያስተዋሉት ነገር፣ ከጋብቻ በፊት የሚከሰት እርግዝና ለሚያስረግዛት ሰው ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትልበት ሲሆን፣ የልጃገረዷን አብሱማ ለመካስ ብዙ ከብቶች እንዲከፍል ቅጣት ይጣልበታል። ከማህበረሰብ ሀ አንድ በዕድሜ ከፍ ያለ ልጅ እንዳብራራው: ‹‹ልጅቱ ካረገዘች በሕይወት ዘመኗ ሁሉ እንዲከፍል ቅጣት ይጣልበታል››።

አዋቂዎች የኤች.አይ.ቪ ስርጭት መጨመር አሳሳቢ መሆኑን ይገልጻሉ። እንደምክንያት ይሆናል ያሉትም ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሰት እየጨመረ መሄዱ፣ በከተሞች አካባቢ በቤት ውስጥ ልጃገረዶችንና ወጣት ሴቶችን የሚጠብቁ ወንዶች ቁጥር መጨመር፣ እና በዞን 5 ውስጥ የታዳጊዎች ወሲባዊ ባህሪ መለወጥ (ለምሳሌ ሳዳህ ከተሰኘ ታዳጊ ሴቶች እና ወንዶች የሚሳተፉበት ባህላዊ ጭፈራ ጋር ተያይዞ ከብቻ በፊት የሚፈጸም ወሲባዊ ግንኙነት) ናቸው። በተለይም የኮንዶም አቅርቦቶች በብዙ አካባቢዎች የተገደቡ በመሆናቸውና በአጠቃቀማቸው ላይ ያለው ማህበራዊ ተቀባይነት በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭ መሆኑ ሌላው ዋና ስጋት ሆኗል።

## 3.6 የለውጥ ስትራቴጂዎች

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በብዙ የገጠር ምርምር ጣቢያዎቻችን በተለይም በደቡብ ጎንደር የጤና፣ የምግብ እና ስነተዋልዶ ጤና ልማት ማሻሻያዎችን በማምጣት ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፤ ሆኖም ግን የአገልግሎቱ ጥራት በምስራቅ ሐረርጌና በተለይም በዞን 5 (አፋር) ውስጥ የበለጠ ተለዋዋጭ ነው። በተጨማሪም፣ መሠረታዊ አገልግሎቶችን በመስጠት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የአመጋገብንና የንፅህናን አስፈላጊነት እንዲሁም የቅድመ እርግዝና አደጋዎችን ለወላጆችና ለወጣቶች እያስተማሩ ነው። በከተሞች አካባቢ አንዳንድ የጤና ክሊኒኮች የምሽት አገልግሎት፣ የግል የማማከርና የቤት ለቤት ጉብኝቶችን የሚያካትቱ ለታዳጊዎች ተስማሚ የሆኑ አገልግሎቶችን እየሰጡ ነው። ምንም እንኳን ከአፍላ ወጣትነት ጋር የተያያዙ መረጃዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቢቀርቡም፣ የሴቶች ክለቦች ለሴቶች ልጆች ስለ አፍላ ወጣትነት ጠቃሚ መረጃዎችን በመስጠት እና በወር አበባ ወቅት ድጋፍ በመስጠት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። በአመጋገብ ረገድ የውጤታማ ሴፍቲኔት ፕሮግራም (Productive Safety Net Programme) በቤተሰብ ደረጃ የምግብ እጥረትን ለማቃለል እየረዳ ሲሆን የት/ቤት ምገባ ፕሮግራሞች በሚኖሩበት አካባቢ በድርቅ በተጎዱ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚገኙ ታዳጊዎች በረሃብ እንዳይጠቁ እየረዱ ነው። ይሁን እንጂ፣ መልስ ሰጭዎች በበርካታ የምርምር ማህበረሰባችን ውስጥ በሴፍቲኔት ፕሮግራሙ ውስጥ የተካተቱት አባወራዎች ዝርዝር እስከ አንድ አመት ድረስ ሳይቀየር የቆየ በመሆኑ በተለይም ለወጣት ባለትዳሮች ችግር ያለበት መሆኑን ተናግረዋል።

# 4 ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት

## 4.1 መግቢያ

የሥነ ልቦናና ማህበራዊ ደኅንነት በታዳጊነት ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶችን ራስን የማወቅ፣ የራሳቸውን የወደፊት ግቦች የማውጣትና ችግሮችን የመቋቋም ችሎታን ያጠቃልላል፡ ፡ ውስጣዊ ስሜታዊ አቅም እና ከታመኑ አዋቂዎችና እኩዮች የሚደረግ ውጫዊ ማህበራዊ ድጋፍ አስፈላጊነት የሚመለከት ሲሆን (Jose et al., 2012) የጠበቀ ማህበራዊ ትስስር የሌላቸው ታዳጊዎች በአዕምሮ ህመም የመያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው (Lamblin et al., 2017)፡፡ እርስበርስ የመተባበርና የጋራ ደኅንነት አስተሳሰብ ከረጅም ጊዜ በፊት ባህል በሆነባት ኢትዮጵያ (Kassa et al., 2016) ከቤተሰብ ጋር ቅርብ መሆን በተለይ ለታዳጊ ጤንነት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ (Camfield and Tafere, 2009; 2011; Bireda and Pillay, 2017; Jones et al., 2017)፡፡ በሌላ በኩል ግን በኢትዮጵያ የልጆች የአእምሮ ህመም ከፍተኛ (ከ 12% እስከ 25% መካከል) ሲሆን፣ አጋላጭ ምክንያቶቹም ከፍተኛ ድህነት፣ የምግብ ዋስትና አለመኖርና ለጥቃት መጋለጥ መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ (Asfaw and Hagos, 2008; MoH, 2012; Jebena et al., 2016)፡፡

ኢትዮጵያውያን ታዳጊ ልጃገረዶች ከወንድ እኩዮቻቸው ይልቅ ደካማ የሥነ ልቦና ውጤቶች ይታዩባቸዋል። ታዳጊ ልጃገረዶችን ብዙውን ጊዜ በማኅበራዊ ኑሮ እንዲገለሉ የሚያደርጓቸውና እንቅስቃሴያቸውን የሚገድቡ ማህበራዊ ደንቦች በቤት ውስጥ ሥራ ላይ ሴቶችን ከመጠን በላይ ጫና በመፍጠር፣ ትምህርታቸውን ለአደጋ ላይ በመጣል እንዲሁም ለወሲባዊ ጥቃት የመጋለጥ ዕድላቸውን ከፍ እንዲል በማድረግ የዚህ የጾታ መድሎ ውጤት ቁልፍ ምክንያቶች ሆነው ተለይተዋል (Jones et al., 2017; Pankhurst et al., 2018)፡፡ አንዳንድ የልጃገረድ ቡድኖች፣ የታጨና ያገቡ ሴት ልጆችን እና የቤት ሰራተኞችን ጨምሮ በተለይ ለአዕምሮ ጤና ችግር ተጋላጭ ናቸው፡፡ (Erulkar and Ferede, 2009; Gage, 2013; Jones et al., 2014b; 2016b)፡፡

## 4.2 ችግር የመቋቋምና በችሎታ የመተማመን ብቃት

አጠቃላይ የጤና መጠይቅ (GHQ-12)፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመሰከረለት የአእምሮ ህመም መለኪያ (Tait et al., 2003)[3] በመጠቀም በአጠቃላይ በእኛ ናሙና ውስጥ ያሉ ወጣቶች (አማካይ ነጥብ ለታናሹ ቡድን 0.95፣ እና ለታላቁ ቡድን 1.64) በስሜታዊነት ጠንካራ መሆናቸውን የጊጅ የዳሰሳ ጥናት ግኝቶች ያሳያሉ።

ሆኖም ግን፣ እንደየቦታው ልዩነቶች አሉ። ለምሳሌ በከተሞች የሚገኙ ታዳጊዎች በአጠቃላይ ከገጠር አቻዎቻቸው ይልቅ የከፋ ችግር (16% ልዩነት) ያለባቸው ሲሆን፣ በተለየ ሁኔታ አፋር ውስጥ ያሉ ታዳጊዎች ከሌሎች አካባቢዎች ጋር ሲነፃፀር የአጠቃላይ ጤና ውጤት የሌሎቹን እጥፍ መሆኑ የከፍተኛ ደረጃ የአእምሮ ችግርን ያመለክታል፡፡ ከዚህ በታች በዝርዝር እንደምናየው፣ ይህ ችግር ምናልባት ከአሳዳጊዎች የሚያገኙት ስሜታዊ ድጋፍ ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም ከእኩዮቻቸው ጋር ካላቸው በጣም ውስን የሆነ ማህበራዊ ግንኙነት ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም የአይነታዊ ግኝቶቻችን በአፋር ማህበረሰብ ውስጥ የታዳጊዎችን ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት በአእምሮ ጤንነት ችግርና በድህነትና በምግብ እጦት ተጋላጭነት መካከል ካለው ቀጥተኛ ትስስር ጋር ይዛመዳል (Jebena et al., 2016)፡፡ በማኅበረሰብ ሀ፣ ሰሚሮቢ ውስጥ አንዲት የ10 ዓመት ልጃገረድ እንዲህ ስትል ገልፃለች፤ ‹‹በቤት ውስጥ ያለነው ልጆች 6 እንሆናለን። በቂ ምግብ ስለሌለ መመገብ አቁመናል። ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳችን በፊት ምግብ እንድንመገብ መምህሩ ያሳስበናል ነገር ግን ቁርስ አልበላም። እናቴ ጠዋት ምግብ አታዘጋጅም - ቡና ብቻ ነው የምታፈላው።››

በአጠቃላይ የጤና መለኪያ (GHQ-12) ውጤቶች ውስጥ ያለው የጾታ ልዩነት ከዝቅተኛው የዕድሜ ክልል ቡድናችን ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ እና ብዙም ልዩነት የማይታይበት ግን በዕድሜ ከፍ ያሉት ታዳጊ ሴቶች ከወንዶቹ አቻዎቻቸው ጋር ሲነፃፀር በጣም የከፋ (28% ከፍ ያለ) ነው። ይህ የጾታ ልዩነት በችሎታ የመተማመን ብቃት መለኪያ ላይም የተገኘ ሲሆን፣ በዕድሜ ከፍ ያሉ ሴቶች ከወንዶች 5 በመቶ በታች በማስመዝገብ በኢትዮጵያ ከተካሄዱ ሌሎች ጥናቶች ጋር የሚጣጣም ሆኗል። ለምሳሌ፣ ዴርኮን እና ሲንግ (Dercon and Singh, 2013) የወጣቶች ህይወትን መረጃ በመጠቀም፣ የኢትዮጵያ ልጃገረዶች የራሳቸውን ህይወትና ዕጣ ፈንታ ከመቆጣጠር ስሜት አንጻር ከወንዶች ይልቅ በራስ ችሎታ የመተማመን ብቃታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ገልጸዋል። በተመሳሳይ የጆንስና ጓደኞቹ (Jones et al., 2014a; 2014b; 2016b; 2016c; 2017c; 2017c) ጥናት እንዳመለከተው የጾታ ልዩነት የታየው ምናልባትም በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶች በሕይወታቸው ላይ ተጽዕኖ ባላቸው አስፈላጊ ውሳኔዎች ላይ

---

3 አጠቃላይ የጤና መጠይቅ (GHQ-12) ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ታዳጊዎች ዙሪያ ጥቅም ላይ ባይውልም በኤልኤምአይሲ (LMICs) ሀገራት ትክክለኛነቱ መረጋገጡን ልብ ይሏል (e.g. Abubakar et al., 2011, Gelaye et al., 2015)፡፡ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው በጎልማሶች ላይ ቢሆንም በታዳጊዎች ላይም ጥቅም ላይ ውሏል - በTait et al. (2003) ከ11 – 15 እድሜ ባላቸው ትንንሽ ታዳጊዎች ፣ በታዳጊዎችና ወጣት ጎልማሶች (13- 22 እድሜ ባላቸው) በማላዊ (Baird et al., 2012) እና በታዳጊዎችና ወጣት ጎልማሶች (18- 35 እድሜ ባላቸው) በቺሊ፣ ኢትዮጵያ፣ ፔሩ እና ታይላንድ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በተለይም የሚያገቡበትን ዕድሜ፣ ትምህርታቸውን ከአንደኛ ደረጃ በላይ ስለሚቀጥሉበት ሁኔታ፣ እና በአካባቢያቸው በሚያደርጉት እንቅስቃሴ (በወሲባዊ ጥቃት እና በቤተሰብ ክብር ስጋት ምክንያት) ውሳኔ በመስጠት እምብዛም የማይሳተፉ በመሆናቸው ነው ።

ለአካል ጉዳተኛ ታዳጊዎች፣ የአጠቃላይ ጤና መለኪያ (GHQ-12) ውጤቶች በእኛ የምርምር ናሙና ውስጥ ለነበሩ ለሁለቱም የዕድሜ ክልል ለሚገኙ ታዳጊዎች አካል ጉዳት ከሌለባቸው በሁለት እጥፍ የሚበልጡ ሲሆን፣ በተጨማሪም በራስ ችሎታ የመተማመን መለኪያ ዝቅተኛ ውጤት (አካል ጉዳተኞች 8% ዝቅ ያለ ሆኖ) በእድሜ ከፍ ባሉት ላይ ተንፀባርቋል። የአይነታዊ ምርምራችን ግኝቶች እንደሚያመለክቱት፣ይህ የሆነው ምናልባትም በሚያጋጥማቸው ከፍተኛ የመገለል፣ መድሎና ማህበራዊ መነጠል ምክንያት ነው። አንዲት ትምህርት ቤት ያልገባች የ15 ዓመት አይነ ስውር ታዳጊ እንዳብራራችው፣ ‹‹ጓደኛ የለኝም። ሀዘን ሲሰማኝና የሚያስጨንቀኝ ነገር ሲኖር ለማንም አልናገርም። ጸጥ ብዬ ቁጭ እላለሁ።››

## 4.3 የአዋቂዎች ስሜታዊ ድጋፍ

የቤተሰብ ድጋፍ ለኢትዮጵያዊያን ታዳጊዎች የስነ-ልቦናና ማህበራዊ ደህንነት በጣም ወሳኝ ሆኖ ተገኝቷል (Camfield and Tafere, 2009; 2011; Bireda and Pillay, 2017; Jones et al., 2017)። ታዳጊ ልጃገረዶችና ወንዶች ከ 0 እስከ 4 ባለው የሊኬት መለኪያ ወንድ እና ሴት አሳዳጊዎቻቸው ጋር በትምህርት፣ ሥራ፣ ጉልበተኝነት እና ሀይማኖት ጉዳይ ላይ መወያየት መቻላቸውን ውጤታቸው የወጣት ቡድኑ በአማካኝ 2.01 ለየአባቶች እና 2.05 ለእናቶች እንዲሁም በዕድሜ ከፍ ካሉት መካከል 2.26 እና 2.58 በቅደም ተከተል ተመዝግቧል። በአጠቃላይ፣ ልጃገረዶች ከወንዶች ባነሰ ከአባቶቻቸው ጋር መወያየት እንደማይችሉ የሚሰማቸው ሲሆን፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ታዳጊዎች አካል ጉዳት ከሌለባቸው እኩዮቻቸው ይልቅ ከወላጆቻቸው ጋር የመወያየት አቅማቸው ዝቅተኛ እንደነበረና ልዩነቱ በተለይ በእናቶች ላይ ጎልቶ የሚታይ (17% ያነሰ) እንደሆነ ገልጸዋል። በገጠር አካባቢዎች ለአብዛኞቹ ታዳጊዎች ከቤተሰባቸው ጋር ያላቸው ስሜታዊ ትስስር ከእኩዮቻቸው ጋር ካላቸው ትስስር ይልቅ አስፈላጊ መሆኑን የጆንስና ጓደኞቹ (Jones et al., 2017)) ጥናት የሚያሳይ ሲሆን የጌጅ ግኝቶች እንደሚያመለክቱት በከተማ የሚኖሩ ታዳጊዎች በገጠር ከሚኖሩ ልጆች ይልቅ ጉዳዮችን ከወላጆቻቸው ጋር ለመወያየት እንደሚችሉ ይሰማቸዋል። ይህ ሊሆን የቻለው በከተማ አካባቢዎች ባለው የልጅ አስተዳደግ ዘይቤ መለወጥ ምክንያት ነው። የካሳ (Kassa et al., 2016) ምርምር እንደሚያመለክተው የከተማ ወላጆች (በተለይም የተሻሉ የሚባሉት) በልጆቻቸው ስሜታዊ እርካታ ላይ የበለጠ መዋዕለ ንዋይ አፍስሰው እና የሌጆቹን ግላዊ ፍላጎት ለማሳደግ የሚያስችላቸውን ስሜታዊና ወቀታዊ ድጋፍ ይሰጧቸዋል። በእርግጥ ይህ በእኛ የአይነታዊ ምርምር ግኝቶችም የከተማ ታዳጊዎች ከወላጆቻቸው ጋር የበለጠ ግልጽ ውይይት የድረግ ፍላጎት እንዳላቸው ተረጋግጧል። ለምሳሌ ያህል፣ አንዲት የ16 ዓመት ወጣት ከባቱ፣ ምስራቅ ሸዋ፣ እንዲህ ስትል ገልጻለች: ‹‹ለእናትና አባቴ በጣም ግልጽ ነኝ። እነሱ በእኔ ስለሚተማመኑብኝ



ወንድ ታዳጊ ከአፋር © ናታሊ በርትራምስ / ጌጅ 2019

> **አንዳንድ ጊዜ ልጃገረዶች ብሶታቸውን ለወላጆቻቸው ሲያካፍሉ ከሌሎች አካላት ጋር ግጭት ያስከትላል። ለምሳሌ አንዲት የተደፈረች ልጃገረድ ለቤተሰቧ የሆነውን ብትነግራቸው እሷን ከመርዳት ይልቅ የደፈራትን ለመደብደብ ወይም ለመግደል ሊሄዱ ይችላሉ።**
>
> **(አንዲት የ12 ዓመት ልጃገረድ፣ ማህበረሰብ ሀ, ዞን 5፣አፋር፣ ኢትዮጵያ)**

ፈቃዳቸውን የማልጠይቅባቸው ጊዜያት አሉ። እንዳያስቡ ብቻ ወደ አንድ ቦታ እንደምሄድ እነግራቸዋለሁ። ስለዚህ በቤታችን ውስጥ ጥርጣሬ አይኖርም፣ እርስ በእርሳችን እንተማመናለን። ለምሳሌ፣ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ለመግዛት አባቴን ገንዘብ እንዲሰጠኝ እጠይቀዋለሁ።››

በተቃራኒው፣ በገጠሩ ማህበረሰብ ውስጥ፣ እና በተለይም በጣም ድሃ በሆኑ ቤተሰቦች ውስጥ፣ የኢኮኖሚ አስፈላጊነት ማለት አብዛኛዎቹ ወላጆች ልጆቻቸው ቤተሰቦቻቸውን ማስተዳደር በሚችሉባቸው መንገዶች ላይ ማተኮራቸውን ይቀጥላሉ ማለት ነው። ከማህበረሰብ ሸ፣ ሀረርጌ፣ አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጭ እንዳስረዳው፣ ይህ በልጅ አስተዳደግ ትምህርት እጥረት ምክንያት የተከሰተ መሆኑን ገልፀዋል፤ ‹‹ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር በመወያየት ረገድ ክፍተት አለ።... ይህ እውቀት ባለመኖር የሚመጣ ክፍተት ነው።›› ይህ የግንኙነት ክፍተት በተለይ በአፋር ማኅበረሰቦች ውስጥ በወሰድነው ናሙና ውስጥ በጣም ጎልቶ የታየ ሲሆን ታዳጊዎች ከወላጆቻቸው ጋር ለመወያየት እምብዛም የማይታዩበት (ከአጠቃላይ መለኪያ አማካይ 2.01 እና 2.05 ውጤት ጋር ሲነፃፀር፣1.33 ከአባቶች ጋር እና 1.35 ከእናቶች ጋር) ነበር። ግኝታችን እንደሚያመለክተው ይህ የሆነው በተለይ ለሴቶች እና ከቤተሰብ ክብር ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ነበር። ከማህበረሰብ ሀ፣ ዞን 5 (አፋር)፣ የ 12 ዓመት ታዳጊ ስታብራራ ‹‹አንዳንድ ጊዜ ልጃገረዶች ብሶታቸውን ለወላጆቻቸው ሲያካፍሉ ከሌሎች አካላት ጋር ግጭት ያስከትላል። ለምሳሌ አንዲት የተደፈረች ልጃገረድ ለቤተሰቧ የሆነውን ብትነግራቸው እሷን ከመርዳት ይልቅ የደፈራትን ለመደብደብ ወይም ለመግደል ሊሄዱ ይችላሉ።››

## 4.4 የእድሜ እኩያዎች ማህበራዊ ድጋፍ

ከእኩዮችና ከማህበረሰቡ ጋር ያለው ማህበራዊ ትስስር እንዲሁ ለታዳጊዎቸች የስነ-ልቦናና ማህበራዊ ደህንነት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል (Population Council and UNFPA, 2010; Edmeades et al., 2014; Sewasew et al., 2017; Jones et al., 2014a; 2016b; 2017)። ከሶስት አራተኛ በላይ (76%) የሚሆኑት ታዳጊዎችና ከ84% በላይ በዕድሜ ከፍ ያሉ ታዳጊዎች የሚያምኑት ጓደኛ እንዳላቸው የዳሰሳ ጥናታችን አመልክቷል። ታዳጊ ልጃገረዶች እና ወንዶች ከጓደኞቻቸው ጋር አብረው ጊዜ እንደሚያሳልፉ፣ ሌሎች የዕለት ከዕለት ተግባራትን ለምሳሌ፣ ውሃ መቅዳት፣ መጫወት፣ ማጥናት፣ እና የእኩዮች ተጽዕኖን ለመቋቋም መተጋገዝ የመሳሰሉትን በጋራ እንደሚያከናውኑ ተናግረዋል። ከ10-12 አመት እድሜ ያላቸው ልጃገረዶች በማህበረሰብ ልየታ ውስጥ ተሳታፊ የነበረች ልጃገረድ እንደገለፀችው፣ ‹‹አንዳንድ ጊዜ ጥሩ ጓደኞች አሉ፤ መጥፎ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጓደኞችም አሉ።

ለምሳሌ ትምህርቴን እንዳጠና የምትገፋፋኝ፣ የቤት ስራ አብረን የምንሰራ፣ የቤት ውስጥ ስራዎችን የምታግዘኝ እንደ እህቴ የምቆጥራት ጓደኛ አለችኝ። በተቃራኒው ደግሞ ወደተሳሳተ የህይወት ጎዳና የሚወስዱህ ልጃገረዶች አሉ... ወንዶች ወደሚገኙበት የተሳሳተ ቦታ እንዲሄዱ ጓደኞቻቸውን የሚገፉ ልጃገረዶች አሉ። እግር ኳስ ለመመልከት ወይም አብረዋቸው ምግብ ለመግዛት እና ለመጠጣት ሲሉ ከወንዶች ጋር መሄድ አጥብቀው ይፈልጋሉ።››

ከእኩዮች ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ጾታ ጠቃሚ ተፅእኖዎች እንዳሉት የሚያጎላ፣ ነገር ግን ልጃገረዶች በማህበራዊ መነጠል የመጠቃት ዕድላቸው ከፍተኛ መሆኑን (Edmeades et al., 2014; Jones et al., 2014a; 2016b; 2016c; 2017) እና ጥቂት ጓደኞች የሚኖራቸው መሆኑን (Camfield, 2011) ከሚያመለክተቱት ሰፊ ጥናታዊ ጽሑፎች በተቃራኒው የእኛ የዳሰሳ ጥናት ግኝቶች የተለየ ስዕል ያሳያሉ። ወጣት ልጃገረዶች የሚያምኑት ጓደኛ የመያዝ ዕድላቸው 7% ሲሆን በከፍተኛው የዕድሜ ክልል ውስጥ ባሉት መካከል የጾታ ልዩነት አለመኖሩን ደርሰንበታል። ሆኖም ግን፣ ልጃገረዶች በተለይም በመካከለኛና በከፍተኛው የታዳጊነት ዕድሜ ላይ ሲደርሱ ከዕድሜ እኩዮቻቸው ህብረት የመቀላቀል እድላቸው ዝቅተኛ ነው። ማለትም፤ በዕድሜ ታናሽ የሆኑ ልጃገረዶች በተመሳሳይ ዕድሜ ውስጥ ከሚገኙ ወንዶች ይልቅ ከእኩዮቻቸው ቡድን አባል የመሆን እድላቸው 19% ዝቅተኛ ነው፣ ዕድሜያቸው 15 እና ከዚያ በላይ ከደረሱ በኋላ ደግሞ ወደ 35% ያንሳል። በዝቅተኛውና በከፍተኛው የዕድሜ ክለል ውስጥ የሁለቱም ቡድን ሴት ልጆች ከእኩዮቻቸው ጋር በስፖርታዊ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ እድላቸው 22% እና 46% በቅደም ተከተል ዝቅተኛ ነው። አንድ ቁልፍ የመረጃ ሰጪ ከማህበረሰብ ቀ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ እንደገለጹት፡ “በዚህ ወረዳ ውስጥ ሴት ልጆችን ወደ ስፖርት መላክ ባህላዊም የተለመደም አይደለም... ለጊዜው ሁሉም የክለቡ አባላት ወንዶች ናቸው።››

> **አንዳንድ ጊዜ ጥሩ ጓደኞች አሉ፤ መጥፎ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጓደኞችም አሉ። ለምሳሌ ትምህርቴን እንዳጠና የምትገፋፋኝ፣ የቤት ስራ አብረን የምንሰራ፣ የቤት ውስጥ ስራዎችን የምታግዘኝ እንደ እህቴ የምቆጥራት ጓደኛ አለችኝ። በተቃራኒው ደግሞ ወደተሳሳተ የህይወት ጎዳና የሚወስዱህ ልጃገረዶች አሉ...**
>
> **(አንዲት የ10–12 ዓመት በኢትዮጵያ የማህበረሰብ ልየታ ተሳታፊ የነበረች)**

በአፋር ውስጥ ባለው የአይነታዊ ምርምር ግኝታችን ውስጥም ጠንካራ የጾታ ልዩነቶች ነበሩ። ልጃገረዶች እና ወንዶች ልጆች ሁለቱም ፊዬማ የተሰኘው የአብሮ አደግ የዕድሜ እኩዮች ቡድን አካል ሲሆኑ፣ በባህሉ መሰረት ለወንዶች ፊዬማ የበለጠ የተደራጀ ሚና ይሰጣል፤ ምክንያቱም ታዳጊ ወንዶችና ወጣቶች የጎሳውን ሕጎችና ሥነ ምግባራዊ ደንቦቻቸውን እንዲማሩበት የሚያደርግ ሂደት ስለሆነ ነው። ምንም እንኳን ይህ በታዳጊነት ዕድሜ ላይ ያሉ ልጆችን ጠንካራ የአኔነት ስሜት እንዲኖራቸው ቢያደርግም፣ የፊዬማ ደንቦችን አለማክበር እስከ ሞት የሚያደርስ የቡድን ቅጣት ሊያስከትል የሚችል አሉታዊ ጎን አለው።

በታዳጊ ወንዶች የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች በሽማግሌ የቀብር ሥነ-ስርዓት ላይ አለመገኘትን እንደ ምሳሌ በማንሳት እንዳስረዱት፣ ‹‹የፊዬማ ህብረቱ ይደበድበዋል... በጣም እስኪቆስል ድረስ ይጎዳዋል... ከሞተም እዚያው ይቀበራል... በጣም ከተጎዳ በባህላዊ አምቡላንስ (ቃሬዛ) ወደ ጤና ተቋም እንወስደዋለን፤ ለህክምና ወጪው ቤተሰቡን አንጠይቅም። ወጪውን ፊዬማው ይሸፍናል... ይህን የምናደርገው ከመደብደቡ በፊት ከነበረው የተሻለ ለማድረግ ነው።››

## 4.5 ጥራት ያለው የስነ-ልቦናና ማህበራዊ አገልግሎት

ጥናቶች እንደሚያሳዩት የኢትዮጵያ ታዳጊዎች የስነ-ልቦናና ማህበራዊ አገልግሎቶች በተለይም በገጠር አካባቢዎች ሲበዛ በጣም ውስን ናቸው (Jones et al., 2014b; 2017)። ምንም እንኳን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንዳንድ ጊዜ (ቢያንስ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ) ተማሪዎችን አካላዊ፣ ስሜታዊ እና አካዴሚያዊ ችግሮችን ለመቋቋም የሚረዳ መመሪያና የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ቢሆንም፣ የፕሮግራም እውቀትና ግንዛቤና ግን ዝቅተኛ ነው። ለምሳሌ አንድ ጥናት እንዳመለከተው ግማሽ የሚሆኑት ተማሪዎችና አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት መምህራን ብቻ አገልግሎቶች መኖራቸውን የሚያውቁ ሲሆን፣ አንድ አምስተኛ የሚሆኑት ብቻ ማንኛውንም ዓይነት እርዳታ የሚሹ ነበሩ (Alemu, 2013)። የGAGE ናሙናችን በዋናነት አሁንም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያለና የአማካሪዎች ተደራሽነት ይበልጥ የተገደበ ሲሆን፣ ከመላሾቻችን መካከል አንድም የትምህርት ቤት አማካሪ ማግኘት የቻለ የለም። ከምንም በላይ፣ ልጃገረዶች አገልግሎቶችን የማወቅ ዕድላቸው ከፍ ያለ መሆኑን፣ ወንዶች ልጆች ደግሞ እነሱን የመጠቀም ዕድላቸው ከፍተኛ መሆኑን ከሚያሳየው ከአለሙ (Alemu, 2013) ጥናት ወጤት በተቃራኒ፣ የኛ ግኝቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ፣ ልጃገረዶች መደበኛ ያልሆነ የምክር አገልግሎትና መመሪያ ከልጃገረዶች ክለቦች በተሻለ ማግኘት ይችላሉ፤ ይህም በተለይ በአማራ ክልል የበለጠ ተስፋፍቶ ይገኛል። እንዲያም ሆኖ፣ ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች እንደሚሉት፣ ይህ ምንም ልዩ የሥነ-ልቦና ሥልጠና ባላገኙ ግለቦች አስተባባሪነት ላይ የተመሰረተ ነው። ከጎንደር አንዲት የልጃገረዶች ክበብ አስተባባሪ እንደገለጸቸው፣ ‹‹የሴት ተማሪዎቹን ችግሮች ስናይ ከትምህርት ቤቱ የሚያደረግላቸው ምንም ድጋፍ የለም፣ የሚረዳቸውም የለም። ልጃገረዶቹን ቀረብ ብሎ ችግሮቻቸውን በዝርዝር የሚረዳላቸውና የስነ-ልቦና ድጋፍ ሊያደርግላቸው የሚሞክር ማንም የለም። በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉት የልጃገረዶች ክለቦችም እንኳ የደከሙ ናቸው። ትምህር ቤቱ ክለቦቹን የሚደግፍበት ምንም ሀብት የለውም።››

ለልጆችና ለታዳጊዎች የአዕምሮ ጤና ችግሮች፣ መንስኤዎችና ህክምናዎች የወላጆች ግንዛቤ በአገልግሎቶች አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል። አበራና ጓደኞቹ (Abera et al., 2015) ከ90% በላይ የሚሆኑት ወላጆች የወጣት ሰዎች የአዕምሮ ህመሞች መንስኤ መናፍስት እንደሆኑ ያምናሉ፤ እንዲሁም ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው ችግር ካጋጠማቸው ሃይማኖታዊ ፈውስን ይፈልጋሉ ወይም ይጸልያሉ ብለዋል። የጌጅ አይነታዊ ግኝቶችም እንዲሁ የታዳጊዎች የስነልቦና ደህንነት ችግሮች መፍትሄዎች ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ አገልግሎቶች ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ያሳያሉ። ለምሳሌ፣ በጎንደር በሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ማኅበረሰቦች ውስጥ ወላጆች ከካህናቱ ምክር ለማግኘት እና/ወይም በጸበል ፈውስ ለማግኘት ይፈልጋሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በአፋር በተለይም ታዳጊ ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች ቤዳኩበር በሚባል ተመስጦ በሚመስል ዓይነት ሥነ-ሥርዓት የፈውስ ድጋፍ ይፈልጋሉ። በዚህ ሥነ-ሥርዓት መንፈሱን ከታማሚዉ ለማስወጣት ሲባል ግለሰቡ ለብዙ ቀናት በአልጋ ላይ እንዲቆይ ተደርጎ ጓደኞቹ፣ ቤተሰቦቹና ጎረቤቶቹ ጭፈራ እና ድግስ ያካሂዳሉ። ከማህበረሰብ ሀ (ዞን 5፣ አፋር)፣ አንዲት በዕድሜ ከፍ ያለች ታዳጊ ልጃገረድ በቡድን ውይይት ወቅት እንዳብራራችው፣ ‹‹ቤዳኩበር ሲኖር አንድ ላይ ተሰብስበን ክብ እንሰራና እንዘፍናለን፣ እናጨበጭባለን። መሀል ሆና ዘፈኑን የምትመራ አንዲት ሴት ትኖራለች። የምንዘፍነው የታመመው ሰው እፎይታ እንዲያገኝና ከበሽታው እንዲፈወስ ነው።››

መደበኛ የሥነ-ልቦናና የአዕምሮ ህክምና አገልግሎቶች በዋና ዋና ከተሞች በሚገኙ ሆስፒታሎች ውስጥ ቢኖሩም የአይነታዊ ምርምር ግኝቶቻችን ከነዚህ ምላሽ ሰጭዎቻችን መካከል አንዳቸውም እንደዚህ ዓይነት አገልግሎቶችን እንዳልፈለጉ አመልክተዋል። ይህ ማለት ምንም እንኳን በታዳጊዎች ዘንድ ራስን ማጥፋት፣ ራስን የማጥፋት ሙከራዎችና የደረሱበት መጥፋት ሁኔታዎች ያሉ ቢሆንም በተለይም ልጃገረዶች ያለዕድሜያቸው እንዲያገቡ የተደረጉ ወይም ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ የተደረጉ መሆናቸውን የሚገልጹ በርካታ ሪፖርቶች ቢኖሩም ማለት ነው። እንዲሁም በ2017 መገባደጃ/ በ2018 መጀመሪያ ላይ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች መካከል በተከሰተው የጎሳ ግጭት ምክንያት ለተፈናቀሉ ሰዎች በመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ድጋፍ ለመስጠት የተደረገ ጥረት መኖሩን የሚያሳይ ምንም ማስረጃ አላገኘንም። ምናልባት በባቱ፣ ደብረ ታቦርና ድሬዳዋ ከተሞች ለሚገኙ ወላጅ አልባ ሕፃናት፣ የጎዳና ተዳዳሪ ሕፃናትና በወሲብ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ታዳጊ ልጃገረዶች የስነ ልቦና ድጋፍ ለመስጠት በጣም አነስተኛ ሙከራዎች ተደርገዋል።

## 4.6 የለውጥ ስትራቴጂዎች

በአጠቃላይ፣ የታዳጊዎችን የስነ ልቦናና ማህበራዊ ደህንነትና የአእምሮ ጤናን ለማሻሻል ስለታለሙ የለውጥ ስትራቴጂዎች

ያገኘነው ማስረጃ በጣም ውሱን ነው። እነዚህም ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው በልዩ ሁኔታ በትላልቅ ከተማ ማዕከላት ውስጥ በተለይም የጎዳና ተዳዳሪ የሆኑ፣ በወሲብ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ እና/ወይም በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጋላጭ የሆኑ ታዳጊዎችን ለመደገፍ የሚሰሩ አነስተኛ መንግስታዊ ያልሆኑ ፕሮጀክቶች ናቸው፡ ፡ ለስነ-ልቦና ጭንቀት ወይም ለአዕምሮ ጤና እክሎች የተጋለጡ የታዳጊዎችን ወላጆች ለመደገፍ ካለው ተነሳሽነት አንጻር አሁንም የፕሮግራም አወጣጥ በጣም ውስን ነበር። ይልቁንም የሃይማኖት ተቋማት - የኦርቶዶክስ ክርስቲያንና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትና መስጊዶች - አንዳንድ ወላጆች ፍልሰትን የሚመለከቱ ጫናዎች፣ አደንዛዥ ዕጽ ለመጠቀም የእኩዮች ተጽዕኖ፣ ወዘተ ስለመሳሰሉ ወጣቶችን ስለሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች መወያየት የሚችሉባቸው መድረኮች ነበሩ። ከጎንደር በትምህርት ዘርፍ ያሉ ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች የጎልማሶች ትምህርት ማዕከላት አንዳንድ ወላጆች በትምህር በት ስለ ልጆቻቸው ትምህርት ሁኔታ እንዲጠይቁና ልጆቻቸውን በትምህርታቸው ለመደገፍ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንዳስቻላቸው ተናግረዋል።

በአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ፣ በትላልቅ ከተሞች በሚገኙ ሆስፒታሎች ከሚሰጡት የስነ-አዕምሮ ህክምና አገልግሎቶች ውጪ ታዳጊዎችን የሚመለከቱ አገልግሎቶችን ይቅርና አጠቃላይ የሥነ-ልቦና እና የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችን ለማጠናከር ያለው ተነሳሽነት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል። በደብረታቦር ውስጥ አንድ ለየት ያለ ሁኔታ የነበረው በዩናይትድ ስቴትስ አለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (ዩ.ኤስ.አይ.ዲ) የገንዘብ ድጋፍ የተደረገለት የኢትዮጵያ ሶሺዮሎጂስቶች፣ ሶሻል ወርከሮችና አንትሮፖሎጂስቶች ማህበር ከማህበረሰቡ ውስጥ በተለይ ለችግር የተጋለጡ ህጻናትና ታዳጊዎችን ለመደገፍ እንዲሁም መሰረታዊ የስነ-ልቦና ድጋፍና ሪፈራል አገልግሎቶችን ለመስጠት ፈቃደኛ ሠራተኞችን ለማሠልጠን ያደረገው ተነሳሽነት ነበር።

በወረዳ ደረጃ፣ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የአካል ጉዳተኛ ታዳጊዎችንና ህጻናትን ጨምሮ አካል ጉዳተኞችን የሚደግፍ ክፍል አለው፤ በተግባር ግን ሚናው ችግር ያለባቸውን በቁጥር መረጃ በመሰብሰብና ደጋፊ መሳሪያዎችን በማቅረብ ብቻ የተገደበ ነው። የስነልቦናና ማህበራዊ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስፈልግ ተገቢ የሰው ኃይል እጥረት አለበት።

# 5 ድምጽና ውሳኔ ሰጪነት

## 5.1 መግቢያ

የታዳጊዎች የድምፅና ውሳኔ ሰጪነት ተደራሽነት፣ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ከእድሜያቸው ጋር አግባብነት ያላቸውን መረጃዎችና ቴክኖሎጂን የማግኘት ችሎታና የራሳቸውን ሕይወት፣ ቤተሰቦቻቸውን፣ መማሪያ ክፍሎቻቸውንና ማህበረሰቦቻቸውን በሚቀይሩ ውሳኔዎች ላይ ትርጉም ባለው መልኩ የመሳተፍ ችሎታ የደህንነታቸው ወሳኝ አካል ነው። በኢትዮጵያ የዕድሜ እርከኖች ታዳጊዎችን ንቁ የኢኮኖሚ ወኪሎች አድርገው ሲመድቧቸው በተመሳሳይ ደግሞ እንዲሁ ለአዋቂዎች እንዲታዘዙ ያደርጓቸዋል (Bevan and Pankhurst, 2007)። ሆኖም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አንዳንድ ታዳጊዎች (በተለይም ወንዶችና በዕድሜ ከፍ ያሉ፣ በከተሞች ውስጥ የሚኖሩና የተሻለ ትምህርት ደረጃ ያላቸው) የራሳቸውን ግቦች ለማስቀመጥና ህይወታቸውን በሚቀይሩ ውሳኔዎች ውስጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት እየፈለጉ ነው (Jones et al., 2014a; 2016c; 2017)። ለምሳሌ ጆንስና ጓደኞቹ (Jones et al., 2017)፣ አንዳንድ ታዳጊዎች ወላጆቻቸው ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ የማይፈቅዱላቸው ከሆነ ለባለሥልጣናት ሪፖርት እያደረጉ መሆናቸውን፣ እና አንዳንድ ልጃገረዶችም በቤተሰብ የተመቻቹ ጋብቻዎችን አንቀበልም እያሉ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። (በተጨማሪም Camfield and Tafere, 2011; Tefera et al., 2013; Mjaaland, 2018 ይመልከቱ)። የተሻለ የትምህርት ተደራሽነት፣ በታዳጊዎች ክለቦች ውስጥ የመሳተፍ ዕድሎችና አርአያ የሚሆኑ ሰዎች ጋር የመገናኘት አጋጣሚ የለውጡ አነሳሾች ይመስላሉ (CEDAW, 2010; Jones et al., 2016c; 2017)።

ምንም እንኳን እነዚህ ለውጦች ቢኖሩም፣ ልጃገረዶች ከድምፅና ውሳኔ ሰጪነት ተደራሽነት አንፃር ከወንዶች ጋር ሲነፃፀሩ በከፍተኛ ደረጃ ተጎጂ ሆነው ቀጥለዋል። ለእውነተኛ ደህንነታቸው ከመፍራት የተነሳና የቤተሰብ ክብር በሴት ልጅ የግብረስጋ ንጽህና ላይ በሚያተኩረው ማህበራዊ ደንብ የተነሳ በእንቅስቃሴያቸው ላይ የበለጠ ገደቦች አሉባቸው። በተጨማሪም ልጃገረዶች ከወንዶች ልጆች ይልቅ መረጃ እና ዲጂታል ቴክኖሎጂ የማግኘት ዕድላቸው አነስተኛ ነው። ጊዜያቸውን እንዴት እንደሚያሳልፉ (ለምሳሌ ትምህርታቸውን በማጥናትና የቤት ውስጥ ስራዎችን በመስራት)፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ፣ እና መቼ ማግባት እንዳለባቸው ከወንዶች ይልቅ ጥቂት ውሳኔዎችን እንዲሰጡ ተደርገው ነው ያደጉት (CRS, 2013; Mjaaland, 2018)። በተጨማሪም ምንም እንኳን ብዙውን ጊዜ የየአካባቢው ማህበራዊና ባህላዊ መለያዎች ቁልፍ አካል ቢሆኑም ታዳጊ ልጃገረዶች በሃይማኖታዊ ተቋማት ውስጥ ከመሳተፍ እንደሚገለሉ ጆንስና ጓደኞቹ (Jones et al., 2017) ይገልጻሉ።

## 5.2 የመንቀሳቀስና ምቹ ቦታዎች ተደራሽነት

የእኛ ግኝት እንደሚያሳየው በጣም ብዙ ወጣቶች (92%) ቢያንስ ወደ አንድ ቦታ ለመሄድ ፈቃድ መጠየቅ አለባቸው። በአነስተኛው የዕድሜ ክልል ውስጥ ባሉት መካከል የጾታ ክፍተት ቢኖርም (ሴት ልጆች 7% ያህል ፈቃድ መጠየቅ ሲኖርባቸው)፣ በከፍተኛው የዕድሜ ክል ውስጥ ባሉት መካከል ወደ 37% ከፍ ብሏል። ይህ ግኝት ቀደም ካሉ ጥናቶች ጋር አብሮ የሚሄድ ሲሆን ይህም በልጃገረዶች ላይ የሚደረጉ ገደቦች ዕድሜያቸው ከፍ እያለ ሲሄድ የሚጨምሩና በወንዶች ላይ ደግሞ እየቀነሰ የመሄድ አዝማሚያ አላቸው። እንዲሁም በብዙ ሁኔታዎች፣ ያገቡ ልጃገረዶች በጣም በጥብቅ ቁጥጥር ውስጥ የሚገኙ ናቸው (Tefera et al., 2013; Jones et al., 2014a; 2014b; 2016b; 2016c; 2017; Chuta, 2017; Pankhurst et al., 2018)። ከማህበረሰብ ሐ፣ ደቡብ ጎንደር፣ የ12 ዓመት ልጃገረድ እንደገለጸቸው ፤ "ወንዶች ልጆች ወደ ፈለጉት ቦታ ሁሉ መሄድ ይችላሉ፣ ወደ ሰሌሜያም [2 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወዳለቸው] ይሄዳሉ። ነገር ግን እንደ እኔ ሁልጊዜ በቤት ውስጥ የሚቆዩ ልጃገረዶች አሉ።›› ከማህበረሰብ መ አንዲት ባለትዳር የ12 ዓመት ያገባች ልጃገረድ ባለትዳር ልጃገረዶችን በተመለከተ ጫናዎቹ አሁንም ደበልጥ ጠንካራ መሆናቸውን እንዲህ ስትል ታብራራለች፡ ‹‹ወደ እናቴ ቤተክርስቲያን ሄጄ እንድሄድ ተፈቅዶልኛል ። ያልተፈቀደለኝ መንደር ነው… ወደ ጓደኞቼ ቤት መሄድ አልችልም… ሐሜተኞች ‹ያገባች ሴት ከቤት ከወጣች ዓላማው ሌላ ነገር ነው› ይላሉ።›› ለሙሽራ ከቤት እንድትወጣና ቤቷን ለቃ እንድትሄድ አይፈቀድም። ይህ ግኝት እንዲሁ ከ15-19 ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙት ባለትዳሮች 40 በመቶ ያህሉ ባሎቻቸው በማንኛውም ጊዜ የት እንደሚገኙ ማወቅ አለባቸው ከሚለው የኢትዮጵያ የስነህዝብና ጤና የቅርብ ጊዜ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ነው (CSA and ICF, 2017)።

በከተማ እና በገጠር ታዳጊዎች መካከል ትንሽ ግን ጉልህ ልዩነት አለ፤ የከተማ ልጆች በገጠር ካሉት ይልቅ የበለጠ የተገደቡ ናቸው፡ ፡ በደብረ ታቦር ከተማ የምትኖር አንዲት የ 15 ዓመት ልጃገረድ

> ወደ እናቴ ቤተክርስቲያን እንድሄድ ተፈቅዶልኛል። ያልተፈቀደልኝ መንደር ነው… ወደ ጓደኞቼ ቤት መሄድ አልችልም፡ ፡ ሐሜተኞች፣ "ያገባች ሴት ከቤት ከወጣች ዓላማው ሌላ ነገር ነው" ይላሉ።
>
> (አንዲት ያገባች የ12 ዓመት ልጃገረድ፣ ማህበረሰብ መ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ኢትዮጵያ)


ታዳጊ ወንድ ልጅ፣ ድሬዳዋ © ናታሊ በርትራምስ/ ጌጅ 2019

እንዳለቸው፣ ‹‹ወደ ቤተክርስቲያንና አንዳንድ ጊዜም እናቴ ስለምታውቃት ወደ ጓደኛዬ ቤት እሄዳለሁ፡፡ ከቤተክርስቲያንና ከጓደኛዬ ቤት ውጪ ሌላ ቦታ እንድትሄድ እናቴን ጠይቄያት አላውቅም፡፡ ከእነዚህ ቦታዎች ውጪ አንድሄድ የምትፈቅድልኝ አይመስለኝም…. ወላጆቼ እንደ ሌሎች መጥፎ ጠባይ ያላቸው ልጃገረዶች ከወንዶች ጋር ወደ ከተማ ትሄድ ይሆናል ብለው ይጨነቃሉ፡፡›› በተጨማሪም ግኝቶቻችን በክልሎች የገጠር አካባቢዎች ውስጥ ጉልህ ልዩነት እንዳለ ይጠቁማሉ፡፡ ይኸውም፣ በአፋር ያሉ ታዳጊዎች 74% ፈቃድ የሚፈልጉ ሲሆን፣ በደቡብ ጎንደር ከሚኖሩት አቻዎቻቸው (95%) ወይም ከምስራቅ ሀረርጌ (91%) ካሉት ሲነጻጸር ፈቃድ የመፈለግ አዝማሚያቸው አነስተኛ ነው፡፡

አብዛኛዎቹ ወጣት ታዳጊዎች (92%) ቀን ቀን ሲሆን በአካባቢያቸው ደህንነት እንደሚሰማቸውና 96% የሚሆኑት ደግሞ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ደህንነት እንደሚሰማቸው ግን 44% የሚሆኑት ብቻ በምሽት ሰዓት ደህንነት እንደሚሰማቸው ተናግረዋል፡፡ የደህንነት ስሜት ከወንዶች ልጆች ይልቅ በልጃገረዶች ዘንድ በጣም ዝቅተኛ ሲሆን እድሜያቸው ሲጨምር የባሰ ይሆናል፡፡ ይኸውም፣ በምሽት ወቅት ደህንነት የሚሰማቸው ወጣት ታዳጊዎች ወንዶቹ 53% የሚሆኑት ሲሆኑ ልጃገረዶቹ ደግሞ 34% የሚሆኑት ናቸው፡፡ በዕድሜ ከፍ ካሉት ታዳጊዎች መካከል ሲነጻጸሩ ወንዶቹ 68% ሲሆኑ ሴቶቹ ደግሞ 38% የሚሆኑት ናቸው፡፡ የአይነታዊ ምርምር ግኝቶቻችን የሚያመለክቱት በከተሞች አካባቢ በወጣት ክለቦች ወይም ማዕከላት ውስን መሆን ምክንያት ለወጣቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ ስፍራዎች በጣም የተገደበ ሲሆን ክለቦች ባሉበት ቦታም እንኳ ዝቅተኛ አቅርቦት ያለባቸው ናቸው፡፡ በተጨማሪም ጨዋታዎቹና መሳሪያዎቹ ልጃገረዶችን የማያካትቱና በአጠቃላይ ለወንዶች ተብለው የተዘጋጁ ናቸው (ለምሳሌ፣ ፑል፣ የጠረጴዛ ኳስ፣ የቅርጫት ኳስ - ሁሉም ‹የወንዶች› ጨዋታዎች ተደርገው የሚታዩ ናቸው)፡፡

## 5.3 ዕድሜ-ተኮር መረጃ እና የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደራሽነት

የታዳጊዎች የመረጃና የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደራሽነት በጾታ፣ በዕድሜና በሚኖሩበት ቦታ ይለያያል፡፡ በገጠር አካባቢዎች ለሚኖሩ ወጣት ልጃገረዶች ተደራሽነቱ በጣም የከፋ ሲሆን በከተሞች አካባቢ ለሚኖሩ በዕድሜ ከፍ ላሉ ወንዶች ልጆች ግን የተሻለ ነው (Jones et al., 2017)፡፡ ዝቅተኛ ገቢ ባለበት የገጠር አካባቢ በአጠቃላይ የመገናኛ ዘዴ ተደራሽነት አሁንም ውስን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ስነህዝብና ጤና የቅርብ ጊዜ ጥናት መሠረት ዕድሜያቸው ከ15-19 ከሆኑ ታዳጊዎች ውስጥ 29% የሚሆኑት ልጃገረዶችና 42% የሚሆኑት ወንድ አቻዎቻቸው ብቻ የሞባይል ስልክ ያላቸው ሲሆን ኢንተርኔት የተጠቀሙት 7% ልጃገረዶችና 15% ወንዶች ልጆች ብቻ ናቸው (CSA and ICF, 2017)፡፡ የመገናኛ ዘዎዎቹ ተደራሽነት በዕድሜ ደረጃ የሚለያይ መሆኑን ግኝቶቻችን ይጠቁማሉ፡፡ በከተሞች አካባቢ በዕድሜ ከፍ ካሉ ታዳጊዎች መካከል ግማሽ ያህሉ (43%) የግል ስልክ አላቸው፤ ነገር ግን ጉልህ የሆነ የጾታ ልዩነት ያለ ሲሆን ልጃገረዶቹ ስልክ የማግኘት ዕድላቸው በ17% ያነሰ ነው (በንጽጽር ስልክ ያላቸው ወንዶች ልጆች 47% ሲሆኑ ልጃገረዶቹ ደግሞ 39% ናቸው)፡፡ በአነስተኛው የዕድሜ ክልል ለሚገኙ ታዳጊዎች የስልክ ተደራሽነት ዝቅተኛ (3%) ሲሆን ወንዶች ልጆች የልጃገረዶቹን ሁለት እጥፍ ስልክ የማግኘት እድል

አላቸው። በሚገርም ሁኔታ፣ በአፋር ውስጥ ያሉ ታዳጊዎች በሌሎች ክልሎች ካሉ አቻዎቻቸው ስስልክ የበለጠ ተደራሽ ናቸው (ንጽጽሩ የአፋር 5%፣ ደቡብ ጎንደር 1%፣ እና በምሥራቅ ሐረርጌ 5% ነው)። ይህ የሆነው ምናልባትም ለእንስሳት መኖ ፍለጋ ረጅም ርቀት መጓዝ ስለባቸው ይሆናል።

በአነስተኛው የእድሜ ክልል የሚገኙ ታዳጊዎች ኢንተርኔት በሚፈልጉበት ሰዓት በከተማም ሆነ በገጠር ተደራሽ አይደለም። ምንም እንኳን የጾታ ልዩነቱ ለሴቶች የመድረስ እድሉ 50% አነስተኛ ቢሆንም በከተሞች ላሉት በዕድሜ ከፍ ላሉ ታዳጊዎች እስከ 36% ደርሷል። የተሻለ የቴክኖሎጂ ተደራሽነት ጥቅማጥቅሞችን እንደሚያስገኝ ሁሉ ጉዳቶችም አሉት። አይነታዊ የምርምር ግኝቶቻችን እንደሚያሳዩት ስለታዳጊዎች የመረጃ ቴክኖሎጂዎች ተደራሽነት ያለው አመለካከት የተደባለቀ ነው። ለምሳሌ በማህበረሰብ ለ (አፋር)፣ አንድ ቁልፍ የመረጃ ሰጭ ሞባይል ስልኮች የታዳጊዎችን የዕውቀት አድማስ እያሰፉ ስላሉበት ሁኔታ ሲገልጹ፣ ‹‹ታዳጊ በነበርኩበት ጊዜ ስለ መንግስት፣ ልማት፣ መብቶች፣ ትምህርት፣ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም … አሁን ግን ታዳጊዎች ስለ ብዙ ነገሮች ያውቃሉ። በክልላችንና በሀገራችን ውስጥ እየተከናወነ ስላለው ነገር ይናገራሉ፣ በሞባይል ስልኮቻቸው የተለያዩ ዜናዎችን ይሰማሉ፣ እንዲሁም ስለ ከተሞች ያውቃሉ፣ ዘፈኖችን ሞባይላቸው ላይ ቀድተው ያዳምጣሉ።››

ሆኖም፣ እያደገ የመጣው የዲጂታል ቴክኖሎጂ፣ በተለይም የኢንተርኔት ተጠቃሚነት በታዳጊዎችን ላይ ስለሚያስከትለው አደጋ (የማጭበርበር፣ የመበዝበዝ ወይም ለአሉታዊ ባህሪዎች እና ወሲባዊ ወይም የአመጻ ይዘት ላላቸው የመጋለጥ) በማህበረሰቡ መሪዎችና ወላጆች ዘንድ ከፍተኛ ስጋት አለ። በሌላ በኩልም ደግሞ ወላጆች በልጆቻቸው ሕይወት ላይ ያላቸውን ተፅእኖ እየቀነሰ ነው። በድሬዳዋ ውስጥ አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንደገለጹት፣ ‹‹ብዙ ቤተሰቦች እነዚህን ዘመናዊ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል እውቀቱ የላቸውም…. ታዳጊዎች በቀላሉና ያለአግባብ የሚጠቀሙባቸው ብሎም ደህንነታቸው ላልተጠበቁ ድረገጾች ሊያጋልጧቸው የሚችሉ መተግበሪያዎች አሉ። በማህበራዊ ሚዲያ በመጠቀም ከብዙ ቡድኖች ጋር በቀላሉ መወያየትና በባሕርያቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የወሲብ ፊልሞችን ጨምሮ መጥፎ ይዘት ያላቸውን ቪዲዮዎችን መጋራት ይችላሉ።›› በምሥራቅ ሀረርጌ አንድ የሃይማኖት መሪ በበኩላቸው፣ ‹‹የመገናኛ ተክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆናቸው ልጆች ከወላጆቻቸው ቁጥጥር ውጭ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። አዕምሯቸው በዘፈን አለመጠን ተበርዟል … እናም የአባቶቻቸውንና የእናቶቻቸውን ምክር እንዳይቀበሉ ያደርጋቸዋል›› ሲሉ አሳስበዋል።

## 5.4 ድምጽና ውሳኔ አሰጣጥ በቤተሰብና በማህበረሰብ ውስጥ

ጥናቶች እንደሚያሳዩት የታዳጊዎች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ በተለይም ለወንዶች ልጆች፣ በዕድሜ ከፍ ላሉ ታዳጊዎችና የተሻለ የትምህርት ደረጃ ላላቸው ወይም በከተሞች ለሚኖሩ ወጣቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው (Jones et al., 2014a; 2016b; 2017; GHE, 2105; CSA and ICF, 2017)። በጥናታችን መሠረት በቤተሰብ ውስጥ በድምጽና በውሳኔ አሰጣጥ ረገድ ከ0–6 በተቀመጠው መለኪያ የታዳጊዎቹ አማካይ ውጤት 2.79 ሲሆን ይህም ታዳጊዎች በቤተሰባቸው ውስጥ ያላቸው ድምጽ መካከለኛ ደረጃ እንደሆነ የሚሰማቸው መሆኑን ያመላክታል።

ልጃገረዶች እስከሚያገቡ ድረስ የወላጆቻቸውን ከዚያ በኋላም የባለቤታቸውን ፍላጎቶች እንዲከተሉ ተደርገው ያደጉ መሆናቸውን ከሚያሳዩ ጥናታዊ ጽሑፎች (Camfield and Tafere, 2011; CRS, 2013; Tefera et al., 2013; Jones et al., 2014a; 2014b; 2016b; 2016c; 2017; Pankhurst et al., 2018) ጋር በሚስማማ ሁኔታ፣ በወጣት ታዳጊዎች መካከል በቤት ውስጥ ውሳኔ ሰጪነት መጠነኛ የጾታ ልዩነት ያለ ሲሆን የልጃገረዶች ከወጣት ወንዶች ጋር ሲነፃፀር 7 በመቶ ያነሰ ነበር። ለምሳሌ ከማህበረሰብ ረ፣ ደቡብ ጎንደር፣ የ 12 ዓመት ወጣት እንደገለጸችው፣ ‹‹ልጃገረዶች ከወንዶች ልጆች ይልቅ በታዛዥነታቸው የሚታወቁ ሲሆን በቤተሰባቸው ውስጥ ያላቸው ተሰሚነት አነስተኛ ነው። እናቴ የማትሠራቸውን ሥራዎች ሁሉ እሰራለሁ። አድርጊ ያለችኝን ሁሉ አደርጋለሁ።›› ቁልፍ የባህላዊ ድርጊት አመላካች ከሆኑት የሴት ልጅ ግርዛትና ያለዕድሜ ጋብቻ አንጻር የሴቶች ተሰሚነትና ውሳኔ ሰጪነት ወሰን የተገደበ መሆኑን በተለይ የሴቶች ግርዛት በታዳጊነት ዕድሜና ከጋብቻ በፊት በሚከናወንበት በማህበረሰብ ቀ (ምስራቅ ሃረርጌ) አንድ ቁልፍ የመረጃ ሰጪ እንዳመለከቱት፣ ‹‹ልጅቷ አይሆንም ማለት ትችላለች ግን እናቷ በጭራሽ አትቀበለውም፣ ምክንያቱም ሴት ልጅ ሳትገረዝ ካገባች በባህላችን እንደ ትልቅ ውርደት ይቆጠራል። ስለዚህ ሴት ልጆቻቸውን ሳይገረዙ አይደተዋቸውም።››

እንዲሁም በየክልሎቹ ጉልህ የሆኑ ልዩነቶች ነበሩ። ለምሳሌ፣ በአፋር ያሉ ታዳጊዎች ውሳኔ ሰጪነት በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይገልጻሉ (ንጽጽሩ በአፋር 2.02፣ በምስራቅ ሐረርጌ 2.55 እና በጎንደር 3.21)። ይህ ምናልባትም የጎሳ ህጎች የታዳጊዎችን ባህርያት በመቅረጽ የሚጫወቱትን ጠንካራ ሚና ያንፀባርቃል። ከማህበረሰብ ሀ (ዞን 5፣ አፋር)፣ የ12 ዓመት ያገባች ልጃገረድ እንዳብራራችው፣ ‹‹ቤተሰቦቼ ፍየሎች እንዳሰማራ ነገሩኝ በዚያው ትምህርቴን አቋረጥሁ። በጊዜው ወደ ትምህርት ቤት መሄድ እንደምፈልግ ነገርኳቸው እናም ለዚያ ቀን ፍየሎችን መንጋ እንዳሰማራ ነገረውኝ በዚያው አቋርጬው ቀረሁ።›› ሆኖም በዞን 5 (አፋር) እና በምስራቅ ሐረርጌ በአከባቢያዊ ባህል ታዳጊዎች ከወላጆቻቸው ቁጥጥር ውጪ በባህላዊ ጭፈራዎች (ሳዳ በዞን 5 እና ሸጎዬ በምስራቅ ሃረርጌ) ጊዜያቸውን እንዲያሳልፉ የሚያስችሉ አስፈላጊ የደህንነት መቆጣጠሪያዎች መሆናቸውን ማመላከቱ

**አይሆንም ማለት ትችላለች ግን እናቷ በጭራሽ አትቀበለውም ምክንያቱም ሴት ልጅ ሳትገረዝ ካገባች በባህላችን እንደ ትልቅ ውርደት ይቆጠራል። ስለዚህ ሴት ልጆቻቸውን ሳይገረዙ አይደተዋቸውም።**

(ቁልፍ የመረጃ ሰጪ፣ ማህበረሰብ ቀ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ ኢትዮጵያ)

ጠቃሚ ነው። እነዚህ የአዳር ጭፈራዎች ለሁለቱም ጾታዎች ከቅድመ ታዳጊነት ዕድሜ ጀምሮ እንዲቀላቀሉ የተፈቀደላቸው ሲሆን የማህበረሰቡ አካል እንዲሆኑ ከፍተኛ ነፃነት ያስገኙላቸዋል፡ ፡ ጭፈራው የወላጅ ወይም የማህበረሰብ መሪ ቁጥጥር የሌለበት፣ ብዙውን ጊዜ የፍቅር አጋሮችን፣ በምስራቅ ሀረርጌ የትዳር አጋሮችን፣ የሚያገኙበት ቦታ ነው። ከማህበረሰብ ቸ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ የሴቶች ክለብ አስተባባሪ እንደተናገሩት፣ ‹‹በዚህ አካባቢ ልጃገረዶች በምሽት የሸጎዬ ባህላዊ ዘፈን ተጫውተው በጠዋት ቤተሰቦቻቸው ሳያዩአቸው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። ይህንየሚያከናውኑት ማንንም ሳያማክሩ ነው። አንድት ልጃገረድ ሸጎዬ ብትጫወት አባቷና እናቷ አይቃወሟትም፤ ምክንያቱም ልጅቷ ለማድረግ ወስኖለች። ልጅቷ አንዴ የሸጎዬ ባህል መጫወት ከጀመረች ማቆምዋን ማቆም ከባድ ነው… ማህበረሰቡ የተማረ ስላልሆነ እንደ መጥፎ ባህል አይቆጥሩትም።››

## 5.5 የዜግነት ተሳትፎ

መሰረታዊ መረጃችን በሚሰበሰብበት ወቅት (በ2017 መጨረሻና በ2018 መጀመሪያ) የለውጥ ፖለቲካው በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ ሹመት መካሄድ የጀመረበት ስለነበረ መረጃ መሰብሰብ የማይታሰብ ነበር። በዚህ ወቅት በመላ ሀገሪቱ፣ እኛ ምርምር የምናደርግባቸውን ዞኖችን ጨምሮ፣ ጎንደር እና ምስራቅ ሀረርጌ በተካሄዱ የተቃውሞ ሰልፎችና ከፖሊሶችና ወታደሮች ጋር በተፈጠሩ ግጭቶች በጣም ተጎድተዋል። በተጨማሪም፣ መጠነ ሰፊ የሆነ የነዋሪዎች መፈናቀል የነበረ ሲሆን ከሶማሌ ወደ ኦሮሚያ ክልል ቢያንስ ግማሽ ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ተፈናቅለዋል፡ ፡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመብቶች ላይ የተመሠረተ ውይይቶችን እንዳያደርጉ ለመከልከል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የዜግነት ምዝገባ ሕጎች በጥብቅ እየተተገበሩ ነበር።

ከዚህ አንፃር የአይነታዊ ምርምር መረጃዎቻችን እንደሚያሳዩት ታዳጊዎች ደህንነቱ ለተጠበቀ የዜግነት ተሳትፎ በጣም የተገደቡ ዕድሎች የነበራቸው ሲሆን፣ በቀበሌ ስብሰባዎች ውስጥ ምንም አስተያየት የማይሰጡና በወቅቱ በነበረው ውጥረት የተነሳ ስለነበራቸው ተሳትፎም ሆነ ስለአመለካከታቸው ለመወያየት ፈቃደኛ አልነበሩም4 ። የሰማነው ነገር ቢኖር በከተማ ውስጥ ማህበራዊ ሚዲያዎች ታዳጊዎችና ወጣቶች በሰላማዊ ሰልፎችና በመላዉ የፖለቲካ አመፅ ውስጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ስላደረጉበት ሁኔታ በአካባቢው የመንግሥት ቁልፍ የመረጃ ሰጭዎች አማካይነት ነበር። ለምሳሌ በደብረ ታቦር ውስጥ የአንድ ቁልፍ መረጃ ሰጭ አይታ እንደሚከተለው ነበር። ‹‹የታዳጊዎች የኢንተርኔት ተደራሽ መሆን በከተሞች አካባቢ በፖለቲካ ጉዳዮች የበለጠ ተሳታፊ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል… የተወሰኑት መረጃዎች ታዳጊዎች በአመጾች ውስጥ እንዲሳተፉም ያሳስቷቸዋል… እንዲሁም ህዝቡ የመንግስትን ህጎች እንዲጥሱ ያነሳሳሉ… ወንዶቹም ሴቶቹም ታዳጊዎች በአመጹ ውስጥ ተሳትፈዋል፣ ነገር ግን አብዛኛዎቹ ቁልፍ ተዋናዮች ወንዶች ነበሩ። ከዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች አንዱ በአካባቢው የወጣቶች ሥራ አጥነት መጠን መጨመር ነበር።››

ሆኖም በምስራቅ ሐረርጌ በተከሰተው አለመረጋጋት ምክንያት በተለይም ከሶማሌ ክልል በገፍ የተፈናቀሉ ሰዎች የሚገኙበት በመሆኑ ምክንያት በአካባቢው የነበሩ አመራሮች በጣም ውስን በመሆኑበት ሁኔታ፣ በዕድሜ ከፍ ያሉ ታዳጊዎች (በተለይም ወንዶች) ቄሮ ተብሎ የሚጠራዉን የወጣቶች ቡድን በማደራጀት የአካባቢያቸው ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅና በተቻለ መጠን ተፈናቅለው የነበሩ ቤተሰቦችን ለመደገፍ ይንቀሳቀሱ ነበር። በማኅበረሰብ ቀ አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጭ እንደገለጹት፣ ‹‹ወጣቶች የተፈናቀሉ ሰዎችን እየረዱ ነው እናም በድንበር ግጭት ውስጥ ላሉት ሰዎች ሎጂስቲክስ ለማቅረብ እየሰሩ ነው። በእኛ ቀበሌ ሁሉም ወጣቶች ያላቸውን እያበረከቱ ነው - ገንዘብ ሊሆን ይችላል፣ እህል ሊሆን ይችላል - ለተፈናቃዮች ይሰጣሉ። በተጨማሪም በድንበር አካባቢ ከሶማሌዎቹ [በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ከሚገኙ የሶማሌ ተወላጆች] ጋር ለሚዋጉ ሰዎች ምግብ እየሰጡ ናቸው።››

## 5.6 አርአያዎች

በኢትዮጵያ ታዳጊዎች የመጀመሪያ ትውልድ ተማሪዎች በሆኑበት ሁኔታ ታዳጊዎችን በተለይም ልጃገረዶችን የራሳቸው የወደፊት ራዕይ እንዲኖራቸው ለማገዝ አርአያ የሚሆኑ ሰዎች ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ (Jones et al., 2014a; 2014b; 2016b; 2016c; 2017)። የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ አስተማሪዎችና የመንግሥት ባለሥልጣናት በትምህርት ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስና ጋብቻን እስከ ጎልማሳነት ዕድሜ ድረስ ማዘግየት ያለውን ጠቀሜታ ለወጣቶችና ለቤተሰቦቻቸው ሊያስረዱ እንደሚችሉ ጥናቶች ያሳያሉ (ibid.)። የእኛ ግኝቶች እንደሚያሳዩት አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት (36%) ታዳጊዎች ብቻ አርአያ የሚሆናቸውን የለዩ ሲሆን፣ አርአያ ያላቸው ልጃገረዶች (33%) ከወንዶቹ አቻዎቻቸው (38%) ሲነጻጸሩ ጥቂት ናቸው። ይህ አኃዝ በታላላቆቹ ታዳጊዎች ዘንድ እጥፍ ያህል ሲሆን፣ 66% የሚሆኑት በዕድሜ ከፍ ያሉ የከተማ ታዳጊዎች አርአያቸውን መለየት ችለዋል።

የአይነታዊ ምርምር ግኝታችን በተጨማሪ እንዳመለከተው በከተማ የሚኖሩ ታዳጊዎች በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት ለየት ያሉ አዳዲስ አርአያ ሞዴሎችን ለምሳሌ፣ የባህል ልብስ ዲዛይነሮችንና ሳይንቲስቶችን ማግኘት ሲችሉ፣ በገጠራማ አካባቢዎች ያሉ ታዳጊዎች ደግሞ ባህላዊ በሆነው መንገድ ታላላቆቻቸውን የማየት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። ለምሳሌ፣ በማህበረሰብ ለ፣ ዞን 5 (አፋር)፣ የ10 ዓመት ልጅ በአፅንኦት ሲገልጽ፣ ‹‹እኔ እንደ ታላላቆቼ መሆን እፈልጋለሁ። ልክ እንደ አባቴ መሆን እፈልጋለሁ፣ አባት መሆን እፈልጋለሁ፣ ብዙ ከብቶች እንዲኖሩኝ፣ ጨቤና ጠመንጃ እንዲሁም

4 የታዳጊዎች ፖለቲካዊ ተሳትፎ ከጊዜ ጊዜ እየተለወጠ መሆኑንና በፖለቲካዊ አለመረጋጋት ወቀትም ቢሆን በታዳጊዎች መረዳትና ተሳትፎ ዙሪያ ያላቸው ግንዛቤ እየጨመረ መሄዱን አሁን ከአንድ አመት በኋላ በተመሳሳይ የጥናት ቦታዎች ላይ በታላላቅ ታዳጊዎች ላይ እየተሰሩ ያሉ አሳታፊ ጥናቶቻችን አመላክተዋል። ይሁን እንጅ የዚህ ሪፖርት ዋና ትኩረታችን በመነሻ ጥናት መረጃ ስብሰባ ላይ የነበረው ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመሰረተ ነው።

> “ከዩኒቨርሲቲ የተመረቀ ስራ ካልተቀጠረ ጊዜያችንን ለምን እናባክናለን?” በማለት አብዛኞቹ ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ። በእኛ አካባቢ አንድ የተማረ ሰው ገበሬ ከሆነ እንደ ውርደት ይቆጠራል ... ሁሉም ተማሪዎች የሚማሩት የመንግስት ሰራተኛ ለመሆን ነው፤ ስለሆነም ስራ የሌላቸውን ወጣቶች ሲመለከቱ ተስፋ ይቆርጣሉ።
>
> (ቁልፍ የመረጃ ሰጪ፣ ማህበረሰብ ቀ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ ኢትዮጵያ)

ገንዘብ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ›› ብሏል። በሌላ በኩል በማህበረሰብ ሀ፣ የእድሜ አቻው የሆነች የ11 ዓመት ያገባች ልጃገረድ ስታብራራ፣ ‹‹በሃይማኖታቸው ጠንካራ እንደሆኑ ሴቶች መሆንና ሌሎችን ማስተማር እፈልጋለሁ። በአለባበሳቸው የተለዩ ናቸው፤ እነዚያ ሴቶች ለጋብቻ ታማኝ ናቸው እናም ይጸልያሉ ቁርአንም ይማራሉ፡፡ ባለቤቴ የሃይማኖት ሰው ነው። በሃይማኖታቸው ጠንካራ የሆኑ ሴቶች ዘመዶች አሉኝ። ራሳቸውን ስለሚሸፍኑ መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉ።››

እዚህ ላይ የኛ ግኝቶች እንደሚጠቁሙት አርአያ የሚሆኑ ሰዎች መጥፎ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ መሆናቸውንም መረዳት ያስፈልጋል። በአንዳንድ የምርምር ማህበረሰቦቻችን ውስጥ፣ ታዳጊዎች ታላላቆቻቸው የጿከሙበት ትምህርታቸው ህይወታቸውን ሊቀይርላቸው አለመቻሉን ሲመለከቱ በትምህርታቸውና በወደፊት ስራ ማግኘታቸው ተስፋ እንደቆረጡ ገልፀዋል። ከምሥራቅ ሀረርጌ ማህበረሰብ ቀ፣ አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንደገለፁት፣ ‹‹‹ከዩኒቨርሲቲ የተመረቀ ስራ ካልተቀጠረ ጊዜያችንን ለምን እናባክናለን?› በማለት አብዛኞቹ ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ። በእኛ አካባቢ አንድ የተማረ ሰው ገበሬ ከሆነ እንደ ውርደት ይቆጠራል ... ሁሉም ተማሪዎች የሚማሩት የመንግስት ሰራተኛ ለመሆን ነው፤ ስለሆነም ስራ የሌላቸውን ወጣቶች ሲመለከቱ ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡›› ወጣቶች፣ ካሁን በፊት ተሳክቶላቸው በስደት ወደ ሌላ ሀገር በሄዱ ታዳጊዎች ይታለላሉ፣ ነገርግን በስደት ስለሚያጋጥማቸው አደጋ ትክክለኛውን መረጃ አይሰጧቸውም።

## 5.7 የለውጥ ስትራቴጂዎች

በምርምር ጣቢያዎቻችን የታዳጊዎችን ድምጽና ውሳኔ ሰጪነት ከፍ ለማድረግ ያለሙ በርካታ ተነሳሽነቶች አሉ፤ ነገር ግን ደግሞ ለታዳጊዎችና ለአዋቂዎች አጠቃላይ መሻሻል የተሻሉ አገልግሎቶችና መርሃግብሮች ያስፈልጋሉ። የልጃገረዶች ክለቦች የሚሰሩባቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ እነዚህ ልጃገረዶች መብታቸውን እንዲገነዘቡና በራስ የመተማመን ስሜታቸውን እንዲያሻሽሉ የሚረዱ ጠቃሚ ስልቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እናም ታዳጊዎች ከአስተማሪዎቻቸው ጋር ሆነው የልጃገረዶችን ከትምህርት ማቋረጥና ያለዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል በርካታ ስራዎችን እየሰሩ መሆናቸውን ሰምተናል። ይህ ተስፋ ሰጪ ቢሆንም፣ የልጃገረዶች ክለቦች በአጠቃላይ ያልተሟሉና ከጎንደርና ከከተሞች ውጭ ያሉት ብዙውን ጊዜ በስም ብቻ ያሉ ናቸው። የትምህርት ቤት ፓርላማዎች ከትግበራ አንፃር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ንቁ እና ተነሳሽነት ባላቸው መምህራን የሚሰሩ እና የሚደገፉ ሲሆን፣ የታዳጊዎችን ድምጽና ውሳኔ ሰጪነት ለማሳደግ አስፈላጊ መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን በተግባር ከሚታየው የተለዩ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ያገኘነው ነገር፣ ተማሪዎች በመደበኛነት በወላጅ - መምህር - ተማሪ ማህበራት ውስጥ ተካትተዋል፡ ነገር ግን እነዚህ መዋቅሮች የታዳጊዎችን የድምጽና ውሳኔ ሰጪነት ከማሳደግ ይልቅ፣ በትምህርት ቤት ስላሉ የስነምግባር ደንቦች ጥሰት ላይ፣ በሕግ የተከለከውን አካላዊ ቅጣትን ጨምሮ፣ ቅጣቶችን መቅረጽ ላይ የበለጠ ትኩረት ያደርጋሉ።

ከትምህርት ቤቶች ውጪ ባሉ አካባቢዎች፣ ከተሞችን ጨምሮ የሚያስደንቅ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚመራ ታዳጊ ተኮር እንቅስቃሴዎችን አግኝተናል። ከዚህ በፊት የተሸለ ፕሮግራም ነበር፣ ነገር ግን እነዚህ ተነሳሽነቶች ተጠናቀዋል፤ ምናልባትም ከመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምዝገባ ሕግ አንፃር መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶች የሚያንጸባርቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለዕድሜ እኩዮች ማህበራዊ ግንኙነቶች ጥቂት እድሎች በዋነኝነት የቀረቡት በቤተክርስቲያን ድርጅቶች እና በተወሰነ መጠንም ቢሆን በመስጊዶች እንዲሁም በመንግስት የወጣት ማዕከላትና በስፖርት ክለቦች ነበር። ሆኖም የወጣት ማዕከላት ያልተሟሉ እንደሆኑና የስፖርት ክለቦች በዋነኝነት የተቋቋሙት ለወንዶች እንጂ ለሴቶች እንዳልሆለ ታዳጊዎች በተደጋጋሚ ተናግረዋል።

# 6 የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት

## 6.1 መግቢያ

ኢትዮጵያ በፍጥነት እያደጉ ካሉ የአፍሪካ ኢኮኖሚዎች አንዷ ስትሆን በ1995 61% የነበረውን የድህነት ምጣኔ በ2013 ወደ 26 በመቶ ቀንሳለች (UNDP, 2015)፡፡ ሆኖም ከባለዘርፈ ብዙ ድህነት አንፃር ከዓለማችን በጣም ድሃ ከሆኑት ሀገሮች መካከል አንዷ ናት (87%) (OPHI, 2017)፤ እንዲሁም በጣም የቅርብ ጊዜ በሆነው የሰው ልማት ማውጫ ላይ ከ 189 አገሮች 173ኛ ደረጃን ይዛለች (UNDP, 2018)፡፡ ምንም እንኳን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሕፃናት ድህነትና የድህነት ልዩነት ሁለቱም ቢቀንሱም (OPHI, 2017; Pankhurst et al., 2018)፣ ህጻናት በተለይ ተጎጂ ናቸው፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ የሕጻናት ጉልበት መጠን ከሚሰጡት አገራት መካከል አንዷ ነች፡፡ ከሁሉም ህጻናት እስከ ግማሽ የሚሆኑት በሆነ ዓይነት ሥራ ላይ ተሰማ ርተው ይገኛሉ (UNESCO, 2012)፡፡ ታዳጊዎች ብዙውን ጊዜ ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶችና ሀብቶች ብቻ ሳይሆን የስራ ዕድሎችም ጭምር እጥረት እያጋጠማቸው ነው፤ ይህ ደግሞ በተለይ በሴቶችና በወጣት ሴቶች ላይ የሚታይ ነው (Broussar and Tekleselassie, 2012; Yèhoué et al., 2013; Igbatayo and Babalola, 2014).

## 6.2 ኢኮኖሚያዊ ምኞቶች

ምንም እንኳን በዕድሜ ከፍ ያሉ ብዙ ታዳጊዎች በግብርና ስራ የተሰማሩ ቢሆኑም (CSA and ICF, 2017)፣ ብዙ ወጣቶችና ወላጆቻቸው ግብርናን ቋሚ የመተዳደሪያ አማራጭ አድርገው አይወስዱትም፡፡ በሕዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት የተከሰተው



Adolescent girl with tea, Oromia
© Nathalie Bertrams / GAGE 2019

የእርሻ መሬት እጥረት ከሌሎች ችግሮች ለምሳሌ የማዳበሪያ ዋጋ መጨመር፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የአፈር ለምነት ማጣት፣ እና ግብርና ኋላቀርና አድካሚ ነው ከሚል አሉታዊ አመለካከት ጋር ተዳምሮ ግብርና ካሁን ወዲያ ብዙ የገጠር ታዳጊዎችን የሚስብ አይመስልም (Tadele and Gella, 2012; Jones et al., 2014b; 2016c; 2017)። አሁን ላይ ያሉ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ይህ በልጃገረዶች የሚብስ ሲሆን፣ ወንዶች ልጆች በተለምዶ ግብርናውን እንደማያገኙት ሁሉ ልጃገረዶች ነጻነትን ለማግኘት መማርና ተቀጥሮ መስራት ያስፈልጋል ብለው ያምናሉ (Tadele and Gella, 2012; Jones et al., 2017 ይመልከቱ)።

የጌጅ ምርምር ግኝቶች እነዚህን አጠቃላይ አዝማሚያዎች ያረጋግጣሉ። በሦስቱም ክልሎች ሴት ልጆች አስተማሪ መሆን የሚፈልጉ ሲሆን የወንዶች ልጆች ምኞት ግን ይለያያል። በአማራና በኦሮሚያ አስተማሪና ሐኪም፣ በአፋር ደግሞ ደመወዝ ተከፋይ ባለሙያና ከብት ጠባቂ መሆን ይመኛሉ። አንዲት የ15 ዓመት ልጃገረድ፣ ከሰሚሮቢ፣ ዞን 5 (አፋር) እንዳብራራቻው: ‹‹ወላጆቻችን በተሰማሩበት በተመሳሳይ ስራ ውስጥ መሳተፍ አንፈልግም... ወላጆቻችን በየዕለቱ የጉልበት ሥራ እየሰሩ ነው፣ ያደክማቸዋል። የመንግሥት ሠራተኞች መሆን እንፈልጋለን።››

ብዙውን ጊዜ የታዳጊዎችን ምኞት ስለሚቀርጹ ወላጆች ለልጆቻቸው ያላቸውን ምኞት መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው (Favara, 2017)። ግኝቶቻችን እንደሚያሳዩት ወላጆች ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው ሲሆን፣ በጣም የሚመርጡት ልጆቻቸው ክህሎት ባለው የሙያ ዘርፍ ስራ እንዲኖራቸው ነው። ሆኖም አንዳንድ ጉልህ የሆኑ ክልላዊ ልዩነቶች አሉ። በዞን 5 (አፋር) ውስጥ 27.8% የሚሆኑት እናቶች 3.5% ከሚሆኑት በምስራቅ ሐረርጌና ከ1% በታች ከሚሆኑት በደቡብ ጎንደር ካሉት ጋር ሲነጻጸሩ፣ ታዳጊዎች የቤት እመቤት እንዲሆኑ ይፈልጋሉ። በዞን 5 የሚገኙ እናቶች ብዙውን ጊዜ ወንዶች ልጆቻቸው ደመወዝ ተከፋይ ባለሙያ (19.9%) ወይም ከብት ጠባቂ (18.5%) እንዲሆኑ ይፈልጋሉ፤ በምሥራቅ ሐረርጌ ግን ግማሽ ያህሉ (47.2%) የሚመኙት ወንድ ልጃቸው ዶክተር እንዲሆን ነው። በአማራ፣ የወላጆች ምኞት ወንዶች ልጆቻቸው ሐኪም (25.1%) እና ደመወዝ ተከፋይ ባለሙያዎች (20.3%) እንዲሆኑላቸው ነው።

የዳሰሳ ጥናት ግኝታችን በተጨማሪ ወላጆች ለልጆቻቸው መተዳደሪያ የሚመኙት ልጆቻቸው ቁልፍ የሕይወት ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ከሚጠብቁበት ዕድሜ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ያሳያል፡ ፡ እናቶች ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ልጆቻቸው በሃያዎቹ ዕድሜያቸው ውስጥ ቁልፍ የህይወት ለውጦች እንዲያመጡ ይጠብቃሉ፤ ይህም የከፍተኛ ትምህርትን ማጠናቀቅና በገንዘብ ረገድ ራስን መቻልን ያጠቃልላል።

## 6.3 ገበያ ተኮር ክህሎቶች

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም በማዳረስ ረገድ ጉልህ መሻሻል ቢኖርም፣ በዓለም ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 24 የሚደርሱ መሰረታዊ ክህሎት የሌላቸው ወጣቶች ከሚገኙባቸው አምስት አገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ነች (UNESCO, 2012)። ሀገሪቱ በይፋ የፋይናንስ ትምህርትን (የቁጠባ፣ የዕቅድና የበጀት አጠቃቀምን ጨምሮ) በትምህርት ቤት ስርአተ-ትምህርት ያካተተች መሆኗ እንዳለ ሆኖ (Hopkins et al., 2012)፣ እንደዚህ ዓይነት የክህሎት ግንባታ በንቃት እንደተተገበረ የሚያሳይ በአይነታዊ ምርምራችን የተገኘው ማስረጃ አነስተኛ ነው። ምንም እንኳን መንግሥት በ2025 የመካከለኛ ገቢ ደረጃን ለማሳካት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕድሎችን እያሳደገ ቢሆንም፣ የመደበኛ ሥልጠና ዕድሎች ተደራሽነት አሁንም ዝቅተኛ ነው (Belete, 2011)። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቅበላ ቀንሷል (MoE, 2018)። በጥናታችን ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ በርካታ ወጣቶች የገለጹት፣ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ካላገኙ ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለመግባት የማይፈልጉ መሆናቸውንና የዚህም ምክንያት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ያለውን ከፍተኛ ክብር የሌለውና በጣም ውድ ስለሆነም ነው። ከማህበረሰብ ሐ (ደቡብ ጎንደር)፣ አንድ በዕድሜ ከፍ ያለ ታዳጊ እንደገለፀው፣ ‹‹በወር በ90 ብር ክፍያ ያለው በመሆኑ ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መግባት አልፈልግም ነበር... ይልቁንም ዲግሪዬን ለመቀጠል ፈልጌ ነበር። ከጊዜ በኋላ በእብናት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ በኤሌክትሪሲቲ የዲፕሎማ ትምህርት ጀመርኩ። ነገር ግን ቤተሰቦቼ የሚያደርጉልኝን ድጋፍ ስላቆሙ እኔም ትምህርቴን አቆምኩ... ከዚያ ወደ ሱዳን ሄጄ የሰሊጥ ሰብል መሰብሰብ ሥራ ለመስራት ሄድኩ።››

የክህሎት ክፍቱም እንዲሁ በጾታ የተለየ ነው። በአንድ በኩል የጾታ እኩልነትን ለማጎልበት በመንግስት በኩል ካለው ቁርጠኝነት የተነሳ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከተመዘገቡት ውስጥ ግማሽ ያህል የሚሆኑት ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች ሲሆኑ (MoE, 2018)፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆች የተለያዩ ትምህርቶችን እንደሚመርጡ ታዳጊዎቹ አስተውለዋል። በቀደሙት ጊዜያት ልጃገረዶች እንደ ፀጉር ስራ፣ ምግብ ዝግጅትና የጽሕፈት ሙያዎች በመሳሰሉት የሴት ተብለው በተፈረጁ ስልጠናዎች ላይ የተገደቡ ሲሆን (Tefera and Pereznieto, 2013)፣ የኛ ግኝቶች እንደሚጠቁሙት ይህ ልማድ መለወጥ ጀምሯል፡ ፡ ሆኖም ልጃገረዶች በመንግስት መስሪያ ቤቶች መቀጠር የሚያስችሏቸውን ኮርሶችን ለመምረጥ የሚያዘነብሉ ሲሆን ወንዶች ደግሞ የራሳቸውን ንግድ ለማቋቋም ሲሉ የግንባታና የምህንድስና ኮርሶችን የመውሰድ አዝማሚያቸው ከፍተኛ ነው። በድሬዳዋ የሚኖር አንድ ታዳጊ እንዳስረዳው፣ ‹‹ወንዶች ብዙውን ጊዜ ቴክኒካዊና ጉልበት የሚጠይቁ ትምህርቶችን በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ይማራሉ። የራሳቸውን የንግድ ሥራ ይከፍታሉ፡ ፡ ልጃገረዶች ግን ኮምፒተር ሳይንስ ወይም አይቲ [መረጃ ቴክኖሎጂ] ለመማር ይመርጣሉ እናም ሥራ ለመቀጠር ይሞክራሉ።››

## 6.4 ሀብትና ንብረት ማፍራት

የታዳጊዎች እንደ መሬትና የቁም ከብት ያሉ ምርታማ ሀብቶች ተደራሽነትና እንደ የቁጠባ ሂሳብና ብድር ላሉ የገንዘብ ሀብቶች ተደራሽነት፣ በተለይም ለሴት ልጆችና ለወጣቶች፣ በአንፃራዊነት ውሱን ይመስላል (Bekele and Worku, 2008; Bezu and Holden, 2014a; 2014b; CSA and ICF, 2017)። የቅርብ ጊዜ የስነህዝብና

ጤና ጥናት እንደገለጸው፣ ዕድሜያቸው ከ15–19 ካሉት ታዳጊዎች ውስጥ 8% የሚሆኑት ሴቶች ልጆችና 10% የሚሆኑት ወንዶች ልጆች ብቻ የባንክ ሂሳብ ይጠቀማሉ (CSA and ICF, 2017)። የዳሰሳ ጥናት ግኝታችን በተመሳሳይ የጾታ ልዩነቶች መኖራቸውን ያሳያል፡ ፡ ለምሳሌ፣ በከተሞች ውስጥ በዕድሜ ከፍ ያሉ ወንዶች ልጆች (39%) ከሴቶች ልጆች (21%) ይልቅ በገንዘብ ላይ የመቆጣጠር ዕድላቸው ከፍተኛ ነው:: በተመሳሳይ የአይነታዊ ምርምራችን እንዳመለከተው ብድር ማግኘት የሚችሉት በዕድሜ ከፍ ያሉ የከተማ ታዳጊ ወንዶች ብቻ ናቸው። ወጣቶች ብድር ለማግኘት ዋስትና ለማቅረብ የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ መንግስት ለወጣቶች በማህበር እያደራጀ የቡድን ብድር ይሰጣል፡ ፡ የተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች ቢኖሩም፣ መርሃግብሩ ያሉበት ችግሮች ረዘም ላለ ጊዜ መዘግየት፣ የካፒታል መጠን ውስን መሆንና በብዛት ችግር ውስጥ ያሉ ወጣቶች ዋስትና ማቅረብ አለመቻል ናቸው። አንዲት በዕድሜ ከፍ ያለች ልጃገረድ ከደብረ ታቦር እንዳብራራችው፣ ‹‹በቅርቡ ስራ አጥ ወጣቶችን የሚመዘግበውን ሰው በድጋሚ ስጠይቀው 10,000 ብር ብድር እንድወስድና የዶሮ እርባታ እንድጀምር ነገረኝ። ሆኖም ይህንን ገንዘብ ለመውሰድ ዋስ ሊሆነኝ የሚችል ማንም የለኝም። ስለዚህ መንግስት የድሆችን ችግር እንዲያጤን እጠይቃለሁ። አዎ፣ በከተማ ውስጥ እንደ እኔ አይነት ተመሳሳይ ችግሮች ያሉባቸው ብዙ ልጃገረዶች አሉ… ሌላ የማውቃት ልጅ እንዲሁ መንግሥት ብድር እንዲሰጣት ጠየቀች። እሷም እንደ እኔ በማህበር እንድትደራጅ ተነገራት። እሷም እንደኔ ምንም ገንዘብ አልነበራትም።››

መደበኛ የባንክ ሂሳብ ተደራሽነት እንኳን ሳይቀር በጣም የተገደበ ነው። አንድ በዕድሜ ከፍ ያለ ታዳጊ ከማህበረሰብ ሐ (ደቡብ ጎንደር) እንደተናገረው፣ ‹‹ብዙ ባይሆንም ለመቆጠብ እሞክራለሁ… የባንክ የቁጠባ ደብተር አለኝ… ቤተሰቤ የሚደግፈኝ ከሆነ ትምህርቴን መቀጠል እፈልጋለሁ። በምቀጥበውም ገንዘብ በግል ኮሌጅ መማርና ከዚያም የመንግስት ሰራተኛ መሆን እፈልጋለሁ።››

በናሙናችን ውስጥ ከታካተቱት ታዳጊዎች ያገኘነው ማስረጃ መደበኛ ያልሆነ የቁጠባ ዓይነት በብዛት የሚጠቀሙ መሆኑን ነው። ከማህበረሰብ ቀ (ምስራቅ ሀረርጌ) አንዲት በዕድሜ ከፍ ያለች ልጃገረድ እንደገለጸችው፣ ‹‹ከ100 ኪሎ ለውዝ 50 ብር ትርፍ አገኘሁ… ትርፉን አስቀምጣለሁ… የቁጠባ ሳጥን አለኝ… ለቤተሰቦቼ አስቀምጥላቸዋለሁ።›› በደቡብ ጎንደር ተመሳሳይ ዕድሜ ያላቸው ልጃገረዶች እንዳሉት በተዘዋዋሪ መንገድ በወላጆቻቸው አማካይነት በባህላዊ ቁጠባዎች ወይም በእድሮች ውስጥ ተካተዋል።

## 6.5 ተመጣጣኝና ከእድሜ ጋር አግባብ ያለው ሥራ ማግኘት

ምንም እንኳን ዝቅተኛው ስራ የመቀጠሪያ ዕድሜ 14 ዓመት ቢሆንም፣ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ያለባት ሀገር ናት (UNESCO, 2012)። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ወንዶች ከሴቶች ይልቅ ተከፍሏቸው የሚሠሩ ሲሆን ልጃገረዶች ግን በሙሉ ጊዜያቸው ወላጆቻቸውንና የባላቸውን ቤተሰቦች በነጻ ማገልገል

> **ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ትንሽ ናቸው ተብሎ ሲለሚታሰብ ስራ እንዲሰሩ አይፈቀድላቸውም፤ ነገር ግን የ8 ዓመት ልጅ ሆኖ ቁመቱ ትልቅ ከሆነ ሊያሰሩት ይችላሉ።**
>
> (አንድ ቁልፍ የመረጃ ሰጪ፣ እብናት፣ ኢትዮጵያ)

ይጠበቅባቸዋል (CSA, 2014b; Jones et al., 2017; Pankhurst et al., 2018)።

የጌጅ የዳሰሳ ጥናት ግኝቶች እነዚህን ጥናቶች ያስተጋባሉ፡ ፡ ወጣት ታዳጊ ወንዶች (6%) ከሴቶች ልጆች (5%) ይልቅ ተከፍሏቸው የመስራት የበለጠ ዕድል ያላቸው ሲሆን፣ በተመሳሳይ ለትላልቅ ታዳጊ ወንዶች (30%) በክፍያ የመስራት ዕድል ከሴቶች ልጆች (15%) ሲነጻጸር ከፍ ያለ ነው። ከዚህ አንጻር ሁለት ወሳኝ ክልላዊ ልዩነቶች ታይተዋል፡ (1) በአፋር አይነታዊ የምርምር ግኝቶቻችን እንደሚያመለክቱት ታዳጊዎች ተከፍሏቸው ሥራ የማግኘት ዕድላቸው አነስተኛ ነው። ይህ የሚያሳየው ምንም እንኳን ታዳጊዎች በእረኝነት ሥራ ላይ ዘወትር የሚሰማሩ ቢሆኑም ትርፉ ትዳር እስከሚይዙ ድረስ በወላጆች እጅ የሚቆይ መሆኑን፣ እና (2) በከተማ ከሚገኙ ምላሽ ሰጭዎች መካከል በባቱ የሚገኙ ታዳጊዎች የሚያንቀሳቅሱት ገንዘብ የማግኘት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። ይህ ሊሆን የቻለው ባቱ የምርምር ጣቢያዎቻችን አካባቢ በሚገኘው የአበባ እርሻ ከሌሎች የኦሮሚያና አጎራባች የደቡብ ክልል ዞኖች ያሉ ታዳጊዎች በመሳባቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል።

የአይነታዊ ምርምር ግኝታችንም እንዲሁ ከሌሎች ጥናቶች ጋር በሚስማማ መልኩ በክፍያ በሚሰሩ ሥራዎች ላይ የሚሳተፉ ልጃገረዶች ዝቅተኛ ክፍያ ባላቸውና እንደ የቤት ውስጥ ሥራ ባሉ አደገኛ የስራ ዘርፎች የመገደብ አዝማሚያ አላቸው (Broussar and Tekleselassie, 2012; Loveday and Dom, 2016; Jones et al., 2014a; 2014b; 2016b; 2016c; 2017)፡ ፡ ሆኖም ልጃገረዶች ለእንደዚህ አይነቶቹ የሥራ ዕድሎች የበለጠ አዎንታዊ አመለካከት ነበራቸው። ከደቡብ ጎንደር አንዲት የ15 ዓመት ልጃገረድ እንዳብራራችው፣ ‹‹የቤት ሰራተኛ ሆነን እየሰራን መማር እንችላለን። እየሰራን ትምህርታችንን መጨረስ እንችላለን፡ ፡ ደሞዝተኛ ስለምንሆን እራሳችንን ችለን ስለራሳችን መወሰን እንችላለን።››

በቤት ሰራተኝነት በሚደረገው አለም አቀፍ ስደት (በተለይም ወደ መካከለኛው ምስራቅ) ስለሚገጥመው ስጋት ግንዛቤ እያደገ ቢሆንም በምርምር ጣቢያዎቻችን ያሉ ምላሽ ሰጪዎች በዋነኝነት በአለም አቀፍ ስደት ለይ ተስፋ እንደጣሉ ነው። ከድሬ ዳዋ አንዲት የ16 ዓመት ታዳጊ እንደገለጸችው፣ ‹‹እንደ ታላቅ ወንድሜ መሆን እፈልጋለሁ፣ ቤተሰቡን በጣም ይወዳል። ከማግባቱ በፊት እናቴን እዚህ አምጥቶ ከእሷ ጋር ይኖር ነበር። ወደ አረብ ሀገር ሄጄ ልክ እንደ እሱ እናቴን መርዳት እፈልጋለሁ።›› በወቅታዊ ስደት የሚሳተፉ ወንዶችም ልጆችም እንዲሁ ከፍተኛ አደጋ ላይ ናቸው። በተለይ በደቡብ ጎንደር የሚገኙ በዕድሜ ከፍ ያሉ ታዳጊዎች ህግና ስርዓት

በማይከበርባቸው የመተማና ሁመራ ዝቅተኛ ቦታዎች በሰሊጥ እርሻ ላይ በሚሰማሩበት ጊዜ ከፍተኛ ህመም (በተለይ የወባ በሽታ) እና ከአሰሪዎቻቸው ጥቃት (ግድያን ጨምሮ) እንደሚደርስባቸው ገልጸዋል።

## 6.6 ዕድሜና ጾታ ተኮር ማህበራዊ ጥበቃ ተደራሽነት

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አገልግሎት መርሃ ግብር (የሴፍቲ ኔት ፕሮግራም) በታዳጊዎች ላይ ስላመጣው ውጤት የተደባለቀ መረጃ አለ። በምግብ ዋስትና፣ በቤተሰብ ፍጆታ፣ በልጆች የእውቀት (ኮግኒቲቭ) ውጤቶችና (በተወሰነ ደረጃ) በልጆች አመጋገብ ላይ ጉልህ አዎንታዊ ተፅዕኖዎች ቢኖሩትም (Gilligan et al., 2009; Favara et al., 2019 Pankhurst et al., 2018)፣ በዕድሜ ከፍ ያሉ ታዳጊዎች በሴፍቲ ኔት ፕሮግራሙ ላይ በጉልበት ስራ ወላጆቻቸውን ተክተው ሊሰሩ እንደሚችሉ የሚያሳይ ማስረጃ አለ (Favara et al., 2019; Pankhurst et al., 2018).

በገጠር ማህበረሰቦች ውስጥ 31% የሚሆኑት ወጣት ታዳጊዎች (እና በግምት 4% የሚሆኑ በከተማ የሚገኙ ወጣት ታዳጊዎች) የሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ድጋፍ በሚቀበሉ ቤተሰቦች የታቀፉ ሲሆኑ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ደግሞ በዞን 5 (አፋር) ነው። ቤተሰቦቻቸው የሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች የነበሩ ታዳጊዎች በኢኮኖሚያዊ ደህንነታቸው ላይ አወንታዊ ውጤት ያስገኘላቸው መሆኑን አረጋግጠዋል። ከድሬዳዋ በዕድሜ ከፍ ያለች አንዲት ታዳጊ እንዳለችው፣ ‹‹ስለ ትምህርት ቤት ቁሳቁሶች ሳልጨነቅ መማር እችላለሁ። እኔም እንደ ጓደኞቼ መልበስ እችላለሁ።›› ለአንዳንድ የገጠር ታዳጊዎች የሴፍቲኔት ፕሮግራሙ ለወደፊት ዋስትናቸው ተስፋ ሰጥቷቸዋል። በእብናት (ደቡብ ጎንደር) የምትኖር ሌላ በዕድሜ ከፍ ያለች ታዳጊ እንዳስረዳችው፣ ‹‹የሴፍቲ ኔቱ ተጠቃሚ ከሆንሽ ጥሩ ባል ታገኛለሽ። ስለዚህ የሴፍቲ ኔት ተጠቃሚ የመሆን ዕድሉን ካገኘሁ ጥሩ ባል አግብቼ የተሻለ ሕይወት እንኖራለን።›› ነገር ግን ከታዳጊዎች የጊዜ አጠቃቀም ጋር የተያያዘው ሌላው ጠቃሚ ጉዳይ ነው። ቀጥተኛ ድጋፍ ከሚሰጣቸው የከተማ ተጠቃሚዎች በተቃራኒ የገጠር ተጠቃሚዎች የጉልበት ኮታ ማሟላት አለባቸው። ከእብናት አንድ ቁልፍ የመረጃ ሰጪ እንደገለጹት፣ በሕዝባዊ ሥራዎች ላይ በሚሠሩ ወጣቶች ላይ መደበኛ መመሪያ ቢኖርም ሲተገበር ግን አይታይም። ‹‹ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ትንሽ ናቸው ተብሎ ሲለሚታሰብ በሴፍቲ ኔት ፕሮግራሙ ላይ እንዲሠሩ አይፈቀድላቸውም፤ ነገር ግን የ8 ዓመት ልጅ ሆኖ ቁመቱ ትልቅ ከሆነ ሊያሰሩት ይችላሉ።››

## 6.7 የለውጥ ስትራቴጂዎች

በአጠቃላይ፣ የታዳጊዎችን ኢኮኖሚያዊ አቅም መደገፍ አሁን ካለው የፕሮግራም እና አገልግሎቶች አንፃር ደካማ ከሆኑ ዘርፎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በታዳጊዎችና በአዋቂዎችም ዘንድ ሰፊ የወጣቶች ሥራ አጥነትና ከደረጃ በታች ቅጥርን ጨምሮ እንደ ትልቅ አሳሳቢ ጉዳይ ታይቷል። ከሙያ ስልጠና ጋር በተያያዘ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አገልግሎት በወረዳና በዞን ከተሞች እና በትላልቅ ከተሞች ውስጥ ይሰጣል። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ስልጠናው የሚፈልገው የትምህርት ደረጃና ክፍያ ተጋላጭ የሆኑ ታዳጊዎች ሊያሟሉት ከሚችሉት በላይ ነው። ለወጣቶች የብድር አቅርቦት ተደራሽነት በሰፊው ተዘርግቷል፣ ነገር ግን በሚፈለገው መጠን አይደለም። እንዲሁም ተጨማሪ የክህሎት ግንባታ አለመኖር ብዙውን ጊዜ በወጣቶች የተጀመሩ ትናንሽ ንግዶች ይከስራሉ ማለት ሲሆን ይህም ከፍተኛ ዕዳ ያስከትላል።

ከማህበራዊ ጥበቃ አንፃር፣ ታዳጊዎች በተዘዋዋሪ ከሴፍቲ ኔት የህዝብ ስራዎች መርሃግብር ሊጠቀሙ ቢችሉም ቤተሰቦች ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ የታዳጊዎች ተጋላጭነቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም። በእርግጥ፣ እንደ ሌሎች የምርምር ማስረጃዎች (Favara et al., 2017; Pankhurst et al., 2018) ሁሉ፣ በአንዳንድ ማህበረሰቦች ውስጥ የህብረት ስራው ታዳጊዎችን በትምህርታቸው ላይ ጫና በማሳረፍ ወደ ስራ እንቅስቃሴዎች እንዲገቡ ሊያደርግ ይችላል። በልዩ ፍላጎት ትምህርት ለሚማሩ አካል ጉዳተኛ ታዳጊዎች ለትምህርት ወጪዎች በሚሰጥ ገንዘብ ወላጆች ልጆቻቸው ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ መፍቀድ እንዲችሉ በማበረታታት ረገድ ለውጦች የነበሩ ቢሆንም፣ የሚያስገኙት ጥቅም በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ወጣቶች ለጉልበት ብዝበዛ ወይም ፍላጎታቸውን ለማሟላት በልመና ስራ እንዲሰማሩ ያደርጋቸዋል።

# የፖሊሲና ትግበራ ምክረ ሀሳቦች

በሁሉም የስድስቱ የጌጅ አቅም ዘርፎች፣ የመሠረታዊ ምርምር ግኝቶቻችን በፖሊሲና በፕሮግራም አወጣጥ አንዳንድ ቁልፍ እንድምታዎችን ያመለክታሉ። እነዚህ ምክረ ሃሳቦች ኢትዮጵያ ከዘላቂ የልማት ግቦችና ከአለም አቀፍ ስምምነቶች እና ከአገሪቷ የሴክተር ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም ከተወሰኑ የታዳጊዎች ፖሊሲ ማዕቀፎች ጋር እንዴት እንደሚጣጣሙ በማጉላት የእነዚህን እንድምታዎች ዝርዝር መግለጫ አስቀምጠናል። ዋና ዋና ነጥቦችን ጠቅለል አድርገን እንደሚከተለው አቅርበናል።

## ትምህርትና መማር

- ታዳጊዎችን አሰልጣኝ በመመደብ የተግባር ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ምኞታቸውን እንዲያሳኩ መደገፍ፣
- ወላጆች ታዳጊ ልጆቻቸውን (በተለይም ሴቶች ልጆቻቸውን) በትምህርታቸው ስኬታማ ለማድረግ ምን ማድረግ እንደሚችሉ፣ ተግባራዊ መመሪያን ጨምሮ ስለትምህርት አስፈላጊነት ግንዛቤያቸውን ማሳደግ፣
- በመምህራን ጥቅማጥቅምና ስልጠና ላይ በማተኮርና በቂ ብቃት ባላቸው ትምህርት ቤቶች ላይ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ እየሰሩ ለሚማሩ ታዳጊዎች የማታ ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት የትምህርት ተደራሽነትን እውን ማድረግ፣
- በትምህርት ውጤቶች ላይ ትኩረት በማድረግ፣ የማጠናከሪያና ማካካሻ ትምህርቶችን በመስጠት በብሔራዊ ፈተናዎች የማያልፉ የገጠር ተማሪዎች አስፈላጊ የሆነው ደረጃ ላይ ለመድረስ እንዲችሉ መረዳት፣
- በትምህርት ቤቶች አወንታዊ የስነ-ምግባር ማስተካከያ አማራጮችን በማሳየትና አካላዊ ቅጣትን ፈጽሞ በማስቀረት በመምህራን የሚደርሰውን ጥቃት በፍጥነት ማረም፣
- ተጨማሪ ትምህርት ቤቶችን በመገንባት፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሎጂስቲካዊ ድጋፍ እንደ መጓጓዣና ለገጠር ተማሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ ማረፊያ (በተለይም የሴት ልጆች ወሲባዊ ጥቃት ስጋት ባለበት ሁኔታ) በማመቻቸት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን መደገፍ፣

## አካላዊ ምሉዕነትና ከጥቃት ነጻ መሆን

- ከታዳጊ ልጃገረዶችና ወንዶች ልጆች ጋር በአፍላ ዕድሜ ትምህርት ክፍለ ጊዜዎች፣ በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጭ ባሉ ክለቦችና ሚዲያዎች በመሳተፍ ወሲባዊና ጾታ ተኮር ጥቃትን ስለሚያደርሱ ማህበራዊ ደንቦች ግንዛቤያቸውን ማሳደግና ችግሮቹን እንዲቋቋሙ መርዳት፣ ይህ የሴት ልጅ ጥቃትን የተለመደ አድርጎ ማሰብን፣ በሴቶች ወሲባዊ ንፅህና ላይ አፅንዖት መስጠትንና የወንዶችን በጉልበት የመጠቀም ችግሮችን መቅረፍ እንዲሁም ጥቃት ለደረሰባቸው ምላሽ የሚያገኙበትን ትክክለኛ መንገድ እንዲያውቁ ግንዛቤ ማሳደግ የሚያስችሉ መልዕክቶችን ማካተት አለበት።
- የታዳጊዎችን ለጥቃት ተጋላጭነቶችን የሚፈጥር ሁኔታን እንዲሁም ጥቃቶችን የመከላከልና ምላሽ የሚያገኙባቸውን መንገዶች ግንዛቤ ማሳደግን በተመለከተ ከወላጆችና ከማህበረሰቡና ከሃይማኖት መሪዎች ጋር መሳተፍ/ አብሮ መስራት፣
- ከጥቃት ነጻ የሆኑ ትምህርት ቤቶችን ለመፍጠር ተማሪዎች ማንነታቸው ሳይታወቅ ጥቆማ የሚያቀርቡባቸውን አማራጮች ማስቀመጥና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመምህራንን ስነምግባር ለማስተካከል ስርዓት ለበዘርጋት ከትምህርት ቤቶች ጋር አብሮ መስራት፣
- ያለዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛት/ብልት መቁረጥ/ ስለሚያስከትለው አደጋና ችግሩ ስለሚቀረፍበት ሁኔታ በትምህርት ቤቶች የተማሪ ክለቦች (በተለይም የልጃገረዶችና የስርዓተ ጾታ ክለቦች) እና የተማሪ ፓርላማዎች ውይይቶችን ማስፋት፣
- ለፖሊስ እና ለፍትህ አካላት በሥርዓተ ጾታና እድሜ ተኮር ሥልጠና በመስጠት መደበኛ የፍትህ ስርዓቱን ማጠናከር፣ በማህበረሰቡና በአከባቢው አገልግሎት ሰጭዎች ዘንድ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ፣
- የኢትዮጵያ አዲስ የማኅበራዊ ጉዳይ ሠራተኞች በዕድሜ ፣ በጾታ እና በስርዓተ ጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት የደረሰባቸውን ለመለየትና ተገቢ የሆኑ ምላሾችን ለመስጠት የሰለጠኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

## ንነት፣ አመጋገብና ጾታዊና ስነ-ተዋልዶ ጤና

- በትምህርት ቤት ያሉ መድረኮችን ጨምሮ ለታዳጊዎች የጤና ግንዛቤና አገልግሎቶች ተደራሽነትን ማጠናከር
- በቤት ውስጥና በትምህርት ቤት የምግብ ድጋፍን እንደ ማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራም ዋና አምድ ማስፋፋት እና ድጋፉ በድርቅ ምክንያት ወይም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ ለተከሰተ የምግብ ዋስትና ችግር የሚደረግ መሆኑን ማረጋገጥ።

- የጾታና ስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተደራሽነት አስፈላጊነትን ጨምሮ በወላጆች እና በማህበረሰብ መሪዎች ዘንድ ማህበራዊ ተቀባይነትን እንዲያገኝ በማድረግ በአፍላ ወጣትነት ትምህርት ላይ ትኩረት ማድረግ፣
- በትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ውጭ ባሉ የሴቶች ክለቦች አማካይነት ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ ተደራሽነት ማሳደግ፣
- በአመቺ ሰዓቶችና ሚስጥራዊነት ላይ በማተኮር ለታዳጊዎች ተስማሚ የሆኑ የጾታዊና ስነተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ጥራትና ተደራሽነትን ማስፋት

## ማህበራዊና ስነልቦናዊ ደህንነት

- ከጥቃት ነጻ የሆኑ የዲሲፕሊን አካሄዶችን ጨምሮ ወጣቶችን ወደ ጉርምስና ዕድሜው በሚሸጋገሩበት ጊዜ ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ለወላጆችና ለአስተማሪዎች ስልጠናና መመሪያ መስጠት፣
- በተሻሻለው የመምህራን ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት በክፍል ውስጥ ተሳትፎን የሚያበረታቱ ደበልጥ ለህጻናት ተስማሚ የሆኑ የማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም፣
- ታዳጊዎች በተለይም ሴቶች ልጆች ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ ከእኩዮቻቸው ጋር ጊዜ የሚያሳልፉባቸውን ቦታዎች ማዘጋጀትና ለማህበረሰባቸው አስተዋፅኦ የሚያደርጉባቸው የወጣት ማዕከላት ማጎልበት፣ የክፍል ትምህርቶችንና ክለቦችን በመጠቀም ደህንነታቸው ያልተጠበቀባቸውን አካባቢዎች ለመለየትና ደህንነታቸው ካልተጠበቀ ቦታዎች ራሳቸውን እንዲያርቁ በሚያስችል መንገድ እንዲያስቡ እንዲሁም በማህበረሰባቸው ውስጥ በበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ እድሎችን ማመቻቸት፣
- ያገቡ ልጃገረዶች፣ ከብት የሚጠብቁ ወንዶች ልጆች፣ የቤት ሠራተኞች፣ ስደተኛ ሠራተኞችና የመንገድ ዳር ሕፃናት የመሳሰሉትን በጣም የተገለሉ ቡድኖችን መድረስና ፕሮግራም ቀርጾ ተጎጂ ታዳጊዎችን መርዳት፣
- የታዳጊዎችን የአእምሮ ጤንነት ፍላጎቶች እንዲደግፉ የሰለጠኑ የማኅበራዊ ስራተኞች ማብዛት፣ ድጋፍና የምክር አገልግሎት የሚፈልጉ ወጣቶችን እንዴት መለየት እንደሚችሉ ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና ለአስተማሪዎች ሥልጠና መስጠት፣
- የታዳጊዎች የሞባይል ስልኮች ተደራሽነትና አለም አቀፍ መልካም ተመክሮዎችን በመጠቀም የሥነ ልቦና ችግር / የአእምሮ ህመም ያለባቸው ታዳጊዎች ላይ መስራት፣

## ድምጽና ውሳኔ ሰጪነት

- ከማህበረሰቡ አርአያ የሚሆኑ ግለሰቦችን በማሳተፍ ወጣቶች ስለወደፊቱ የህይወት መንገዳቸው ተግባራዊ በሚሆኑ ሀሳቦች ላይ ልምድ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በትምህርት ቤትና በወረዳ ደረጃ የቀድሞ ተማሪዎች ማህበራትን ማቋቋምና በአካባቢው ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጋር በማስተሳሰር ከአርአያዎች እና አማካሪዎች ጋር በመደበኛነት እንዲገናኙ ማድረግ፣
- ታዳጊዎች ደህንነቱ የተጠበቀ መረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም በአስተማማኝ የበይነመረብ አጠቃቀምን ጨምሮ ታዳጊዎችና ወላጆች አስተማማኝ የመረጃ ተደራሽነት ትምህርት እንዲያገኙ መደገፍ፣
- በጊዜ ሂደት በሁሉም የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ቤተ መጻሕፍቶችንና የኮምፒውተር ቤተ ሙከራዎችን ለማቋቋም ለጋሽና መንግስታዊ ካልሆኑ መንግስታዊ ድርጅቶች ጋር መስራት፣
- የተሳትፎ ዕድሎችን ለማበረታታት በትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደ የሕጻናት ፓርላማ፣ የልጃገረዶች ክለብና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች የመሳሰሉ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ማስፋፋት፣

## የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት

- በፋብሪካዎች፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮች እንዲሁም በቤት ሰራተኝነትና ከሀገር ውጪ በስደት ላይ ላሉ ደህንነቱ የተጠበቀና የጉልበት ብዝበዛ የሌለበት የስራ ልምምድ እንዲኖር ማድረግና ግንዛቤ ማስጨበጥ፣
- የጉልበት ብዝበዛና በደል ሲደርስ በወጣቶች ማእከሎች ፣ በማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች ፣ ወዘተ ሪፖርት ለማድረግ ስም-አልባ መረጃ ማቀበያ ሰንሰለቶችን ማሻሻል፣
- ወጣቶች እስከ 8ኛ ክፍል መጨረሻ ድረስ በትምህርት ቤት እንዲቆዩ በማድረግ የታዳጊዎችን መሰረታዊ የሂሳብና የፋይናንስ ክህሎቶችን ማሻሻል፣ የታዳጊዎች ደህንነት በኢትዮጵያ፡ በጾታ የተለዩ ችሎታዎች፣ አውዶችና የለውጥ ስትራቴጂዎች ፍተሻ
- በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕድሎች ላይ ዝርዝርና ተደራሽ የሆነ መረጃና መመሪያ በመስጠት (በተለይም ለገጠር ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች)፣ መሰናክሎችን በመቀነስ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የሚጀምሩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎችን በማዘጋጀትና በገበያ ፍላጎቶች ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግ ስለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ግንዛቤ ማስጨበጥና የቀበላ መጠኑን ማሻሻል፣
- በክለቦች፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በወጣት ማዕከላት በኩል የታዳጊዎችን በተለይም የሴቶችን የቁጠባ ዕድሎች ተደራሽነት ማሳደግ፣ እንዲሁም በዕድሜ ከፍ ላሉ ታዳጊዎች በተለይም ለሴቶች በክልሎች የብድርና ቁጠባ ተቋማት በኩል የብድር ፕሮግራሞችን ተደራሽ ማድረግ፣
- በገጠርና በከተማ አካባቢዎች የሴፍቲኔት ፕሮግራሙ ታዳጊዎችን በተለይም የአካል ጉዳተኞችን፣ በተፈናቀሉ ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉ ታዳጊዎችን፣ እና ያለዕድሜ የግዴታ ጋብቻ ተጋላጭ የሆኑ ልጃገረዶችን ያገናዘበ መሆኑን ለማረጋገጥ የኢትዮጵያን ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣

# ማጣቀሻዎች


Abera, M., Robbins, J. and Tesfaye, M. (2015) 'Parents' perception of child and adolescent mental health problems and their choice of treatment option in southwest Ethiopia' Child and Adolescent Psychiatry and Mental Health 9(40)

Abubakar, A. and Fischer, R. (2011) 'The factor structure of the 12-item General Health Questionnaire in a literate Kenyan population' Stress and Health (28): 248–254

Alemu, Y. (2013) 'Assessment of provisions of guidance and counseling services in schools in East Harerge Zone and Hareri Region, Ethiopia' Middle Eastern and African Journal of Educational Research 28(2)

Asfaw, A. and Hagos, B. (2008) Desk review, case assessment on the present situation of corporal punishment, sexual abuse and bullying in schools in Ethiopia. Addis Ababa: Plan Ethiopia

Baird, S., de Hoop, J. and Özler, B. (2013) 'Income shocks and adolescent mental health' The Journal of Human Resources 48(2): 370–403

Bastian, J., Steer, L., Berry, C. and Lichtman, L. (2013) Accelerating progress to 2015: Ethiopia. Paris: The Good Planet Foundation

Bekele, E. and Worku, Z. (2008) 'Women entrepreneurship in micro, small and medium enterprises: the case of Ethiopia' Journal of International Women's Studies 10(2): 3–19

Belete, S. (2011) 'Literacy, skills training and entrepreneurship – support for rural women in Ethiopia' in M. Ballara, H. Hinzen, C. Medel-Añonuevo and R. Schwartz (eds.) Non-formal skills training: adult education for decent jobs and better lives. Bonn: DVV International

Bevan P. and A. Pankhurst (2007) Power Structures and Agency in Rural Ethiopia Development Lessons from Four Community Case Studies. (http://siteresources.worldbank.org/INTEMPOWERMENT/Resources/Ethiopia_Power_Structures_and_Agency.pdf)

Bezu, S. and Holden, S. (2014a) Land access and youth livelihood opportunities in Southern Ethiopia: Summary report. Nairobi: United Nations Human Settlements Programme (UN-Habitat)

Bezu, S. and Holden, S. (2014b) 'Are rural youth abandoning agriculture?' World Development 64: 259–272

Bireda, A.D. and Pillay, J. (2017) 'Perceived parental involvement and well-being among Ethiopian adolescents' Journal of Psychology in Africa 27(3): 256–259

Blake S., M Boone, A Kassa, and M. Sommer (2018) 'Teaching Girls About Puberty and Menstrual Hygiene Management in Rural Ethiopia: Findings From a Pilot Evaluation'. Journal of Adolescent Research, 33(5): 623-646

Broussar, N.H. and Tekleselassie, T.G. (2012) Youth unemployment. Ethiopia country study. London: London School of Economics and Political Science

Camfield, L. (2011) 'A girl never finishes her journey': mixing methods to understand female experiences of education in contemporary Ethiopia' Research Papers in Education 26(4): 393–412

Camfield, L. and Tafere, Y. (2009) '"No, living well does not mean being rich": diverse understandings of well- being among 11–13-year old children in three Ethiopian communities' Journal of Children and Poverty 15(2): 119–138

Camfield, L. and Tafere, Y. (2011) 'Community understandings of childhood transitions in Ethiopia: different for girls?' Children's Geographies 9(2): 247–62

Catholic Relief Services (CRS) (2013) A sample gender analysis. Baltimore: Catholic Relief Services (www.crs.org/sites/default/files/tools-research/a-sample-gender-analysis.pdf)

Chant, S., Klett-Davies, M. and Ramalho, J. (2017) Challenges and potential solutions for adolescent girls in urban settings: a rapid evidence review. London: Gender and Adolescence: Global Evidence

Chuta, N. (2017) Young women's household bargaining power in marriage and parenthood in Ethiopia. Young Lives Working Paper 166. Oxford: Young Lives

Central Statistical Agency (CSA) of Ethiopia and ICF (2017) Ethiopia Demographic and Health Survey 2016. Addis Ababa, Ethiopia, and Rockville, Maryland, USA: CSA and ICF

Community Based Monitoring System International Network CBMSIN (2018) Youth Unemployment and Entrepreneurship in Ethiopia: Evidence from Dire Dawa and Addis Ababa. CBMS Network Updates XVI (1). June 2018. (https://www.pep-net.org/sites/pep-net.org/files/CBMS/Newsletter/June_Newsletter_rev071018.pdf)

Dercon, S. and Singh, A. (2013) 'From nutrition to aspirations and self-efficacy: gender bias over time among children in four countries' World Development 45: 31–50

Edmeades, J., Hayes R. and Gaynair, G. (2014) Improving the lives of married adolescent girls in Amhara, Ethiopia. A summary of the evidence. Washington DC: International Center for Research on Women

Erulkar, A. and Ferede, A. (2009) 'Social exclusion and early or unwanted sexual initiation among poor urban females in Ethiopia' International Perspectives on Sexual and Reproductive Health 35(4): 186–193

Erulkar, A. and Mekbib, T. (2007) 'Invisible and vulnerable adolescent domestic workers in Addis Ababa, Ethiopia' Vulnerable Children and Youth Studies 2(3): 246–256

Favara, M. (2017) Do dreams come true? Aspirations and educational attainments of Ethiopian boys and girls. Oxford: Young Lives (https://www.younglives-ethiopia.org/taxonomy/term/174)

Favara, M, C. Porther, and T. Woldehanna (2019) 'Smarter through Social Protection? Evaluating the Impact of Ethiopia's Safety-Net on Child Cognitive Abilities'. Oxford Development Studies, 47 (1) 79-96

Feeny, E. and Crivello, G. (2015) How gender shapes adolescence: diverging paths and opportunities. Oxford: Young Lives

GAGE Consortium (2019 forthcoming) GAGE Ethiopia Baseline Survey. London: Gender and Adolescence: Global Evidence

Gelaye, B., Tadesse, M.G., Lohsoonthorn, V., Lertmeharit, S., Pensuksan, W.C., Sanchez, S.E., Lemma, S., Berhane, Y., Vélez, J.C., Barbosa, C., Anderade, A. and Williams, M.A. (2105) 'Psychometric properties and factor structure of the General Health Questionnaire as a screening tool for anxiety and depressive symptoms in a multi-national study of young adults' Journal of Affective Disorders 187: 197–202

Gilligan D., J. Hoddinott, and A Taffesse (2009) 'The Impact of Ethiopia's Productive Safety Net Programme and its Linkages'. The Journal of Development Studies, 45(10): 1684-1706

GHE (Girl Hub Ethiopia) (2015) What do we know about girls in Ethiopia? Addis Ababa: Girl Hub Ethiopia

Hannigan, J. and Richards, G. (2017) 'Introduction' in J. Hannigan and G. Richards (eds.) The SAGE handbook of new urban studies. London: SAGE.

Heinonen, P. (2011) Youth gangs and street children: culture, nurture and masculinity in Ethiopia. New York: Berghahn Books

Hopkins, D., Porter, B., Perdomo, M. and Munoz, L. (2012) Insights from UNCDF's YouthStart Programme. Policy opportunities and constraints to access youth financial services. New York: UN Capital Development Fund

Igbatayo, S.A. and Babalola, O.O. (2014) 'The challenges of youth unemployment and regional stability in Africa: a comparative assessment of Ethiopia and Nigeria' Journal of Social and Economic Policy 11(2): 117–128

Jebena, M., D. Lindstrom, T. Belachew, C. Hadley, C Lachat, R. Verstaeten, N De Cock, and P. Kolsteren (2016)' Food Insecurity and Common Mental Disorders among Ethiopian Youth: Structural Equation Modeling'. PLoS ONE 11(11): e0165931

Jones, N., Tefera, B., Stephenson, J., Gupta, T., Pereznieto, P., Emire, G., Gebre, B. and Gezhegne, K. (2014a) Early marriage and education: the complex role of social norms in shaping Ethiopian adolescent girls' lives. London: Overseas Development Institute

Jones, N., Presler-Marshall, E., Tefera, B., Emirie, G., Gebre, B. and Gezhegne, K. (2014b) Rethinking girls on the move: the intersection of poverty, exploitation and violence experienced by Ethiopian adolescents involved in the Middle East 'maid trade'. London: Overseas Development Institute

Jones N., Tefera B., Presler-Marshall E., Gupta T., Emirie G., Gebre B. and K. Berhanu (2015) The power of dialogue. The role of community awareness interventions in ending child marriage in Amhara, Ethiopia. London: ODI

Jones, N., Presler-Marshall, E., Tefera, B. and Gebre, B. (2016a) The politics of policy and programme implementation to advance adolescent girls' wellbeing in Ethiopia. London: Overseas Development Institute

Jones, N., Tefera, B., Emirie, G., Gebre, B., Berhanu, K., Presler-Marshall, E., Walker, D., Gupta, T. and Plank, G. (2016b) One size does not fit all: the patterning and drivers of child marriage in Ethiopia's hotspot districts. London: UNICEF and Overseas Development Institute

Jones, N., Emirie, G., Tefera, B. and Presler-Marshall, E. (2016c) Surprising trends in child marriage in Ethiopia. London: UNICEF and Overseas Development Institute

Jones N., B. Tefera, W. Yadete, G. Emire, K. Gezahegne , K. Birhanu, N. Ahmed, and A. Vithlani (2017) Exploring Ethiopian adolescents' gendered experiences and perspectives: findings from formative qualitative research. London: ODI

Jones N., E. Presler-Marshall and M. Stavropoulou (2018a) Adolescents with disabilities: enhancing resilience and delivering inclusive development. London: ODI

Jones, N., Camfield, L., Coast, E., Samuels, F., Abu Hamad, B., Yadete, W., Amayreh, W., Bani Odeh, K., Sajdi, J., Rashid, S., Sultan, M., Presler-Marshall, E. and Malachoswka, A. (2018b) GAGE baseline qualitative research tools. London: Gender and Adolescence: Global Evidence

Jose, P.E., Ryan, N. and Pryor, J. (2012) 'Does social connectedness promote a greater sense of wellbeing in adolescence over time?' Journal of Research on Adolescence, 22(2): 235–251.

Kabeer, N. (2003) Making rights work for the poor: Nijera Kori and the construction of 'collective capabilities' in rural Bangladesh. Working Paper 200. Brighton: Institute of Development Studies

Katayama, R. (2019) 'Half of the world's poor live in just 5 countries'. TheDATABlog. The World Bank (https://blogs.worldbank.org/opendata/half-world-s-poor-live-just-5-countries)

Kassa, T.A., Luck, T., Bekele, A. and Riedel-Heller, S.G. (2016) 'Sexual reproductive health of young people with disability in Ethiopia: a study on knowledge, attitude and practice: a cross-sectional study' Globalization and Health 12(5)

Katsui, H., Ranta, E.M., Yeshanew, S.A., Musila, G.A., Mustaniemi-Laakso, M. and Sarelin, A. (2014) 'Reducing inequalities: a human rights-based approach in Finland's development cooperation with special focus on gender and disability: a case study on Ethiopia and Kenya'. Turku: Institute for Human Rights, Åbo Akademi University.

Lamblin, M., Murawski, C., Whittle, S. and Fornito, A. (2017) 'Social connectedness, mental health and the adolescent brain' Neuroscience and Biobehavioral Reviews 80: 57–68

Loveday, L. and Dom, C. (2016) Economic participation of women and girls in rural Ethiopia (2010-13). WIDE Discussion Brief No. 7 (http://ethiopiawide.net/wp-content/uploads/WIDE_DBSeriesII-Compilation.pdf)

Ministry of Education (2018). Educational Statistics. Annual Abstract 2009 (2016/2017). Addis Ababa: MoE.

Ministry of Health (2012) National mental health strategy 2012/13-2015/16. Addis Ababa: Ministry of Health

MoFED and UN Ethiopia (2012) Investing in boys and girls in Ethiopia: past, present and future. Addis Ababa: Ministry of Finance and Economic Development and the United Nations in Ethiopia

Mjaaland, T. (2018) 'Negotiating gender norms in the context of equal access to education in north-western Tigray, Ethiopia' Gender and Education 20(2): 139–155

Muz, J., Baird, S., Hamory Hicks, J., Faiz Rashid, S., Sultan, M. Yadete, W. and Jones, N. (2018) Finding the Hard to Reach: A Mixed Methods Approach to Including Adolescents with Disabilities in Survey Research, CROP Secretariat

Pankhurst, A., Negussie, N. and Mulugeta, E. (2016) Understanding children's experiences of violence in Ethiopia: evidence from Young Lives. Innocenti Working Paper 2016-25. Florence: UNICEF Innocenti Office of Research

Pankhurst, A., T. Woldehanna, M. Araya, Y. Tafere, J. Rossiter, A. Tiumelissan, and K. Berhanu (2018) Young Lives Ethiopia: Lessons from Longitudinal Research with Children of the Millennium, Country Report. Oxford: Young Lives.

Patton G, et al. (2012) Health of the world's adolescents: a synthesis of internationally comparable data. The Lancet, 379 (9826): 1665-1675

Pawson, R. and Tilley, N. (1997) Realistic evaluation. Thousand Oaks, CA: Sage

Pells, K. and Morrow, V. (2018) Children's experiences of violence: evidence from the Young Lives study in Ethiopia, India, Peru and Vietnam. Summary report. Oxford: Young Lives

Population Council and UNFPA (2010) Ethiopia young adult survey. A study in seven regions. Addis Ababa: Population Council

RISE (2018) RISE in Ethiopia. (https://www.riseprogramme.org/countries/ethiopia/rise-ethiopia-research-overview-non-technical)

Save the Children (2011) CORPORIAL PUNISHMENT OF CHILDREN IN ETHIOPIA. Addis Ababa: Save the Children Sweden.

Sen, A.K. (1984) Commodities and capabilities. Oxford: Oxford University Press

Sen, A.K. (2004) 'Capabilities, lists, and public reason: continuing the conversation', Feminist Economics 10(3): 77–80

Sewasew D., O. Braun-Lewensohn, and E. Kassa (2017) 'The contribution of guardian care and peer support for psychological resilience among orphaned adolescents in Ethiopia'. Contemporary Social Science, 12 (3-4) 175-188

Smith, L., Frankenberger, T., Langworthy, B., Martin, S., Spangler, T., Nelson, S. and Downen, J. (2015) Ethiopia Pastoralist Areas Resilience Improvement and Market Expansion (PRIME) Project impact evaluation. Baseline survey report. Volume 1: main report. Rockville, MD: Westat

Sommer, M., Ackatia-Armah, N., Connolly, S. and Smiles, D. (2015) 'A comparison of the menstruation and education experiences of girls in Tanzania, Ghana, Cambodia and Ethiopia' Compare: A Journal of Comparative and International Education 45(4): 589–609

Stavropoulou, M. and Gupta-Archer, N. (2017a) Adolescent girls' capabilities in Ethiopia: the state of the evidence. London: Gender and Adolescence: Global Evidence

Stavropoulou, M. and Gupta-Archer, N. (2017b) Adolescent girls' capabilities in Ethiopia: the state of the evidence on programme effectiveness. London: Gender and Adolescence: Global Evidence

Tadele, G. and Gella, A.A. (2012) 'A last resort and often not an option at all': farming and young people in Ethiopia' IDS Bulletin 43(6): 33–43

Tafere, Y. (2017) Educational Trajectories From Childhood to Early Adulthood: Aspirations, Gender and Poverty in Ethiopia. Oxford: Young Lives

Tafere Y. and T. Woldehanna (2012) Rural youth aspiring to occupations beyond agriculture:

Evidence from Young Lives Study in Ethiopia. A Paper Presented at the Young People, Farming and Food Conference Accra, Ghana From 19-21 March, 2012.

Tait, R.J., French, D.J. and Hulse, G.K. (2003) 'Validity and psychometric properties of the General Health Questionnaire-12 in young Australian adolescents' Australian and New Zealand Journal of Psychiatry 37(3): 374–381

Tefera, B. and Pereznieto, P., with Emirie, G. (2013) Transforming the lives of girls and young women. Case study: Ethiopia. London: ODI (https://www.odi.org/sites/odi.org.uk/files/odi-assets/publications-opinion-files/8820.pdf)

United Nations Development Programme (UNDP) (2015) National Human Development Report 2014 Ethiopia: accelerating inclusive growth for sustainable human development in Ethiopia. Addis Ababa: UNDP

UNDP (2018) Human Development Indices and Indicators: 2018 Statistical Update. New York: UNDP

United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization (UNESCO) (2012) EFA global monitoring report 2012. Youth and skills: putting education to work. Paris: UNESCO

United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization UNESCO (2015) Education For All global monitoring report 2015. Paris: UNESCO

United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization UNESCO (2018) Ethiopia. (http://uis.unesco.org/country/ET)

United Nations Population Fund (UNFPA) (2018) Worlds apart: reproductive health and rights in an age of inequality. New York: UNFPA

Wonde, D., Jibat, N. Baru, A. (2014) 'The dilemma of corporal punishment of children from parents' perspective in some selected rural and urban communities of Jimma zone, Oromia/Ethiopia' Global Journal of Human Social Science: Sociology & Culture 14(4): 17–27

World Bank (2018) Data. (https://data.worldbank.org/)

Woldehanna, T. and Pankhurst, A. (2014) Education and learning: preliminary findings from the 2013 Young Lives Survey (round 4) in Ethiopia. Oxford: Young Lives, University of Oxford

Woldehanna ,T., Araya, M. and Pankhurst, A. (2017) Education and learning: preliminary findings from the 2016 Young Lives Survey (round 5): Ethiopia. Oxford: Young Lives, University of Oxford

World Health Organization (WHO). 'Sexual and reproductive health: classification of female genital mutilation'. Accessed 2018 https://www.who.int/reproductivehealth/topics/fgm/overview/en/

Yèhoué, E., Kinoshita, N., Ramirez, G. and Wajid, S.K. (2013) The Federal Democratic Republic of Ethiopia. Selected issues. IMF Country Report No. 13/309. Washington DC: International Monetary Fund

# አባሪ: የጌጅ ኢትዮጵያ የምርምር ቦታዎች

## ሰንጠረዥ ሀ1: የከተማና ገጠር አካባቢዎች

| ክልል | ዞን | የከተማ አካባቢዎች | የገጠር ወረዳዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 10-12 ዓመት ዕድሜ ክልል<br>15-17 ዓመት ዕድሜ ክልል | 10-12 ዓመት ዕድሜክልል | ማህበረሰቦች (ቀበሌዎች) in-depth sites | | ማህበረሰቦች (ቀበሌዎች) light-touch sites | |
| | | | | ለወረዳ ከተሞች የቀረቡ | ራቅ ያሉ | ለወረዳ ከተሞች የቀረቡ | ራቅ ያሉ |
| አፋር[1] | ዞን 5 | | | | | | |
| | | | ዳሊፋጌ | | | | |
| | | | ዱዌ | | | | |
| | | | ሃደለላ | | | | |
| | | | **ሰሙሮቢ** | ሀ | ለ | | |
| | | | ተላላክ | | | | |
| አማራ[2] | ደቡብ ጎንደር | | | | | | |
| | | | **እብናት** | ሐ | መ | ሠ | ረ<br>ሰ |
| | | | ላይ ጋይንት | | | | |
| | | | ሊቦ ከምከም | | | | |
| | | | ስማዳ | | | | |
| | | | ታች ጋይንት | | | | |
| | | ደብረ ታቦር (የዞን ከተማ) | | | | | |
| ድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር | | ድሬ ዳዋ (ከኢትዮጵያ ትልልቅ ከተሞች አንዱ) | | | | | |
| ኦሮሚያ[3] | ምስራቅ ሀረርጌ | | | | | | |
| | | | ባቢሌ | | | | |
| | | | **ፌዲስ** | ሸ | ቀ | በ | ተ<br>ቸ |
| | | | ጉርሱም | | | | |
| | | | ሀረማያ | | | | |
| | | | ጃርሶ | | | | |
| | ምስራቅ ሸዋ | ባቱ (የወረዳ ከተማ) | አዳሚ ቱሉ ጂዶ | | | | |
| | | | ኮምቦልቻ | | | | |

1 ታዳጊ ክልል በአብዛኛው አርብቶአደር ነው (አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር)፤ የአፋር ብሔር የሕዝቡን 1.7% ይወክላል። ማስታወሻ: በአፋር ያለው የጋብቻ ዕድሜ የመረጃ ጥራት ቢያንስ በተወሰነ ደረጃ በተሳታፊዎቹ የቁጥር ዕውቀት ማነስ ምክንያት ችግር ያለበት እንደሆነ ይታመናል።

2 የአማራ ብሔር የህዝቡን 27% ይወክላል።

3 የኦሮሞ ብሔር የሕዝቡን 34% ይወክላል።

**በደማቅ የተጻፉ** = ዓይታዊ ምርምር የተካሄደባቸው አካባቢዎች.

ሰንጠረዥ ሀ2፡ የጌጅ ምርምር አካባቢዎች በኢኮኖሚና ማህበራዊ ተጋላጭነት መስፈርት

| ክልል | ዞን | የከተማ አካባቢዎች | የገጠር ወረዳዎች | የምግብ ዋስትና ስጋት ደረጃ[4] (ጁላይ 2016) | ያለዕድሜ ጋብቻ 10-14[5] ዕድሜ ላሉ ልጃገረዶች | ያለዕድሜ ጋብቻ ከ15-17[6] ዕድሜ ላሉ ልጃገረዶች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 10-12 የዕድሜ ክልል 15-17 የዕድሜ ክልል | 10-12 የዕድሜ ክልል | | | |
| አፋር | ዞን 5 | | | | 4.3% | 6.3% |
| | | | ዳሊፋጌ | 1 | 7.9% | 7.7% |
| | | | ደወ | 1 | 2.3% | 4% |
| | | | ሀደለላ | 1 | 3.6% | 5.5% |
| | | | **ሰሙሮቢ** | | **6.7%** | **10.4%** |
| | | | ተላላክ | 1 | 1.9% | 5.2% |
| አማራ | ደቡብ ጎንደር | | | | 9.8% | 29.4% |
| | | | እብናት | **1** | **12.7%** | **36.9%** |
| | | | ላይ ጋይንት | 1 | 7.1% | 25.4% |
| | | | ሊቦ ከምከም | የለም | 10.3% | 32% |
| | | | ስማዳ | 1 | 11.6% | 33.8% |
| | | | ታች ጋይንት | 1 | 7.1% | 25.3% |
| | | **ደብረ ታቦር** | | የለም | 8.9% | 8.7% |
| ድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር | | **ድሬ ዳዋ** | | 1 | 12.6% | 14.8% |
| ኦሮሚያ | ምስራቅ ሀረርጌ | | | | 15.2% | 32.3% |
| | | | ባቢሌ | 1 | 18.7% | 41.7% |
| | | | **ፈዲስ** | 1 | 21.9% | 53.1% |
| | | | ጉርሱም | 1 | 15.1% | 28.3% |
| | | | ሀረማያ | 1 | 21.6% | 38.3% |
| | | | ጃርሶ | 1 | 15.1% | 23.3% |
| | ምስራቅ ሸዋ | **ባቱ** | አዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ | 1 | 10.3% | 14.7% |

4 434 ወረዳዎች በብዙ ምድቦች ደረጃ ወጥቶላቸዋል፤ ከዚያም ከምግብ ዋስትና አንፃር ከ1–3ኛ ደረጃ ይመዳባሉ፤ ደረጃ 1 ከፍተኛ የምግብ ዋስትና ደረጃ ነው (https://data.world/ocha-ethiopia/76029294-3cbc-4bd0-8786-adcdb6475886).

5 በ2007 ህዝብ ቆጠራ እንደተዘገበው

6 በ2007 ህዝብ ቆጠራ እንደተዘገበው

**በደማቅ የተጻፉ** = ዓይታዊ ምርምር የተካሄደባቸው አካባቢዎች.

ሰንጠረዥ ሀ3:  የጎጅ ኢትዮጵያ መነሻ አይነታዊ ምርምር

| | | ጥምር ናሙና | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወጣት ታዳጊዎች (ከ10-14 ዕድሜ) | | በዕድሜ ከፍ ያሉ ታዳጊዎች (ከ15-19 ዕድሜ) | | ወንድምና እህት | | ወላጅ/አሳዳጊ | | አያት | | ጠቅላላ የታዳጊዎች ናሙና |
| | | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | |
| ቦታ | ከተማ | 16 | 18 | 27 | 30 | 7 | 10 | 29 | 39 | 0 | 2 | **91** |
| | ገጠር | 45 | 74 | 1 | 1 | 12 | 19 | 36 | 54 | 2 | 18 | **121** |
| | አርብቶ አደር | 15 | 17 | 1 | 3 | 8 | 6 | 17 | 20 | 0 | 0 | **36** |
| ድምር | | 76 | 109 | 29 | 34 | 27 | 35 | 82 | 113 | 2 | 20 | **248** |
| አካል ጉዳተኝነት | | 9 | 10 | 9 | 9 | (1) | (0) | (1) | (0) | (0) | (1) | **37** |
| የታዳጊው የቤተሰብ ሁኔታ | በወንድ የሚመራ ቤተሰብ | 59 | 88 | 12 | 18 | | | | | | | **177** |
| | በሴት የሚመራ ቤተሰብ | 12 | 20 | 8 | 6 | | | | | | | **46** |
| | በልጅ የሚመራ ቤተሰብ | 3 | 1 | 5 | 5 | | | | | | | **14** |
| ድምር | | 74 | 109 | 25 | 29 | | | | | | | **237** |
| የጋብቻ ሁኔታ | ያገባ | 0 | 6 | 0 | 9 | (3) | (7) | (76) | (80) | (2) | (7) | **15** |
| | የተፋታ | 0 | 4 | 0 | 2 | (0) | (2) | (1) | (20) | (0) | (2) | **6** |
| | በሞት የተለያየ | 0 | 0 | 0 | 1 | (0) | (0) | (1) | (12) | (0) | (10) | **1** |
| ድምር | | 0 | 10 | 0 | 12 | (3) | (9) | (78) | (112) | (2) | (19) | **22** |

## ስለ ጌጅ

ስርዓተ-ፆታና ታዳጊነት፡ አለማቀፍ ማስረጃ (ጌጅ) በደቡባዊ አለማት የሚገኙ የሴት ታዳጊዎችን ህይዎት ለመቀየር የሚያስችል ማስረጃ የሚያስስ የዘጠኝ አመት የረጅም ጊዜ ጥናት ፕሮግራም ነው፡፡ ለበለጠ መረጃ www.gage. odi.org.uk ን ይጎብኙ፡፡

## ማሳሰቢያ

ይህ ሰነድ ከእንግሊዝ መንግስት በእንግሊዘ የእርዳታ ድርጅት (UK aid) የገንዘብ ድጋፍ አማካይነት የተሰራ የስርዓተ-ፆታና ታዳጊነት፡ አለማቀፍ ማስረጃ (ጌጅ) ፕሮግራም ውጤት ነው፡፡ ይሁን እንጅ በሰነዱ የተጠቀሱት እሳቤዎችና የተካተቱት መረጃዎች የእንግሊዝን መንግስት ኦፊሴላዊ ፖሊሲዎች አያንፀባርቁም፤ እሳቤዎችና ወረጃዎችም የእንግሊዝ መንግስት ድጋፍ የላቸውም፤ ስለሆነም የእንግሊዝ መንግስት ሀላፊነት አይወስድም፡:


የጌጅ ፕሮግራም ቢሮ
ኦቨርሲስ ድቨሎፕመንት ኢንስቲቱት
203 በላክፍርያርስ መንገድ
ለንደን SE1 8NJ
እንግሊዝ
ኢሜይል፡ gage@odi.org.uk
ድህረገፅ፡ www.gage.odi.org


## Copyright

አንባቢዎች ይህንን ሪፖርት አትራፊ ላልሆነ የህትመት ስራ በቀጥታ በመጥቀስም ሆነ ተጨማሪ ስራን ለመስራት እንዲጠቀሙበት ይበረታታሉ (ለትርፍ የሚጠቀሙበት ከሆነ ግን ከጌጅ ፕሮግራም ቢሮ ጋር በgage@odi.org.uk በኩል መነጋገር የግድ ይላል) ፡፡ የባለቤት ባለመብት እንደመሆኑ፤ ጌጅ ተገቢዉን ምስጋናና የህትመት ኮፒ እንዲሰጠው ይፈልጋል፡፡ የጌጅን ህትመቶች ማጣቀስ ከፈለጉ ፤ እባክዎ አሳታሚውን ስርዓተ-ፆታና ታዳጊነት፡ አለማቀፋዊ ማስረጃ ብለው ያጣቅሱ፡፡ በቀጥታ የኢንተርኔት መስመር ለሚጠቀሙ፤ አንባቢዎች ቀዳሚ ስራዎቻችንን ከጌጅ ድህረገፅ **www.gage.odi.org** ጋር እንዲያያይዙት እንጠይቃለን፡፡

© ጌጅ 2020 ዓ ም. ይህ ስራ በክርኤቲቭ ኮመን አትሪቢዩሽን - አትራፊ ያልሆነ-ሼርአላይክ 4.0 አለም አቀፍ Creative Commons Attribution – NonCommercial-ShareAlike 4.0 International Licence (CC BY-NC-SA 4.0) ፈቃድ አግኝቷል፡፡

ISBN: 978-1-912942-15-2

የፊት ሽፋን፡ የአፋር ልጃገረዶችና እናቶች© ናታሊ በርትራምስ /ጌጅ 2012 ዓ.ም.

UK aid from the British people